የዚህ መጽሐፍ የቀድሞው ርእስ "Love & Marriage"

# በወጣቶች የሚነሡ ጥያቄዎች


በብሩስ እና ካሮል ብሪትን

ትርጉም - ዓለማየሁ ማሞ

እርማት፡- ጌቱ ግዛው




ከየትኛውም ዘር ወይም ባሕል ቢመጡም እንኳ በአሜሪካ፡ አፍሪካ፡ እስያና አውሮፓ የሚኖሩ ወጣቶች ያልተጠበቁ አደጋዎች ወይም ችግሮችን በማስወገድ እንዴት ጠቃሚና በደስታ የተሞላ ሕይወት መገንባት እንደሚችሉ ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ትምህርትን አግኝተዋል።




**Copyright**

© 2000 by S.I.M. Addis Ababa, Ethiopia. Originaly published in English under the title of *Questions Young People Ask* © 1999 by Worldwide Books, Box 190, Florida, 1710, South Africa.

All rights reserved.



BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

# ማውጫ


ምዕራፍ 1 በእርግጥ ጋብቻ በፍቅር የተሞላ ሊሆን ይችላልን? ..................... 1
ምዕራፍ 2 የተሻለው የጋብቻ ዓይነት የቱ ነው? ..................................... 13
ምዕራፍ 3 ወላጆቼን መተው አለብኝን? .................................................. 18
ምዕራፍ 4 ፍቅራችን እውነተኛ መሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለን? .......... 23
ምዕራፍ 5 ግብረ-ሥጋ? ........................................................................ 35
ምዕራፍ 6 ኤድስ? ................................................................................. 43


# ደብዳቤዎች


ናታን፡- ሦስት ልጃገረዶችን አስረግዞአል። ............................................ 51
ሣራ፡- ብጉር አለብኝ፤ ጡቶቼም በጣም ትላልቅ ናቸው። .......................... 51
ራሔል- ጡቶቼ እስካሁን ትናንሽ ናቸው? ............................................... 53
ሉቃስ፡- ተመለከትኳት፤ እንዴት ያለ ተክለ-ሰውነት፤ እንዴት ያማሩ
እግሮች አሏት! ...................................................................................... 53
እንድርያስ፡- የዘር ፈሳሽ ደካማ ሊሆን ይችላልን? .................................. 55
ስምዖን፡- ከሴት ጋር ሩካቤ- ሥጋ መፈጸም ኃጢአት ነውን? በኮንዶምስ? 55
ማርታ፡- የግብረ - ሥጋ ግንኙነት ተፈጥሮአዊ አይደለምን? ........................ 56
ኢሳይያስ፡- ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አልሞከርክም? ............... 57
ካሌብ፡- ፍትወት ሲያሰኘኝ ምን ላደርግ እችላለሁ? ................................... 58
ሊዎናርዶ፡- «ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ኃጢአት
አይደለም» ትላለች። ................................................................................ 61
ኢዩኤል፡- የዘር ፈሳሽ በሚወጣ ጊዜ በደለኝነት ይሰማኛል። ...................... 61
ሚርየም፡- ወሲባዊ ሕልሞችን አያለሁ፤ ስሜቱም አለኝ። .......................... 63
ሉቃስ፡- ፍትወተ-ሥጋን መለማመድ ይኖርብኝ ይሆን? ............................. 64
ኢዮስያስ፡- እንዴት ክርስቲያን መሆን እችላለሁ? .................................... 66
ጌዴዎን፡- ከእነርሱ ጋር መጠጣትን አቆምኩ። .......................................... 69
ሉይስ፡- አስወረድኩ። ........................................................................... 70
ርብቃ፡- ክርስቶስ የሚፈልገው ዋነኛ ነገር የቱ ነው? ................................. 71
ዶሪን፡- ስለ አንድ ወንድ ምን ማወቅ ይገባኛል? ...................................... 73

ሣራ፦ ፍቅርን ያዘለ ደብዳቤ ...74
አቤሴሎም፦ አንዳችን የሌላውን ብልት እንነካለን። ...75
ኤልሳቤጥ፦ «እስከ. . . ማንንም አልስምም» በማለት ለእግዚአብሔር
ቃል ገባሁ። ...76
ሴም፦ ፍቅሬ ይሟጠጥ ይሆን? ...78
አበኔር፦ ብሩስ የሌሎች ሴቶች ውበት ይማርከሃልን? ...81
ጋቪን፦ እግዚአብሔር የዝሙት ኃጢአቴን ይቅር ሊለኝ ይችላል? ...81
ዲቦራ፦ «ትዕግሥት ይኑርሽ፥ ባሎች ሁሉ አይታመኑም» ይሉኛል። ...82
ሐና፦ ባሌን ባለመፍታቴ ደስተኛ ነኝ። ...83
ናታን፦ ከማግባቴ በፊት ከእርስዋ ምን ማየት አለብኝ? ...84
ቪንሰንት፦ እጮኛ ለመያዝ ልጅ ነኝን? ...85
ፓትሪክ፦ እንዴት እንደምወዳት ልንገራትን? ...86
ዳዊት፦ አሁኑኑ ልንገራት ይሆን? ...87
ዴኒስ፦ ሦስት የምወዳቸው ልጃገረዶች አሉ። ...88
በርናርድ፦ ሚስት እፈልጋለሁ። ...88
ሲልቪያ፦ ወንድሞች ናቸው ወይስ አናብስት? ...89
ሮዳ፦ «እግዚአብሔር በራእይ አንቺን አሳየኝ» ብሎ ነገረኝ። ...89
ሩት፦ እግዚአብሔር ለምን ይቅር አይለኝም? ...90
አውድሬ፦ ከጓደኛዬ ጋር ሲሳሳሙ አገኘኋቸው። ...91
ዮሐና፦ ፍርሃቴ እድሜዬን በላጤነት እንዳልጨርሰው ነው። ...92
በርኒስ፦ እወደዋለሁ፥ እርሱ ግን ክርስቲያን አይደለም። ...93
ምሕረት፦ ክርስቲያን ያልሆነ እጮኛ ሊኖረኝ አይችልም? ...95
ማርታ፦ የልጆቼን አባት ላገባው ይገባኛልን? ...96
አንጄላ፦ «ጥቂት ቢራዎችን ወስጃለሁ» ይላል። ...97
አማንዳና ኤውንቄ በቤቱ መኖር ልጀምር ይሆን? ...99
ያዕቆብ፦ እጮኝነቱን አቋረጠ። ...101
ልድያ፦ ካገባሁ በኋላ ለሁለት ዓመት መውለድ አልፈልግም። ...102
ቋርስቅላ፦ ወሲባዊ የቪዲዮ ፊልሞችን ማየት ይሻለኝ ይሆን? ...103
ኢያሱ፦ ሚስቴ ከሌሎች ሰዎች ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት

ትፈጽም ነበር። ........ 104
ኑኃሚን፡- ደስ ስንሰኝ ልብሶቻችንን እናወልቃለን። ........ 106
አስቴር፡- ወላጆቼ በገንዘብ ጉዳይ ይጨቃጨቃሉ። ........ 107
ዮሐንስ፡- ለቤተ ክርስቲያን መስጠት ያለብኝ ገንዘብ ምን ያህል ነው? ........ 110
ማርያም፡-ሠርግ ባለብዙ ወጪ መሆን አለበትን? ........ 111
ካሌብ፡-እኔ ስሞት ሚስቴ ገንዘቤን መውረስ አለባት። ........ 112
መጋቢ፡- በቤተ ክርስቲያናችን «የቅድመ-ጋብቻ ትምህርት» ያስፈልጋል። ........ 114
ፊልሞና፡- በፍትወተ- ሥጋ ምክንያት ጨብጥ ይዞኛል። ........ 114
ብቸኛው፡- ቆንጆ ወጣት ሴቶች እንድጎበኛቸው ይጠይቁኛል። ........ 117
ግላዲስ፡- መውለድ መቻል አለመቻሌን ማረጋገጥ አለብኝ። ........ 118
ካረን፡- «ወንዶች፥ እንዴት ልጃገረድን ሊፈትኗት ይፈልጋሉ»
ብለው ነገሩኝ። ........ 119
እኔ፡- ለግብረ -ሥጋ ግንኙነት ቢጠይቀኝ፥ ምን ልመልስለት? ........ 121
ደስታ፡- 14 ዓመቴ ነው፥ እንዳላረግዝ ፈርቻለሁ። ........ 123
ሉይስ፡- አወላልቀን ነበር! አርግዤም ሊሆን ይችላል ........ 123
አቤሴሎም፡- ለእርሷ ያለኝ ፍቅር ጠንካራ መሆኑን ትጠራጠር ይሆንን? ........ 125
ቤትሪስ፡- ልጆቼን አይፈልጋቸውም። ........ 125
ጢሞቴዎስ፡- ከሌላ ሰው ወልዳለች። ........ 127
ግሎሪያ፡- ለምን አገባለሁ? ........ 127
ማርቆስ፡- በእግዚአብሔር እታመናለሁ! ታገባኛለች! ........ 128
አቤል፡- እርሷን በፍቅር ማሸነፍ አለብኝ፥ ያለበለዚያ ራሴን እገድላለሁ። ........ 130
ፊልጶስ፡- ከዝሙት ኃጢአት ርቄ መኖር እችላለሁ? ........ 131
የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ........ 132

## ምዕራፍ 1

# በእርግጥ ጋብቻ በፍቅር የተሞላ ሊሆን ይችላልን?

ጃክ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢቭን ያየበትን አጋጣሚ በፍጹም አይረሳውም።* እግር ኳስ በመጫወት ላይ እንዳለ ተመለከታትና ከእርሷ ጋር ለመነጋገር ሃፍረት ተሰማው፤ ምክንያቱም የቆሸሸውን የስፖርት ትጥቁን ገና እንደለበሰ ነበር። እርሷ በጣም ቆንጆ ሴት ነበረች. . . ቀድሞ ካያቸው ልጃገረዶች ሁሉ ትበልጣለች። ከአጠገቧ መቼውንም ቢሆን ላለመለየት ወደደ።

በመጀመሪያ ልትወደው ትችል እንደሆነ ተጠራጥሮ ነበር። ሳምንታት እያለፉ ሲሄዱ ግን፥ እርሷም ስለ እርሱ አስገራሚ የሆነ ስሜት እንዳላት በሚገባ መገንዘብ ጀመረ።

ጃክ ግልፍተኝነት አለችበት፤ ጓደኞቹም እንኳ ቢሆኑ እርሱ ሲናደድ ይፈራሉ። በኢቭ አጠገብ ሲሆን ግን ራሱን ረጋ ያለ ጨዋ ሰው ሆኖ ያገኘዋል።

ተጋቡና ጃክ ይሠራው በነበረበት ቢሮ አቅራቢያ ወደሚገኝ ውብ የመኖሪያ ቤት ተዛወሩ።

ሁለቱም በጣም ደስተኞች ነበሩ!

አንድ ቀን እጅ ለእጅ ተያይዘው በመጓዝ ላይ እንዳሉ «የእግር ጉዞአችን ጥሩ ነው፥ አይደለም እንዴ?» በማለት ኢቭ ወደ ጃክ ጆሮ አንሾካሾከች።

ጃክም እጁን ጭምቅ አደረገና መስማማቱን በፈገግታ ገለጸላት። ፍቅራቸው እንከን አልነበረውም።

ሆኖም ብዙም ሳይቆዩ መነታረክ ጀመሩ። ንትርኩ የጀመረው ጃክ በሚስቱ የባልትና ሙያ ደስ ባለመሰኘቱ ነበር። ከዚያ በኋላም የትኛው የቤት ዕቃ ይገዛ በማለት መጋጨታቸውን ቀጠሉ።

ሁለቱም ራስ ወዳዶችና እልኸኞች ነበሩ።

---

* ይህ እውነተኛ ታሪክ ነው፥ ነገር ግን ስሞቹ ተለውጠዋል።

ወራት እያለፉ ሲሄዱ ንትርካቸው እየተካረረ ሄዶ በጣም መጥፎ ደረጃ ላይ ደረሰ። በመጨረሻ ኢቭ ጃክን ጥላው ወደ ወላጆቿ ቤት ሄደች። ጃክም ወደ እርሱ እንድትመለስ ምንም ጥረት ሳያደርግ ቀረ፤ ይልቁንም ትርፍ ጊዜውን ሁሉ እግር ኳስ በመጫወት ያሳልፍ ጀመር።

አንድ ቀን ማርቆስ ከተባለ የእግር ኳስ አፍቃሪ ወጣት ጋር ተዋወቀና አብረው ወደ እርሱ የመኖሪያ ቤት አቀኑ።

ጃክ፥ ማርቆስ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንደሚወድ በማወቁ ተገርሟል፤ ሆኖም፥ ማርቆስን ወዶታልና ብዙም ሳይቆይ ስለ አሳዛኝ ጋብቻው አንድም ሳያስቀር ነገረው። ማርቆስም ጃክን፥ «እግዚአብሔር ሚስትህን እንድትወዳትና አብረሃትም እንድትኖር ይፈልጋል» አለው።

ጃክም፥ «ያንን ማለት ለእግዚአብሔር ቀላል ነው፤ ምክንያቱም ከእርሷ ጋር አብሮ መኖር ያለበት እርሱ አይደለምና» በማለት መለሰ። ማርቆስም ንግግሩን በመቀጠል፥ «አሁኑኑ ደውልላትና ወደ አንተ እንድትመለስ ጠይቃት» አለው።

«ቶሎ በል፥ አንተ ሰው አሁኑኑ ደውልላት» ሲል አጣደፈው ማርቆስ።

ጃክ ለኢቭ ደወለላት፤ በደረሰው ያልተጠበቀ ምላሽም ተደነቀ። «እሺ፥ ተመልሼ እመጣለሁ፤ ትዳራችንም የተሻለ ይሆናል» አለችው።

ኢቭ ተለውጣ መመለሷን ጃክ ወዲያውኑ ተገነዘበ። ኢቭም፥ «የእኔ ራስ ወዳድነት በትዳራችን ተከስተው የነበሩትን ብዙ ችግሮች እንዳስከተለ መረዳት ችያለሁ» አለችው።

ከዚያም፥ «ምን እንደሆነ እስክነግርህ ድረስ መታገስ አልቻልኩም፤ ውድ ወላጆቼ ቤት በተመለስኩበት ዕለት ወላጆቼ እንዲህ ብለው ነገሩኝ፤ «እንደ በፊቱ ቤተ ክርስቲያን ሳሚዎች አይደለንም፥ እውነተኛ ክርስቲያኖችም ሆነናል»። ከዚያም ወደ አዲሱ መጋቢያቸው ወሰዱኝ፤ እርሳቸውም በጣም ጥሩ ሽማግሌ ሰው ነበሩ። ከእርሳቸውም ኢየሱስ የተሠቃየው እኔ ለሠራኋቸው ኃጢአቶች መሆኑን ተረዳሁ። በኢየሱስም ለማመን ወሰንኩ። አሁን የዘላለም ሕይወትን አግኝቻለሁ፤ እግዚአብሔርም እየለወጠኝ ነው»።

ከዚያ በኋላ፥ ጥያቄአዊ አስተያየቱን ከፊቱ ላይ አንብባ ጃክን፥ «የነገርኩህ ነገር አሁኑኑ ይገባሃል ብዬ አልጠብቅም» አለችው።

ጃክ ጽናት በተሞላው አቋሟ ተነክቷል፤ ተመልሳ በመምጣቷ ተደስቷል። ስለ ኢየሱስ መነጋገሩን ግን አልወደደውም። ለራሱም፥ «ኢየሱስ ለእኔ አያስፈልገኝም» ብሎ ተናገረ።

በተከታዮቹ ሳምንታት፥ ጃክ ኢቭ ከፊት ይልቅ ደስተኛ ሰው እንደሆነች፤ ለእርሱም ሁልጊዜ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን ታደርግለት እንደነበረ አስተዋለ።

ከዚህ በኋላ በአንድ የእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ማርቆስና ጃክ በአጋጣሚ ተገናኙ። ጃክም ማርቆስን፥ «ሚስቴ አዲስ ሰው ሆናለች፥ ኢየሱስን መቀበሏን ትናገራለች፤ መለወጧ ግን በእርግጥ ከእርሱ የተነሣ መሆኑን እጠራጠራለሁ» አለው።

ማርቆስም ሣቅ አለና፥ «እርግጠኛ ነኝ ምክንያቱ እርሱ ነው፤ ኢየሱስ አንተንም እኮ ሊለውጥህ ይችላል» አለው።

ጃክም፥ «እኔ? እኔ መለወጥ ለምን ያስፈልገኛል? የትዳራችን ችግሩ የእርሷ ራስ ወዳድነት እንደነበር ኢቭ ታምናለች፤ በአሁኑ ወቅት እርሷ ተለውጣለች፤ እኛም ደስተኞች ነን» አለው።

ማርቆስም፥ «በእርግጥ ደስተኛ ነህን?» በማለት አጥብቆ ጃክን ጠየቀው።

ጃክ ግን አልመለሰለትም፤ በውስጥ ልቡ፥ መለወጥ የሚገባት ኢቭ ብቻ አለመሆኗን ተረድቶ ነበርና።

በማግሥቱ ጧት ጃክ ልብሶቹን በመለባበስ ላይ እያለ በድንገት ሸሚዙን ቀደደው። ወዲያውኑ በጣም ከመናደዱ የተነሣ ሸሚዙን በወለሉ ላይ ጥሎ መራገም ጀመረ። የሆነውን ነገር ለማየት ኢቭ በሩጫ ወደ ክፍሉ ገባች። በዚያም ቆማ፥ ባሏ ሸሚዙን ሲራገም ተመለከተችው።

በመጨረሻ ጃክ በራሱ አፍሮ በአልጋው ላይ ተቀመጠ። «ኢቭ፥ አንዳንድ ጊዜ፥ ችግሬ ምን እንደሆነ አይገባኝም፥ ያለ ምክንያት እበሳጫለሁ። እንደ እኔ ካለ ሰው ጋር እንዴት መኖር ትችያለሽ?» አላት።

ኢቭም አጠገቡ ተቀመጠችና፥ «አንተ እኮ ባሌ ነህ እኔም እወድሃለሁ» በማለት በጆሮው ሹክ አለችው።

ጃክም ኀዘን በተሞላ አነጋገር፥ «እንዴት እንደምታደርጊው አላውቅም» አላት።

ኢቭም ራሷን በትከሻው ላይ ደገፍ አደረገች፤ እንዲህም ትለው ጀመር፥ «አንተን ባገባሁህ ጊዜ ስለ ራሴ ብቻ አስብ ነበር እንጂ አንተን ደስ ለማሰኘት የምችልባቸውን ዘዴዎች አስቤ አላውቅም፤ እንድታስደስተኝ ብቻ እወድ ነበር። አሁን ግን ብዙም ራስ ወዳድ እንዳልሆን ኢየሱስ እየረዳኝ ነው፤ በውድቀቴም ሁሉ እርሱ ይቅር ይለኛል። ኢየሱስ ሲሞት ስለ እኔ ኃጢአት ይሠቃይ ነበር። ዘላለማዊ ሕይወትን ሊሰጠኝ የሚችለውም ለዚህ ነው። እንግዲህ አንተም ብትቀበለው. . .»

የወዳጅነት ንግግሯ የስብከት ዝንባሌ እያያዘ እንደመጣ ስለተገነዘበች ወዲያውኑ ንግግሯን አቋረጠች፤ ለረጅም ጊዜም በክፍሉ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ። ጃክ በእጆቹ ራሱን ይዞ ወለሉን እየተመለከተ ተቀምጧል።

በመጨረሻ ሲናገር፥ ድምፁ የረጋና ጥልቅ ነበር፤ «ኢቭ፥ እንዴት ኢየሱስን ለማግኘት እችላለሁ?» ኢቭም በጉጉት፥ «እዚሁ ነዋ. . . በዚህ ክፍል ውስጥ!» አለችው።

በዚያን ጊዜ ጃክ በመኝታ ክፍሉ ውስጥ ከኢየሱስ ጋር ለመነጋገር እንደሚችል ተረዳ፥ እንዲህም ይል ጀመር፤ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ እባክህን ይቅር በለኝና ወደ ሕይወቴ ግባ. . . ወደ ኢቭ ሕይወት እንደገባህ»።

በአሁኑ ወቅት ጃክ እንዲህ ይላል፥ «ኢየሱስ ጸሎቴን እንደሰማ አውቃለሁ፤ ከዚያን ቀን ጀምሮ በእኔም ሆነ በኢቭ ሕይወት በመሥራት ላይ ነው።»

ጃክ አሁንም ኳስ መጫወትን ይወዳል፤ ቢሆንም ከኢቭ ጋር አብሮ በመሆን የሚያሳልፋቸው ብዙ ጊዜያት አሉት። ይህም የሆነው ኢቭ ስላስገደደችው ሳይሆን ከእርሷ ጋር አብሮ መሆን ስለሚያስደስተው ነው።

ብዙ ጊዜ እርስ በርሳቸው እንዲህ በማለት ይንሾካሾካሉ፥ «ጥሩ ነው፥ አይደለ እንዴ?» አዎ፥ እግዚአብሔር ጋብቻን ያቀደው ጥሩ እንዲሆን ነው።

## የእግዚአብሔር መልካም ዕቅድ ለጋብቻ

እንስሳት መባዛት ይችሉ ዘንድ ተቃራኒ ፆታ አላቸው፤

ሰዎች ግን የተለዩ ናቸው። ሰዎች በሚጋቡ ጊዜ፥ ፍትወተ ሥጋ አጋሮች ብቻ ከመሆን ያለፈ የቅርብ ወዳጅነት ሊመሠርቱ ይችላሉ።

አዎ፥ ባልና ሚስት የቅርብ ወዳጆች ይሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ሚስት የምትወልድ ብቻ አይደለችም፥ የባሏ የቅርብ ወዳጅም ጭምር እንጂ።

የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚለውም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ፥ «መልካም ነው» ብሏል፤ የመጀመሪያውን ሰው ከፈጠረ በኋላ ግን ያለው፥ «መልካም አይደለም፤» ነበር አዎን፥ ዘፍጥረት 2፡18 እንዲህ ይላል።

እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ «. . . መልካም አይደለም»። «መልካም አይደለም የተባለው ምንድን ነው?» ብለን በጥንቃቄ ማሰብ አለብን።

በዚያን ጊዜ በምድር ላይ አብዛኛው ነገር መልካም ነበር፤ ኃጢአትም አልነበረም። እግዚአብሔር የሰው ወዳጅ፥ ሰውም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር። መልካም ያልሆነ አንድ ነገር ግን ነበር። እስኪ ዘፍጥረት 2፡18ን እንደገና እንመልከት።

እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፥ ________________________ »

ምንም እንኳ እግዚአብሔር እርሱ ጋር ቢሆንም ሰው ግን «ብቻውን!» ነበር። ሰው ወዳጅ ያስፈልገው ነበር፤ በዚህ ምክንያት ነው ሴትን የፈጠራት።

እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፦ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፥ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» (ዘፍጥረት 2፡18)።




ስለሆነም ሰው ብቸኝነት በነበረበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ለችግሩ መፍትሔን ሲሰጠው እንመለከታለን። እግዚአብሔር ለሰው ትክክለኛ የሆነች አጋር ረዳትና ወዳጅን አዘጋጀለት፤ ጋብቻ ማለትም ያ ነው!




እግዚአብሔር፥ «ሁሉም ሰው ማግባት አለበት» ብሎ አልተናገረም። በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው አንዳንድ ሰዎች ሳያገቡ ቢኖሩ ደስተኞች ሊሆኑና እግዚአብሔርንም አብዝተው ሊያገለግሉት እንደሚችሉ ነው። (1ኛ ቆሮ. 7:32–35)።

ሆኖም፥ ለማግባት የሚመርጥ ሁሉ እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ የሚናገረውን መረዳት ይኖርበታል። በሚቀጥለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፥ እግዚአብሔር ጋብቻ ምን እንደሆነ በትክክል ይነግረናል።

## የእግዚአብሔር የጋብቻ ዕቅድ

**«ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ»** (ዘፍጥረት 2:24)።

ይህ ጥቅስ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አራት ጊዜ ተደጋግሞ እናገኘዋለን፡– ዘፍ. 2:24፤ ማቴ. 19:5፤ 1ኛ ቆሮ. 6:16፤ ኤፌ. 5:31።

«ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል» የሚለውን የጥቅሱን ክፍል በመመልከት እንጀምር።

«ይጣበቃል» የሚለው ቃል ትርጉሙ፥ «አንድ ይሆናል» ማለት ነው።

እግዚአብሔር እያንዳንዱ ባል፥ «እኔና ሚስቴ አንድ ነን። እርሷ የቅርብ ወዳጄ ናት። ለእርስዋ የውስጥ ስሜቶቼን፥ ተስፋዎቼንና ፍርሃቶቼን እንኳ ሳይቀር ልነግራት እችላለሁ» የሚል ዝንባሌ እንዲኖረው ይፈልጋል።

## ለሚስቴ መንገር ይገባኛልን?

ባለፈው ዓመት አንድ የተልዕኮ ትምህርት ቤት 300 ገጽ ያለው ትምህርት አዘጋጅቼ በጽሑፍ እንዳቀርብ ጠየቀኝ። እኔም ዘግይቼ እየተኛሁ በማለዳም እየተነሣሁ በትጋት ሠራሁት። በመጨረሻም አጠናቀቅሁና ላክሁላቸው። እንዲህ የሚል ምላሽም ደረሰኝ፡—

> ውድ ሚስተር ብሪትን፥
>
> ያዘጋጀኸው ትምህርት የእኛን መስፈርት ያላሟላ በመሆኑ እናዝናለን። እባክህን ኀዘን አይሰማህ። ብዙ ጎበዝ መምህራንም አጥጋቢ ትምህርቶችን በጽሑፍ ማቅረብ አይሳካላቸውም።

በእርግጥ ኀዘን ተሰማኝ፥ በጣም ከባድ ኀዘን! የሌሎችን ያህል ተሰጥዖ እንደሌለኝ በማሰብ ሁሌም እፈራ ነበር። በልጅነቴም እንኳ ብዙ ጊዜ፥ «ሌሎች ሕፃናት ሁሉንም ነገር ከእኔ በተሻለ አኳኋን መሥራት ይችላሉ» እያልኩ አስብ ነበር።

ደብዳቤውን ደጋግሜ በማንበብ ላይ እያለሁ፥ ራሴን እንዲህ ብዬ ጠየቅሁት፥ «ይህን ደብዳቤ ለሚስቴ ማሳየት ይገባኛልን? ምን እንደተሰማኝስ ልንገራት ይሆንን? ስለ እኔ ዝቅተኛ ግምት እንዲኖራት አልፈልግም። በምድር ላይ ካሉት ሁሉ ታላቅ ሰው እኔ እንደሆንኩ እንድታስብ እንጂ!»

ሆኖም እግዚአብሔር ሰው፥ «ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል» ስለሚል ደብዳቤውን ለካሮል አሳየኋት፤ ምን ያህል ኀዘን እንደተሰማኝም ነገርኳት።

ናቀችኝን? አይደለም፥ አበረታታችኝ፤ በእርሷ የማበረታቻ ድጋፍ፥ ትምህርቱን እንደገና በመጽሐፍ መልክ አዘጋጀሁት። በአሁኑ ጊዜ በብዙ መምህራን ዘንድ ታዋቂ ነው።



አንዳንድ ሰዎች ለራሳቸው፡ «ባል ከሚስቱ ጋር መጨዋወቱ ከወንድ የሚጠበቅ አይደለም» ይሉታል፡ ስለዚህ ከሌሎች ወንዶች ጋር ያወራሉ። ሚስቶቻቸውን የሚያናግሩት አልፎ አልፎ ነው። ውስጣዊ ደስታና ኀዘናቸውን ግን ከማንም ጋር አይጨዋወቱም።

እንደዚያ ያለ ሰው በፍጹም ደስተኛ አይደለም፤ ሚስቱም ሆነ እርሱ በውስጣቸው ብቸኝነት ይሰማቸዋል። በጣም ብዙ ጋብቻዎች የዚህ ዓይነት መሆናቸው አሳዛኝ ነው።

ጋብቻ ግን እንደዚያ ሊሆን አይገባውም። የቅርብ ወዳጆች ለመሆን በመምረጣቸው ምክንያት ይሰማቸዋል። በጣም ብዙ ጋብቻዎች የዚህ ዓይነት መሆናቸው አሳዛኝ ነው።



ጋብቻ ግን እንደዚያ ሊሆን አይገባውም። የቅርብ ወዳጆች ለመሆን በመምረጣቸው ምክንያት በትዳራቸው ጥልቅ ደስታ ያላቸው ባልና ሚስቶች በእያንዳንዱ አህጉር ይገኛሉ።

## ከአሜሪካ፥ አፍሪካ ወይስ እስያ?

በቅርቡ ከተለያዩ አገሮች ከመጡ ወዳጆቼ ጋር በአንድ መኪና እንጓዝ ነበር። ከወዳጆቼም አንዱ፤ «ብሩስ፤ ካገባህ ረጅም ጊዜ ሆኖሃል፤ እስኪ ንገረን. . . ባልና ሚስት እንዴት በትዳራቸው ደስ ሊሰኙ ይችላሉ?» አለኝ።

እኔም፤ «ትዳርን በእውነት አስደሳች ለማድረግ፤ ባልና ሚስት የቅርብ ወዳጆች መሆን አለባቸው። እንዲያውም የቅርብ ወዳጆች ካላቸው ቅርበት ይልቅ እርስ በርሳቸው መቀራረብ ይገባቸዋል» በማለት መለስኩለት።

ከዚያም፤ «ይህን አሳብ ከየት ስፍራ ያገኘሁት ይመስላችኋል? ከእስያ አፍሪካ፥ አሜሪካ ወይስ ከሌላ?» ብዬ ጠየቅኋቸው። በመኪናው ውስጥ የነበሩ አፍሪካውያን ወጣቶችም፥ «ከአፍሪካ አይደለም፥ እኛ አፍሪካውያን ሚስቶቻችንን እንወዳለን፥ የባል የቅርብ ወዳጅ ግን ሚስቱ መሆን አለባት አንልም፤ ይህን አሳብ ያገኘኸው ምናልባት ከአሜሪካ ሊሆን ይችላል» በማለት መለሱ።

አሜሪካውያኑም፥ «ትክክል አይደለም፥ ይህ የአሜሪካውያን አሳብ አይደለም። በርካታ አሜሪካውያን ባልና ሚስቶች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ አብዛኛውን ጊዜአቸውን ሥራ በመሥራት ያሳልፋሉ፤ እርስ

በርሳቸው ፍቅርን ለመጨዋወት ይቅርና ለመነጋገር እንኳ ያላቸው ጊዜ በጣም ጥቂት ነው» በማለት መለሱ።

እውነት ነው፥ ባልና ሚስት የቅርብ ወዳጆች መሆን አለባቸው የሚለው አሳብ የመጣው ከአፍሪካ፥ አሜሪካ፥ እስያ ወይም በዓለማችን ካለ ሌላ ስፍራ አይደለም፤ ይህ አሳብ የመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

እግዚአብሔር ባልና ሚስት «ይጣበቃሉ» ሲል፥ የቅርብ ወዳጆች ናቸው፤ በደስታ. . . ፥ ይነጋገራሉ፥ ይሳሳቃሉ፥ ይዋደዳሉ፥ አብረውም ያመልካሉ ማለቱ ነው።

ጋብቻ ወዳጅነት ነው፥

ተራ ወዳጅነት ግን አይደለም፥

እጅግ በጣም ትልቅ የሰዎች ወዳጅነት እንጂ።

## ከማንም ይልቅ የእርስ በርስ መቀራረብ

ባልና ሚስት ከማንኛውም ሌላ ሰው ጋር ካላቸው ቅርርብ ይልቅ እርስ በርሳቸው መቀራረብ ይገባቸዋል። ባል ከወላጆቹ፥ ዘመዶቹ ወይም ወዳጆቹ ይልቅ ለሚስቱ ቀረቤታ ሊኖረው ይገባል። ሚስትም ከወላጆቿ ወይም ልጆቿ ይልቅ ከባሏ ጋር መጣበቅ ይኖርባታል።

አንዳንድ ባሎች፥ «ሚስቴ ከእኔ ይልቅ ለልጆቻችን እንክብካቤ ታደርጋለች» ብለው ይነግሩናል።

በእርግጥ፥ እናቶች ልጆቻቸውን መውደድ ይገባቸዋል. ነገር ግን የሚስት አብላጫ ፍቅር ለባሏ ሊሆን ይገባል።

«እናቴ አባቴን ትወደዋለች፥

አባቴም እናቴን ይወዳታል»

ለማለት የሚችል ሕፃን ዕድለኛ ነው።

እንደ ክርስቲያን አባት፥ ልጆቼን እወዳቸዋለሁ፤ ስለ ችግሮቻቸው እነግራቸዋለሁ. . . አብሬአቸው እጸልያለሁ፥. . . አብሬአቸውም እጫወታለሁ፤ ለልጆቼ የማደርግላቸው የተሻለ ነገር ግን ሚስቴን መውደዴ ነው!




## የእግዚአብሔር ዕቅድ

የእግዚአብሔር ዕቅድ በጣም ጥሩ ነው፤ አሳዛኙ እውነታ ግን፥ ብዙ ሰዎች ሊከተሉት ያለመምረጣቸው ነው። ከዚያ ይልቅ የዓለምን ዕቅድ ይከተላሉ።

## የዓለም ዕቅድ

በዓለም ዕቅድ መሠረት፥ ባል ከቅርብ ዘመዶቹ ወይም አብረውት ከሚሠሩ ሰዎች ጋር በመቀራረብ እርካታን ለማግኘት ጥረት ያደርጋል። (የገጽ 11 የላይኛውን ክፍል ተመልከት።) ሚስትም ከቅርብ ዘመዶቿና ወዳጆቿ ጋር በጣም ለመቀራረብ ጥረት ታደርጋለች። ውጤቱ፥ የባልም ሆነ የሚስት ይልቁንም የልጆች ዋስትና ማጣት ነው።




የዓለም ዕቅድ

## የትኛውን ዕቅድ እንደምትከተል ምረጥ

አንዳንድ ፍላጎቶች አሉን። አንድ የሚቀርበን ሰው እንሻለን። የሚያደምጠን፥ ነገራችን የሚገባውና የሚጠነቀቅልን ወዳጅ ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር የሚያስፈልጉንን ነገሮች ያውቃል። እርሱ፥ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፥ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት. . . ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል. . .» ብሏል።

ዛሬ በመላው ዓለም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች
በአስደንጋጭ ሁኔታ
ደስታ አልባ በሆኑ
ቤቶች ይኖራሉ። አንተ ግን
በደስታና በፍቅር የተሞላ ቤት
ሊኖርህ ይችላል። የትም ተወለድ
በአሜሪካ፥ አፍሪካ፥ እስያ ወይም በሌላ
ስፍራ ሊሆን ይችላል። ማንኛውንም ዓይነት
የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚቃወሙ ልማዶችን
ለመተውና አስደናቂውን የፈጣሪህን ዕቅድ
ለመከተል መምረጥ ትችላለህ።

ለዚህ ዓለም ልምዶች ጀርባቸውን በመስጠት የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለመከተል ይችሉ ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ በቂ እምነት ያላቸው ሰዎች ብዙዓን ናቸው።




የዓለም ዕቅድ

የእግዚአብሔር ዕቅድ



## ምዕራፍ 2

# የተሻለው የጋብቻ ዓይነት የቱ ነው?




ራስ ወዳድ- ባል ያለበት የጋብቻ ዓይነት

ብዙ ወንዶች «ራስ ወዳድ ባል» ያለበትን የጋብቻ ዓይነት ይፈልጋሉ። ይሁን እንጂ እውነታው፥ እንደዚያ ያለው ጋብቻ ለወንዱም እንኳ ብዙ ደስታን የማያመጣ መሆኑ ነው። ለምን? ምክንያቱም ራስ ወዳድ ባል ባለበት ጋብቻ፥ ሚስት ለባልዋ ምግብን ታበስላለች እንጂ እርሱ የሚወዳቸውን ምግቦች ለማዘጋጀት ጥንቃቄ አታደርግም።

ከእርሷ ጋር ፍትወተ- ሥጋ እንዲፈጽም ትፈቅድለታለች እንጂ በጣም የሚያስደስተው እንዲሆን ግን ጥረት አታደርግም። «ባሌን እንደማከብረው ማስመሰል አለብኝ፥ በልቤ ግን አላከብረውም። እርሱ ራሱን ወዳድ- ሰው ነው። እኔንም አይወደኝም፤ እኔስ እርሱን ለምን እወደዋለሁ?» የሚል አስተሳሰብ አላት።

### ሁለት ራስ-ወዳዶች

በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሴቶች፥ «ራስ ወዳድ ባል ያለበት ጋብቻ ይወገድ! እኛ ሴቶች መብቶቻችንን ማስታወስ አለብን!» ይላሉ።

ይህም የሚያመራው፥




የሁለት ራስ ወዳዶች የጋብቻ ዓይነት

በሁለት ራስ ወዳዶች ጋብቻ፥ ባልም ሆነ ሚስት ባለሥልጣን ለመሆን ይፈልጋሉ። ስለዚህም ጋብቻቸው የየዕለት ፉክክር ይሆናል፤ ወዳጆች ሳይሆኑ፥ ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የመጡና . . . ለመሸናነፍ የሚጥሩ ሁለት ሯጮችን ይመስላሉ።

በዚህ ዓይነት ጋብቻ፥ አብዛኛውን ጊዜ ባልየው፥ «ከዚህች የከተማ ሴት ይልቅ አንዲት የገጠር ወጣት ማግባት ነበረብኝ» በማለት ለራሱ ይናገራል።

ቢሆንም፥ ደስታ ለሞላበት ጋብቻ እውነተኛው ቁልፍ የእግዚአብሔርን ዕቅድ መከተል ነው።

አዎ፥ የእግዚአብሔር ዕቅድ ይሠራል።

በከተሞች እንዲሁም በገጠር፥ በእያንዳንዱ አገርና ባህልም ይሠራል።

## የእግዚአብሔር የጋብቻ ዕቅድ

የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለመከተል፥ ባል ሚስቱን እንደ አጋሩና ወዳጁ መቀበልን ይመርጣል።

እርሷም ባሏን ለማክበር ትመርጣለች።

ራስ ወዳድ ከመሆን ይልቅ ለእርስ በርሳቸው አካላዊ፥ መንፈሳዊ፥ ፍትወታዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች ማሰብን ይመርጣሉ።




## የእግዚአብሔር የጋብቻ ዕቅድ

በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ዙሪያ፥ የተለያዩ አገሮች ባልና ሚስት እንዴት መኖር እንደሚገባቸው የሚገልጹ ልዩ ልማዶችና ደንቦች አሏቸው። ይሁን እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት፥ ፈጣሪያችን በትክክል ምን ማድረግ እንዳለብን ሲነግረን እናገኘዋለን። እንዲህ ይላል፦

| ባሎችን የሚመለከቱ ጥቅሶች | ሚስቶችን የሚመለከቱ ጥቅሶች |
| --- | --- |
| እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፥ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል. . . (1ኛ ጴጥ. 3:7)። | ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ። |
| ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት (ኤፌ. 5:33)። | ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና። |
| ባሎች ሆይ፦ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ (ኤፌ. 5:25)። | ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ (ኤፌ. 5:22–24)። |
| | አሮጊቶች ሴቶች. . . ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ይምከሩአቸው (ቲቶ 2:3–4)። |

እነዚህን ጥቅሶች የሚታዘዙ ባልና ሚስት የሚገኙበት ቤት ደስታ የሞላበት ነው! እንዲህ ባለው ቤት ሚስት፥ «ባሌ የእኔ ራስ ነው» ማለትን በሚገባ ስታውቅ፤ ባልም፥ «ሚስቴ የእኔ አጋር ናት» ማለትን በሚገባ ያውቃል።

ከላይ የተገለጹት ጥቅሶች ስለ ጸሎት የሚናገሩትን ልብ በል። ባል ሚስቱን በአግባቡ ካልያዛት፥ ጸሎቶቹ ኃይል የለሽ ይሆናሉ ወይም ይከለከላሉ።

ስለዚህ ባል፥ «የቤተሰብ ራስ እኔ ስለሆንኩ ባለቤቴን እንደፈለግሁ አደርጋታለሁ፥» የሚል አስተሳሰብ በፍጹም ሊኖረው አይገባም። ይልቁንም፥ «ስለ ፍላጎቶቿ ማሰብ» እና «በጉልበት ደካማ» በመሆኗም በቤት ውስጥ ያለውን ሥራ ማገዝ ይኖርበታል።

ዮሴፍና እና ልድያ ልጆቻቸው በየትኛው ትምህርት ቤት መማር እንዳለባቸው በተከራከሩ ጊዜ፥ ዮሴፍ የሚስቱን ምርጫ ለመቀበል ተስማማ። ሚስቱን የሚወድ ባል ብዙ ጊዜ እንዲህ ያደርጋል።

ሌላ ጊዜ ደግሞ፥ ዮሴፍ አንድ መኪና ለመግዛት ወሰነ። ልድያ ግን መኪናው አሮጌና አስቀያሚ እንደሆነ ብታስብም ባለቤቷን ለማክበርና ውሳኔውንም ለመቀበል ተጠነቀቀች። መኪናዋ ጥገና ባስፈለጋት ጊዜ ሁሉ፥ «እንደዚህ እንደምትሆን ነግሬህ ነበር» ብላ ከመናገርም ተቆጠበች።

ብዙ ጊዜ ባሎች፥ «ሚስትህን ውደድ ማለት ምንድን ነው?» በማለት ይጠይቃሉ። ለዚህ የእግዚአብሔር መልስ እንዲህ ነው።

ፍቅር ማለት፦

- ለሚስትህ ቸርነትን ማድረግና ታጋሽ መሆን ነው።
- የራስን ፈቃድ የሙጥኝ አለማለት ነው።
- ትሑት መሆንና ራስን መስጠት ነው።
- በቀላሉ አለመበሳጨት ነው (1ኛ ቆሮ. 13፡4-8)።

ባል ሚስቱን ቸርነት፥ ትሕትናና ትዕግሥት በታከለበት ፍቅር ለመውደድ፥ ሚስትም ባሏን ለማክበር በተጠነቀቁ ጊዜ ጋብቻ መልካም ይሆናል።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ታላቅ ነው! ክርስቲያኖች ግን እየተከተሉት ነውን? ክርስቲያኖች የጋብቻቸውን ዓይነት እንዴት ነው የሚወስኑት? መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በመመልከት ወይም የአካባቢያቸውን ልማዶች በማየት?



ቢያሳዝንም እንዲህ ማለት አለብን፥ ብዙ ክርስቲያኖች የባህላቸውን ልማዶች ይኮርጃሉ። ከዚያም ራሳቸውን ራስ ወዳድ ባል ባለበት ወይም በሁለት ራስ ወዳዶች ጋብቻ መካከል በማግኘታቸው ይበሳጫሉ።



ያም ሆኖ፦ በአፍሪካ፥ እስያም ሆነ ሌላ ስፍራ፥ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሚመርጡ ጥቂት ባልና ሚስቶች ይገኛሉ። *እነዚህ እንዴት ያለ በወዳጅነትና በፍቅር የተሞላ ታላቅ ደስታን በጋብቻቸው ያገኙ ናቸው!*



ምዕራፍ 3

# ወላጆቼን መተው አለብኝን?

> ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤
> በሚስቱም ይጣበቃል፤
> ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ (ዘፍጥረት 2:24)።

በምዕራፍ አንድና ሁለት ሰው «በሚስቱም ይጣበቃል» የሚለውን የዚህን ጥቅስ ክፍል ተመልክተናል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል» የሚለውን ክፍል እናያለን።

ወላጆችን መተው አስቸጋሪ ነገር ነው! ታዲያ ለምን እናደርገዋለን? ምክንያቱም እግዚአብሔር፥ ሰው ከሚስቱ ጋር መጣበቅ ይችል ዘንድ ወላጆቹን ይተዋል ብሎአል።

ወላጆቹን «መተው» ስንል ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል።

2. «መተው» አስቀድሞ *እርስ በርስ በጉዳዩ ላይ መወያየት* ማለት ነው።

በአንድ ምሽት ስምዖን ለባለቤቱ፥ «ዛሬ ስታንዳርድ የተሰኘው ባንክ ሥራ ሰጠኝ። የማስተማር ሥራዬን በጣም እንደምወድድ ታውቂያለሽ፥ ግን ባንኩ የተሻለ ደመወዝ ይከፍለኛል፥ ምን ይመስልሻል?» አላት።

እርሷም፥ «በመምህርነትህ፥ ተማሪዎችህን ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ለመርዳት በርካታ ምቹ ጊዜያት አሉህ፤ ስለዚህ ማስተማሩን መቀጠል ያለብህ ይመስለኛል። ከባንኩ የምታገኘው ተጨማሪ ገንዘብ ያን ያህል አስፈላጊ አይደለም» በማለት መለሰችለት።

ስምዖንም፥ ከልቡ በመነጨ አነጋገር «አመለካከትሽን ወድጄዋለሁ፥ አንቺ ከገንዘብ ይልቅ አብልጠሽ የምትፈልጊው ክርስቶስን ነው» አላት።

በኋላም ስምዖን ለአባትና እናቱ ስላገኘው ሥራ ነገራቸው። አባቱም ጥልቅ በሆነ ስሜት፥ «ልጄ ሆይ፥ በየወሩ ስለምታደርግልን የገንዘብ

ርዳታ ምን ያህል እንደምናመሰግንህ አንተ አታውቅም፤ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ብለህ ሥራ አትቀያይር» አሉት።

ስምዖን በዚህ ጉዳይ ላይ በቅድሚያ ከሚስቱ ጋር መነጋገሩ መልካም ነው። ይህም የሚያሳየው ወላጆቹን እንደተወና ከሚስቱ ጋር እንደተጣበቀ ነው።

## 2. «መተው»፥ *ሚስትህ ከማንም የቀረበች ዘመድህ ናት* ማለት ነው።

አንድ ወንድ ሲያገባ፥ የቅርብ ዘመዱ ሚስቱ ትሆናለች። እርሱም ከሚስቱ ጋር አንድ መሆን ይችል ዘንድ ወላጆቹን ይተዋል። እርሱና ሚስቱ አንድ በመሆናቸው፥ ባል በሚሞት ጊዜ፥ ገንዘቡና ንብረቱ ሁሉ ለሚስቱ (ለመበለቲቱ) መቅረት ይኖርበታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ አቤሜሌክ ከሞተ በኋላ ንብረቱ ሚስቱ ከነበረችው ከኑኃሚን ጋር ቀርቷል። በኋላም የቀድሞ ባሏ ወንድም ለነበረው ሰው ለሽያጭ አቀረበችለት (ሩት 4፡3)።

ይህ የሚያሳየው የባል እርግጠኛ የቅርብ ዘመዱ ሚስቱ እንደሆነች ነው፤ ለእርሱ ከወንድሙ ይልቅ እንኳ ሚስቱ ትቀርበዋለች።

ስለዚህ በምድራችን ላይ ካሉ ቁርኝቶች ሁሉ ጠንካራው የባልና ሚስት ነው። ይህ ቁርኝት ከሥጋ ዝምድናም ይልቅ የበለጠ ጠንካራ ነው (ማቴ. 19፡4–6)።

በመሆኑም እያንዳንዱ ባል፥ «ወላጆቼን፥ ወንድሞቼንና የሥጋ ዘመዶቼን እወዳለሁ፥ ነገር ግን በጣም የቅርብ ዘመዴ ሚስቴ ናት፤ እኔና ሚስቴ አንድ ነን። ስሞትም፥ ንብረታችንን ሁሉ ትወርሳለች» የሚል አስተሳሰብ ሊኖረው ይገባል። (ገጽ 113 ተመልከት)።

## 3. «መተው»፥ *የራስህ ቤት ይኑርህ* ማለት ነው።

በእርግጥ፥ «መተው» ባል የወላጆቹን ቤት ይተዋል ማለትም ነው፤ ከዚያም፥ እርሱና ሚስቱ የራሳቸውን ቤት ይሠራሉ። ባል ለምን የወላጆቹን ቤት ይተዋል? ከሚስቱ ጋር ይጣበቅ ዘንድ ነው (ዘፍ. 2፡24)።

ይህ ግን ወጣቶች ባገቡ ጊዜ ወላጆቻቸውን መውደድና መርዳትን ማቆም ይኖርባቸዋል ማለት ነውን? አይደለም!

መጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ለወላጆቻቸው እንክብካቤ እንዲያደርጉ ያዛል።

ማንም ባልቴት ግን ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሩአት፥ እነርሱ አስቀድመው ለገዛ ቤተ ሰዎቻቸው እግዚአብሔርን መምሰል ያሳዩ ዘንድ፥ ለወላጆቻቸውም ብድርን ይመልሱላቸው ዘንድ ይማሩ. . . ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው (1ኛ ጢሞቴዎስ 5:4 እና 8)።

በዚህ ምክንያት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ወላጆቻችንን *እንድንታው* ከነገረን በኋላ *እንድንንከባከባቸውም* ያሳስበናል።

*ታዲያ* ይህ እንዴት ሊፈጸም ይችላል? አንድ ወንድ ወላጆቹን *ትቶ*... በሚስቱም ተጣብቆ... እንዴት ለወላጆቹ *እንክብካቤ* ማድረግ ይችላል?

▪

ካሌብ ሚስቱን፥ «እናቴ አሮጊት ነች፤ ለብቻዋም ስለምትኖር፥ አንድ ነገር እስከናደርግላት ድረስ እባክሽን ሂጂና ለጥቂት ሳምንታት ከእርሷ ጋር ቆዩ» አላት።

ሚስትም ሄደች፥ ከአንድ ሳምንት በኋላ ግን እናቱና ሚስቱ መስማማት እንዳልቻሉ ሰማ። እናቱም፥ «እርሷ *ሥራ* አትወድም» ማለትን ያዘወትሩ ነበር።

ካሌብ ሚስቱን መልሶ እስኪወስዳት ድረስ ንትርኩ እየተባባሰ በመሄድ ላይ ነበር። በኋላም *ታናሽ* ወንድሙ፥ «አሁን *ታዲያ* እናታችንን ማን ይንከባከባታል?» በማለት መማረሩን ገለጸለት።

ካሌብ ምን ማድረግ እንደነበረበት አላወቀም። በኋላ ግን፥ አንድ ቀን ቤን ከተባለው ጥሩ ወዳጁ ጋር ተቀምጦ በመነጋገር ላይ ሳለ፥ መልሱ ተገኘ።

«ወንድሜ እየወቀሰኝ ነው፥ *ያንንም* የጀመረው ሚስቴን ከወላጆቼ ቤት በመውሰድ ስሕተት በመፈጸሜ ነበር» በማለት ካሌብ ለቤን ነገረው።

ቤንም በእርግጠኝነት፥ «*ያ* እኮ *ታዲያ* ስሕተት አልነበረም። በእርግጥ ሚስትህን ከእናትህ ጋር እንድትኖር ወደዚያ መላክ አልነበረብህም። ለምን? ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ፥ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል» ይላል አለው።

«*ታዲያ* እናቴን እንዴት ልረዳት ኖሮአል?» በማለት ካሌብ አሳቡን ተቃወመ።

ቤንም «እርግጠኛ ነኝ በርካታ ዘዴዎችን ማሰብ ትችላለህ። ለምሳሌ አንተና ሚስትህ አብራችሁ ምግባቸውን በማቅረብ. . . ቤታቸውን በመጠገን. . . ለጥቂት ሳምንታት እናትህን በመርዳት ማሳለፍ ትችላላችሁ» አለው። ካሌብም «ያ ለጥቂት ጊዜ ይሠራ ይሆናል» በማለት መስማማቱን ነገረው። «ግን በቅርቡ እናቴ አብስላ ለመብላት ወደማትችልበት ደረጃ ትደርሳለች፥ ያን ጊዜስ ምን እናደርጋለን?»

«ከዚያማ ከአንተና ከሚስትህ ጋር እንዲኖሩ ወደ ከተማ ታመጣቸዋለህ. . .»

ካሌብም የቤንን ንግግር በማቋረጥ፥ «ቆይ! እናቴ ከእኔና ከሚስቴ ጋር የምትኖር ከሆነ፥ ያ ማለት ሚስቴ በእናቴ ቤት ከመኖሯ ጋር ተመሳሳይ አይደለምን? በሁለቱም መንገዶች፥ ሁለቱ ሴቶች በአንድ ቤት ይሆናሉ» አለው።

ቤንም፥ «አይሆንም፡- ተመሣሣይ አይደለም፥ እናትህ በእናንተ ቤት ሲኖሩ አንተና ሚስትህ ልትረዱቻውና ልትወዱቻው ትችላላችሁ፤ በዚያ ጊዜም እናትህ ለራሳቸው እንዲህ እንደሚሉ አስባለሁ «እንዴት ያለ ቸርነትን እያሳዩኝ ነው? ይህ የእኔ ቤት አይደለም፥ ነገር ግን የሞቀ አቀባበል አድርገውልኛል፤ ምራቴንም ሆነ ልጄን ለመቆጣጠር መሞከር የለብኝም፤ ምን ያህል እንደማመሰግናቸው ላሳያቸው ይገባኛል እንጂ»።

ካሌብም ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ። በመጨረሻም ሲናገር ድምፁ ከወትሮው ለስለስ ያለ ነበር። «ታውቃለህ ቤን፥ አንተን እየሰማሁ ሳለ በቅድሚያ የሚያስፈልገኝ ለውጥ፥ ሚስቴን መውደድ መጀመር እንደሆነ ተረዳሁኝ። ከሠርጋችን ቀን ጀምሮ የተቀበልኳት እንደ ገረድ ነበር እንጂ እንደ ወዳጄ አልነበረም። ምናልባትም ለእናቴ የማደርገውን ቸርነት የማትፈልግበት ምክንያቱ ያ ሊሆን ይችላል። ከእርሷ ጋር ለመተባበር በመፈለጌ ምክንያት የወላጆቼን ቤት የተውኩ መሆኔን ለሚስቴ ማሳየት ይኖርብኛል»።

ቤንም ካሌብን እያቀፈ፥ *«መሆን ያለበት እንደዚያ ነው፤ ለሚስትህ ፍቅርን ማሳየት ስትጀምር፥ በጣም የተሻለ ስሜት ይኖራታል. . . ከዚያም ሁለታችሁ በአንድነት እናትህን ለመርዳት የምትችሉበትን የተሻሉ ዘዴዎች ታገኛላችሁ»* አለው።




በሚስትህ ተጣበቅ
(ዘፍጥረት 2:24)

እንክብካቤና የልግሥና ፍቅር
ለቤተሰቦችህ አስብ
(1ኛ ጢሞቴዎስ 5:8)።

የእግዚአብሔር ዕቅድ እጅግ በጣም ጥሩ ነው፥ ነገር ግን ቀላል አይደለም!

ለአንድ ባል፥ «አባቱንና እናቱን መተውና በሚስቱ መጣበቅ» ቀላል አይደለም (ዘፍጥረት 2:24)። ዘመዶቻችንን መርዳት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማግኘትም ቀላል አይደለም (1ኛ ጢሞቴዎስ 5:8)።

ቁልፉ ግን፥ በባልና ሚስት መካከል ያለ «የጋራ ፍቅር» እና ለወላጆችም ሆነ ለዘመዶቹ የሚደረግ የእንክብካቤና የልግሥና ፍቅር ነው።

ወጣቶች ሁሉ በሚገባ ሊያውቁት የሚገባቸው፥ «ካገባሁ፥ ወላጆቼን መተውና ከጋብቻ- አጋሬ ጋር መተባበር አለብኝ፤ ከዚያም እኔና ሚስቴ በጋራ ወላጆቻችንን ለመርዳት የምንችልባቸውን ዘዴዎች መፈለግ አለብን» ማለት ነው።

## ምዕራፍ 4

# ፍቅራችን እውነተኛ መሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለን?

ብዙ ወጣቶች «ባልና ሚስት እርስ በርስ ተፋቅረው የሚኖሩበት ዓይነት ትዳር ቢኖረኝ እወዳለሁ» ሲሉ ይደመጣሉ።

ያም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ አንድ ወጣትና አንዲት ልጃገረድ እንደሚፋቀሩ ሊገምቱና ተጋብተው ብዙም ሳይቆዩ ግን በትዳራቸው ላይ ኀዘን ሊያጠላበት ይችላል።




ይህ እንዴት እንደሚከሰት ለማወቅ ፍቅር ሁለት ዓይነት መሆኑን መረዳት ይገባናል። እነርሱም «ራስ ወዳድነት የተጠናወተው ፍቅር» እና «ከራስ ወዳድነት የጸዳ ፍቅር» ናቸው።

ራስ ወዳድነት የተጠናወተው ፍቅር ትዳርን ያበላሻል። የባልና ሚስት ፍቅር ራስ ወዳድነት የተጠናወተው ከሆነ እርሷም ለራሷ እርሱም ለራሱ አብልጠው መጨነቃቸው አይቀሬ ነው። ስለዚህም ቤታቸው በገንዘብ፥ በዘመዶች፥ በልጆች፥ ወዘተ. . . ጉዳይ በሚነሣ ንትርክ የተሞላ ይሆናል።

በአንጻሩ ከራስ ወዳድነት የጸዳ ፍቅር ጋብቻ በደስታ የተሞላ እንዲሆን የሚያደርግ ፍቅር ነው። አንድ ባል ሚስቱን ከራስ ወዳድነት በጸዳ ፍቅር ከወደዳት ከራሱ ይልቅ ለእርስዋ ስለሚያስፈልጋት ነገር አብዝቶ ይጨነቃል።

## ዳን እና ሎይስ

«ሎይስን እወዳታለሁ፤ እናም ላገባት እፈልጋለሁ» በማለት ዳን ለወንድሙ ነገረው።

«እወዳታለሁ ስትል ምን ማለትህ ነው?» ሲል ወንድሙ መልሶ ጠየቀው።

ዳን፥ ይህን ጥያቄ እንዴት መመለስ እንዳለበት እርግጠኛ አልነበረም። ቆይቶ ግን እንዲህ አለ፡- «ለማለት የፈለግሁት፡- እርስዋ አጠገቤ ስትሆን ደስተኝነት ይሰማኛል። ጥሩ ሚስት ልትሆነኝ እንደምትችልም እገምታለሁ። ችግሮቼን እንድትረዳልኝና እንድትንከባከበኝም እፈልጋለሁ። ደስተኛ ሕይወት እንዲኖረኝ ታግዘኛለች»።

የዳን ፍቅር ራስ ወዳድነት የተጠናወተው አይደለምን? አመለካከቱ «ችግሮቼን» ትረዳልኛለች፤ «እንክብካቤም» ታደርግልኛለች የሚል እንደሆነ ልብ በሉ።

ይበልጥ ስለ ራሱ እያሰበ አይደለምን?

## ማርቆስና ግሎሪያ

«ግሎሪያ ደስ የምትል ክርስቲያን ልጃገረድ ነች» አለ ማርቆስ ለመጋቢው ሲናገር። «እወዳታለሁ፤ ከተጋባን በኋላ በየዕለቱ ርኅራኄ በተሞላበት ፍቅር ፍላጎቶቿን ለማሟላት እጠነቀቃለሁ። ገንዘቤን በደስታ ከእርስዋ ጋር እጠቀማለሁ። አጫውታታለሁ። ስሜቶቿን ለመጋራት እሞክራለሁ። የሚገጥማትን ችግር በመረዳት አብሬያት እጸልያለሁ። አሁን እንኳ ሁለታችንም ከቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ጋር ለወንጌል ስርጭት ስንጠመድ እጅግ ደስ ይለናል። ከተጋባንም በኋላ በደስታ እግዚአብሔርን ማገልገላችንን እንቀጥላለን።

የማርቆስ ፍቅር ምን ያህል ከራስ ወዳድነት የጸዳ እንደሆነ ተመልከቱ። ስለ ራሱ ደስታ ብቻ እያሰበ አልነበረም። ለግሎሪያ ቅን አፍቃሪ ለመሆን ይፈልጋል።

ለራሳቸው ሳይሆን ለክርስቶስ መኖር ታላቁ ደስታቸው ነውና ሁለቱም ራስ ወዳዶች አይደሉም።

ከራስ ወዳድነት የጸዳ ፍቅር ቀስ በቀስ የሚያድግ ነው።

ኢዮስያስ ማርታን ባያት የመጀመሪያ ቀን ለራሱ እንዲህ አለ። «ወድጂያታለሁ፤ አዘማመሯና ውብ ዓይኖቿ ይማርካሉ-ፈጥኜም በፍቅሯ ወደቅሁ።»

ሐቁ ግን ኢዮስያስ ማርታን የወደደበት ‹ፍቅር› እውነተኛ አይደለም።

ስለ እርስዋ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚያውቀው በጥቂቱ ነው። ሁለንተናዋን እንደወደደ ሊናገር አይችልም። የተገናኘው ከውጫዊ ማንነቷ ጋር ብቻ ነው።

አንድ ሰው ፈጥኖ በፍቅር ከወደቀ ያ ፍቅር ፈጽሞ እውነተኛ አይደለም።

እውነተኛ ፍቅር (ከራስ ወዳድነት የጸዳ ፍቅር) ፈጥኖ አይመጣም። ለማደግ ጊዜ ይወስዳል።

ስለሆነም ኢዮስያስ «ማግባት የምፈልገው ማርታን ነው» ብሎ ለመናገር መቻኮል የለበትም። ማርታም ብትሆን ስለ እርሱ ለመወሰን መፍጠን አይገባትም።

እርስ በርስ ለመተዋወቅ ጊዜ መውሰድ አለባቸው።

ወራት በተቆጠሩ ቁጥር ምናልባት እውነተኛና ከራስ ወዳድነት የጸዳ ፍቅር በልባቸው ማደጉን ሊገነዘቡ ይችላሉ።

"ምናልባት" የሚለውን ቃል ልብ በል። ከጥቂት ወራት በኋላ «አንዳችን ለሌላችን ከራስ ወዳድነት የጸዳ ፍቅር የለንም። ወዳጅነታችን ከመጠንከር ይልቅ እየተዳከመ ሄዷል» ሊሉም ይችላሉ።

**እርስ በርስ ለመተዋወቅ ጊዜ ውሰዱ።**

በዚህ አኳኋን እነዚህ ሰዎች መጋባት የለባቸውም። ጋብቻ እውነተኛ ፍቅርን ይሻል።

## ለእውነተኛ ፍቅር ስምንት መመዘኛዎች

በማንኛውም ወጣት ልብ ውስጥ «ላገባት/ው ይገባኛልን? *በእውነት* እንዋደዳለን?» የሚል ጥያቄ መኖሩ አይቀርም።

*«ፍቅራችን እውነተኛ ነውን?»* እያለ ለሚጠይቅ ሁሉ አጥጋቢ ምላሽ እንዲያገኝ የሚረዱት ስምንት የመመዘኛ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።» *

## 1) ነፃ ንግግር

«እኔ በንግድ ሙያ አንቺም በሕግ ዲግሪዎች ስላሉን ጥሩ ሥራ ማግኘት እንችላለን። ከዚያ በኋላ ደግሞ እንጋባለን። እናም በርካታ ገንዘብ ይኖረናል» አላት ናታን ለሮዳ።

«ልክ ነህ፡- ውዴ» በማለት መለሰች ሮዳ። በልቧ ያለውን እውነተኛ አሳብ ግን ለመግለጥ ፈርታ ነበር። በውስጥዋ የነበረው አሳብ እንዲህ የሚል ነው። «ለጊዜው ሥራ ቢኖረኝ ደስ ይለኛል. . . የመጀመሪያ ልጃችን እንደተወለደ ግን ሥራዬን ትቼ በቤቴ እቀመጣለሁ። ልጆቻችንን ሁሉ መንከባከብ እፈልጋለሁ። የኛ ልጆች እኔ ባለፍኩበት ዓይነት መንገድ እንዲያድጉ አልፈልግም። እናቴ ከሥራዋ የተነሣ ውጥረት ነበረባት። ስለዚህ እኔን ያሳደገችኝ የተቀጠረች ሞግዚት ናት።

* ከመመዘኛዎቹ አምስቱ የተወሰዱት *«አግብቼሻለሁ»* ከተሰኘው የዋልተር ትሮቢሽ መጽሐፍ ነው (ገጽ 89–92)።

ሁልጊዜ የእናቴን ማሻሸት እናፍቅ ነበር። አልሆነልኝምና አላውቃትም። የዚያ ዓይነት እናት መሆን አልሻም። ከልጆቼ ጋር ጊዜዬን ማሳለፍ እፈልጋለሁ። . . . ግን. . . ለናታን ስለዚህ ጉዳይ ምንም አልነግረውም። አሁን ሳይሆን ከተጋባን በኋላ ልንወያይበት እንችላለን። ነገር ግን ከአሁኑ ወደፊት ሥራዬን ለማቆም እፈልጋለሁ ብለው ይናደድና አላገባሽም ይለኛል»።

ሮዳን እንዲህ ነው የምንላት «ከአሁኑ ጉዳዩን ከናታን ጋር ተወያዩበት። ከልጆችሽ ጋር ጊዜን ለማሳለፍ ምን ያህል እንደምትመኚ አሳውቂው። የልብሽን በግልጽነት ንገሪው። አንቺና ናታን በዚህ ጉዳይ ላይ ተወያይታችሁ ከአንድ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻላችሁ የእናንተ ፍቅር ራስ ወዳድነት የተጠናወተው ነው። በዚህ አኳኋን ልታገቢው አይገባም»።

ፍቅራችሁን ለመመዘን ስትፈልጉ መጀመሪያ ልታስቡበት የሚገባው ጥያቄ ይህ ነው።

*እርስ በርሳችን በነጻነት መነጋገር እንችላለን?*

## 2) ልማዶች

ወጣቶች ብዙ ጊዜ «ከተጋባን በኋላ በእኔ ድጋፍ ከፉ ልማዶቹን/ቿን ይተዋል/ትተዋለች» ሲሉ ይደመጣሉ።

ነገር ግን እውነታው ልማድ ብዙ ጊዜ የማይቀየር መሆኑ ነው።

ስለሆነም ሁልጊዜም ከሚነጫነጭ ወይም ከሚያመሰቃቅል ሰው ጋር ቀሪውን ዕድሜያችሁን መግፋት የማትፈልጉ ከሆነ እንዲህ ዓይነት ልማዶች ያለውን ሰው ለማግባት ፈቃደኛ አትሁኑ።

ኃይለኛ ጠጪ ከሆነ ሰው ጋር መኖር እንደማትችሉ እርግጥ ነው። ስለሆነም የመጠጣት ልማድ ያለውን ሰው አታግቡ።

ጋብቻ ረባሹን ሰው ጨዋ፥ ነጭናጫውን ደስተኛ፥ ኃይለኛ ጠጪውን ደግሞ ራሱን የሚገዛ አድርጎ ሊቀይረው አይችልም።

*ፍቅርን ለመመዘን ሁለተኛው ጥያቄ ይህ ነው፡-*

*ልማዶቹ/ቿ የማይቀየሩ ቢሆኑም እንኳ*

*ከዚህ/ች ሰው ጋር ቀሪ ዘመኔን*

*ለማሳለፍ እወዳለሁን?*




## 3) ያለመነካካት

ጌዴዎን እንዲህ እያለ ያስባል፦ «ዛሬ ከሰዓት በኋላ እኔና አስቴር፦ ዕቃ ለመግዛት እንወጣለን። ከእርስዋ ጋር አብሮ መራመድና መጫወት እንዴት ደስ ይለኛል! እጇን ከእርስዋ ማሸሼን ግን እቀጥላለሁ። እርስዋ በጣም ቆንጆ በመሆንዋ ይህን ማድረግ አስቸጋሪ ነው። ግን «አልነካትም» ስል የገባሁት ቃል እንደ ትክለ-ሰውነትዋ ብቻ ሳይሆን እንደ ሰብዓዊ ፍጡርም የምወዳት መሆኑን እንድንገነዘብ እየረዳኝ ነው።

ሴም ግን የተለየ ነው፤ እንዲህ እያለ ያስባል፦ «ዛሬ ምሽት ከዚህ፦ በፊት ነክቼ የማላውቀውን የሴት ጓደኛዬን የአካል ክፍል እነካለሁ»።

ሴም የሴት ጓደኛውን በእውነት ይወዳት እንደሆነ እርግጠኛ አይደለም። ፍቅሩን ለመመዘን እርስዋን ከመነካካት መቆጠብ አለበት። ያን ጊዜ የሚወድደው የእርሷን ሰብዓዊ ተፈጥሮ ይሁን ወይስ አካልዋን መረዳት ይችላል።

ፍቅርን ለመመዘን ሦስተኛው ጥያቄ ይህ ነው፦

አንዳችን የሌላችንን ሰብዓዊ ተፈጥሮ እናደንቃለን፥

*ወይስ አንዳችን የሌላውን አካል በመደባበስ ብቻ እንደሰታለን?*

## 4) አድናቆት

ሩቤን የበርኒስን አለባበስ ይወደዋል። ነገር ግን አንዳንዴ ራሱን «በወሲብ ጉዳይ ላምናት እችላለሁን?» ብሎ ሲጠይቅ የሚሰጠው መልስ «ፈጽሞ» የሚል ነው።

ሐና ለጆን የፍቅር ዝንባሌ አላት። ግን ስለ እርሱ ያላት መረዳት እንዲህ የሚል ነው፦ «ልጆች አባታቸው እንዲሆን የሚፈልጉት ዓይነት ሰው አይደለም»።

ነገር ግን ሣራ ፊልጶስን በእርግጥ ታደንቀዋለች። ይኸውም ገንዘብን የማያባክን በመሆኑ፥ በቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን በትጋት በማገልገሉ፥ ሕፃናትን በመውደዱና ወሲብን በተመለከተ ንጽሕና የተሞላበት ሕይወት በመኖሩ ነው።

> **ፍቅራችሁ እውነተኛ ከሆነ እርሱ/ሰዋ ጥሩ የትዳር ጓደኛ ይሆነኛል/ትሆነኛለች ብላችሁ ለመናገር ጽኑ ምክንያት ይኖራችኋል።**

ፍቅርን ለመመዘን አራተኛው ጥያቄ ይህ ነው፦

*ያለን የፍቅር ስሜት ብቻ ነው. . . ወይስ እንዳችን ሌላችንን የምናደንቅበት ምክንያት አለን?*

## 5) በሚገባ መተዋወቅ

አንድን ሰው እስካላወቃችሁት ድረስ እርሱን ስለመውደዳችሁ እርግጠኛ ልትሆኑ አትችሉም። ያለፈ እና የአሁኑን ማንነቱን ልታውቁ ይገባችኋል።

ሀ) ያለፈ፦ አበኔር ሺርሌ ለጋብቻ ከመጠየቁ በፊት የሚከተለውን ነገራት፦ «ልነግርሽ የሚገቡኝ አንዳንድ ነገሮች አሉ። ይህን ለመግለጽ በጣም ይከብደኛል። . . . ጌታን እንደ አዳኜ ከመቀበሌ በፊት በጣም እጠጣ ነበር። አንዲት ልጃገረድንም አስረግዣለሁ»።

ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ ሺርሌ አንዳንድ ጥያቄዎችን አቀረበችለት። እርሱም በግልጽነት መለሰላት።

ለአንድ ወጣትና ለአንዲት ልጃገረድ ከጋብቻ በፊት ግልጽ መሆን አስፈላጊ ነው። ይህ ከሆነ ከሁለት አንዳቸው እንዲህ እያሉ አይጨነቁም። «አሁን ያለፈ ታሪኬን ቢደርስበትስ/ብትደርስበትስ?»

ለ) የአሁን፡- በአሁኑ ጊዜ እርሱ/እርሷ ምን ዓይነት ሰው እንደሆኑ እንዴት ለማወቅ ትችላላችሁ? የተሻለው መንገድ ክርስቶስን አብሮ ማገልገል ነው።

አንድ ሰው «ታገቢኛለሽ?» ብሎ ለሚያቀርበው ጥያቄ ጥሩው መልስ የሚከተለው ነው። «በአሁኑ ሰዓት ‹እሺ› ወይም ‹አይሆንም› ለማለት ዝግጁ አይደለሁም። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር እግዚአብሔርን በማገልገል አብረን የበለጠ ጊዜ እንቆይ። ያ እርስ በርስ የበለጠ እንድንተዋወቅ ይረዳናል»።

ከዚያም በሆስፒታል ውስጥ ከሚመሰከር፥ የኤድስ ሕሙማንን ከሚረዳ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ለሕፃናት ከሚነግር ወይም የተራቡትን ከሚመግብ ቡድን ጋር ተቀላቀሉ። እንዲህ ዓይነት ቡድን ማግኘት ካልቻላችሁ ደግሞ አዲስ መሥርቱ። ከዚያ በኋላ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በመተባበር ክርስቶስን ስታገለግሉ እነዚህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎች ምላሽን ታገኛላችሁ። ብዙ ጊዜ ከሰዎች ጋር ይጋጫልን? ከሚነዱት ሰዎች ጋር ለመነጋገር አትፈቅድምን? እየጠጣ ነገሩን በምሥጢር ለመያዝ ይሞክራልን? ጥሩ ሁኔታ ላይ ሳትሆን ስትቀር ጸባይዋ እንዴት ነው? በሚበሳጭ ጊዜ ምን ያደርጋል? ገንዘቧን ለራስዋ ብቻ ትጠቀማለች ወይስ ለጌታ ትሰጣለች? ችግር በሚገጥመው ጊዜ በእግዚአብሔር ይታመናል ወይስ አባይ ጠንቋይ ፍለጋ ገንዘቡን ይከሰክሳል?

ፍቅርን ለመመዘን አምስተኛው ጥያቄ ይህ ነው፡-

*ስለ አለፈውና ስለ አሁኑ በሚገባ እንተዋወቃለን?*

## 6) ለክርስቶስ ያለ ፍቅር

ካሌብ ክርስቶስን ለማገልገል ይተጋል። ሎይስም እንደ እርሱ ናት። «የዓርብ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሰዓት» ለሚባለው ፕሮግራም በየሳምንቱ ሕፃናትን በመጋቢያቸው መኖሪያ ይሰበስባሉ። «ከካሌብ ጋር ከተዋወቅን ወዲህ ወደ እግዚአብሔር በበለጠ ተጠግቼአለሁ» ትላለች ሎይስ።

በሌላ በኩል ኑኃሚን ማርቆስ አንዳንድ የኃጢአት ልምምዶቹን እንዲተው ሁልጊዜ ታሳስበዋለች። እርስዋ ካልገፋፋችው በስተቀር አብረው ጸልየው አያውቁም። ምናልባት ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ እንዲያድግ እየረዳችው ይሆናል። ለእርስዋ ግን ብዙም የሚረባት አይደለም።

*ፍቅርን ለመመዘን የሚያስችለው ስድስተኛው ጥያቄ ይህ ነው፡-*

*ለክርስቶስ የበለጠ ፍቅር እንዲኖረን እርስ በርስ*

*እየተረዳዳን ነውን?*

*ሁለታችንም ክርስቶስን በመታዘዝና በማገልገል*

*ደስ እንሰኛለን ወይስ አንዳችን ብቻ?*

## 7) መስጠት

እውነተኛ ፍቅር መቀበል ብቻ ሳይሆን መስጠትንም ያውቅበታል። እውነተኛ አፍቃሪ ከራሱ ይልቅ ስለ ሌላው ግድ ይለዋል። እውነተኛ ፍቅር «ከአንቺ/ተ ጋር ጨዋና ትዕግሥተኛ እሆናለሁ። አሳብሽን/ህን አደምጣለሁ እናም ስለ ችግሮችሽ/ህ ግድ ይለኛል» የሚል ነው።

እውነተኛ ፍቅር ራስን ከመውደድ የተለየ ነው። ራስን መውደድ «ውደጂኝ/ደኝ ስለሚያስፈልጉኝም ነገሮች አስቢ/ብ» የሚል ሲሆን፥ እውነተኛ ፍቅር «ስለ ፍላጎትሽ/ህ ግድ ይለኛል» ይላል።

ፍቅራችሁ እውነተኛ ከሆነ ደስታን ለመስጠት ትፈልጋላችሁ። እናም ለራሳችሁ ስለ መቀበል ግድ የሚላችሁ በጥቂቱ ይሆናል።

ይህ ማለት ግን ደስታ የራቀው ሰው ማግባት አለባችሁ ማለት አይደለም። ይልቁንስ ደስተኛ ሰው ለመምረጥ ሞክሩ። «ደስተኛ አይደለሁም፤ ማንም እኔን አይወደኝም፤ ደስ ልታሰኚኝ/ኘኝ የምትችይው/ለው አንቺ/ተ ነሽ/ህ» የሚልን ሰው አታግቡ።

ጥሩ ጋብቻዎች እግዚአብሔርን ለማገልገልና አንዱ ሌላውን ደስ ማሰኘት በሚፈልጉ ሁለት ደስተኛ ሰዎች መጀመራቸው የተለመደ ነው።

ፍቅርን ለመመዘን የሚያስችለው ሰባተኛው ጥያቄ ይህ ነው፡—

*«ፍቅርና ደስታን ልሰጣት/ጠው እወድዳለሁን?*

*እርሷ/ሱ ፍቅርና ደስታን መስጠት የምትችል/የሚችል*

*ደስተኛ ሰው ናትን/ነውን?*

## 8) ከጋብቻ በኋላ ይቅርታ

በምድር ላይ ያሉ ጋብቻዎች ሁሉ ግጭቶች ያጋጥሟቸዋል። ነገር ግን ጥሩ ጋብቻ የመሠረቱ ባልና ሚስት ሁለቱም ይቅር ለማለትና የሌላውንም አመለካከት ለመስማት ዝግጁዎች ናቸው።

አንድ ወጣትና አንዲት ልጃገረድ ለመጋባት ከመወሰናቸው በፊት ልብ ሊሉት የሚገባ አንድ ነገር አለ – «ስንጋጭ ምን ይከሰታል?»

እርስ በርሳቸው በእውነት የሚዋወዱ ከሆነ ከሁለት አንዱ እንዲህ ማለቱ አይቀርም «የሚጎዱ ቃላትን በመናገሬ አዝኛለሁ» ይቅርታ ልታደርጊልኝ/ግልኝ ትችያለሽ/ላለህ?»

ሌላውም እንዲህ ይመልሳል። «አዎን፥ ይቅር ብዬሻለሁ/ሃለሁ። እንዲያውም በራስ ወዳድነት የግሌን መንገድ ብቻ በመፈለጌ አዝኛለሁ። እባክሽ/ህ ይቅር በዪኝ/ለኝ። አሁን አሳብሽን/ህን ንገሪኝ/ረኝ። ለመስማት ተዘጋጅቻለሁ»።

> በእውነተኛ ፍቅር ውስጥ
>
> ሁለቱም ሰዎች ሌላውን ስለ መጉዳታቸው ያዝናሉ።
>
> ሁለቱም የራሳቸውን መንገድ ብቻ አይመርጡም።

አበኔርና ሩት ከቤተ ክርስቲያናቸው ዲያቆንና ባለቤቱ ቅድመ–ጋብቻ ምክር ማግኘት ነበረባቸው። ይኸውም በቤተ ክርስቲያን መጋባት እንዲችሉ ነው። «ከግጭት በኋላ እርስ በርስ ይቅር መባባል ትችላላችሁን?» ሲል ዲያቆኑ ጠየቃቸው።

«ተጋጭተን አናውቅም» አሉ ሁለቱም «እንዋደዳለን»።

በእድሜ የበሰለው ብልሁ ዲያቆንም እንዲህ አላቸው «ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት ሁለታችሁም ሁልጊዜ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ በዕጓለ–ማውታ ላሉ ሕፃናት ምግብ ታበስላላችሁ። እኔና ባለቤቴም እንረዳችኋለን። ደስ ትሰኙበታላችሁ። ነገር ግን አብራችሁ ስትሠሩ መጠነኛ ግጭት መከሰቱ አይቀርም። ከዚያ በኋላ ስትጋጩ የሆነውን ነገር መጥታችሁ ትነግሩኛላችሁ»።

ፍቅርን ለመመዘን ስምንተኛው ጥያቄ ይህ ነው፦

*ከግጭት በኋላ ሁለታችንም «አዝናለሁ» ማለት እንችላለን?*
*ይቅርታ እናደርጋለን?*

*አንዳችን የሌላውን አሳብ ያለራስ ወዳድነት*

*ማዳመጥ እንችላለን?*

*ስምምነት ላይስ እንደርሳለን?*

## ወሲብ የፍቅር መመዘኛ አይደለም።

«የምትወጂኝ ከሆነ በተግባር ልየው፤ እንቺነትሽን ስጪኝ» አላት እስጢፋኖስ ለበርኒስ።

«አይሆንም» በማለት መለሰች በርኒስ «ስለምን ለወሲብ ትጠይቀኛለህ? ገና ሳንጋባ? የእግዚአብሔርስ ትእዛዝ? ፍቅርህ ራስ ወዳድነት የተጠናወተው ይመስለኛል»።

«እኔ ራስ ወዳድ አይደለሁም» አለ እስጢፋኖስ «ስለ አንቺ እያሰብኩ ነው። የወሲብ ፍላጎትሽን ላረካ እፈልጋለሁ»።

ነገር ግን በእንቢታዋ እንደጸናች ባየ ጊዜ ይህን ተናገራት።

«እስከ መጨረሻው ደህና ሁኚ»።

በርኒስ ብቻዋን ቀረች። . . . ያም ሚከያስን እስከታውቀው ነበር። እንዴት ያለ የእግዚአብሔር ሰው ነው! እግዚአብሔርን በማገልገል ሁለቱም ደስ ይሰኛሉ! በጆማ የወንጌል ስብከት ላይ ይዘምራሉ።

ቀስ በቀስ ወዳጅነታቸው ጠነከረ። . . . ይህ እውን የሆነው ሁለቱም «ፍቅራችን ስምንቱንም መመዘኛዎች ያልፋል» ማለት በመቻላቸው ነው። ደስ እያላቸው የሠርጋቸውን ቀን ወሰኑ፤ እስከዚያም ቀን ፍትወተ- ሥጋ ላለመፈጸም ቃል ገቡ።




ከከፉ የጎልማሳነት ምኞት ሽሽ (2ኛ ጢሞቴዎስ 2:22)።

ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ። . . . ጡትዋ ሁል ጊዜ ታርካህ፤ በፍቅርዋም ሁልጊዜም ጥገብ (ምሳሌ 5:18−19)።

ከሌላ ሴት ጋር ብትተኛ ትቀጣለህ (ምሳ. 6:29 ተመልከት)።

## እግዚአብሔር እንዴት ይናገረናል?

ስለ ስምንቱ የፍቅር መመዘኛ ነጥቦች ከሰማች በኋላ አንጄላ የተባለች የኮሌጅ ተማሪ ቀጣዩን ማስታወሻ ጻፈችልን።

*የተወደዳችሁ ብሩስና ካሮል፥*

*አንድ ደስ የሚል ሰው እንዳገባው ጠየቀኝ። ልቤ ስለ እርሱ በፍቅር ስሜት ተሞልቷል። እግዚአብሔር በዚህ ስሜት እየተናገረኝ ይመስላችኋል? ወይስ የሚናገረኝ በ«ስምንቱ የፍቅር መመዘኛዎች» ነው? አንጄላ*

ውድ አንጄላ

እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ በስሜቶቻችን አይናገረንም። ለምን? ምክንያቱም የሰው ስሜቶች የሚመጡና የሚሄዱ ናቸው።

እግዚአብሔር ሊናገረን የሚመርጠው በቃሉ ነው። እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

በዚህ ሰዓት ስለዚያ ደስ የሚል ሰው የፍቅር ስሜት አለሽ። ያንን ስሜት እምነት አትጣይበት። መጽሐፍ ቅዱስሽን ተመልከቺ። 2ኛ ቆሮንቶስ 6:14ን በማንበብ የያዘሽ ፍቅር መመዘኛውን ያልፍ እንደሆነ መረዳት ትችያለሽ። ያም «ለክርስቶስ ያለሽ ፍቅር» ነው።

ማቴዎስ 18:21-35 ደግሞ ፍቅር «ከግጭት በኋላ ይቅርታ» የሚለውን መመዘኛ ማለፍ አለበት ይላል።

1ኛ ቆሮንቶስ 13:5 ፍቅር የራሱን እንደማይፈልግ ይናገራል። «የመስጠት» መመዘኛ እርሱ ነው።

ስለሆነም አንጄላ ሆይ፥ «የፍቅር ስሜትሽን» ከማመን ይልቅ «ፍቅር» ምን እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስሽ ተመልከቺ። እናም ፍቅርሽ መመዘኛዎቹን ሁሉ ያልፍ እንደሆነ ለመወሰን አእምሮሽን ተጠቀሚ።

## ምዕራፍ 5

# ፍትወተ-ሥጋ?

> ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥
>
> በሚስቱም ይጣበቃል፥
>
> ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ (ዘፍጥረት 2:24)።

ይህ ጥቅስ ሦስት ነገሮችን ይናገራል፦

ሀ) ሰው ትዳር በሚመሠርትበት ወቅት አባቱንና እናቱን ይተዋል።

ለ) ሚስቱ የእርሱ የቅርብ ዘመዱ ትሆናለች። (ከእርስዋ ጋር «ይጣበቃል»)

ሐ) እርሱና ሚስቱ ፍትወተ ሥጋ በመፈጸም ደስ ይሰኛሉ። («አንድ ሥጋ» ይሆናሉ።)

በርካታ መጽሔቶች፥ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችና ፊልሞች ፍትወተ-ሥጋን ይጠመዝዙታል። ይህም አጥላልተው ለማቅረብ በመሞከር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን አንዲት ሚስት ከባልዋ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈጸምዋ ምንኛ ውብ እንደሆነ ያሳየናል። «መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን» በተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሚስት ባልዋን እንዲህ ትለዋለች።

«በአፉ መሳም ይሳመኝ» (1:2)።

«ውዴ ሆይ፥ እነሆ አንተ ውብ ነህ፥

መልከ መልካምም ነህ» (1:16)።

ባልዋ ደግሞ እንዲህ ይናገራል።

«ሙሽራዬ ሆይ፥ ከከንፈሮችሽ ማር ይንጠባጠባል!

እኅቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት. . . ናት።

ቡቃያሽ. . . የተመረጠ ፍሬ. . . ነው» (4:11-13)።

እነዚህ ባልና ሚስት በእርስ በርስ ፍቅር የሚያገኙት ደስታ እንዴት ታላቅ ነው!

ለባልዋ እንዲህ ብላ እንዳልተናገረችው አስተውሉ «ና፡- አስረግዘኝ። እኔን ለማስደሰት በመሞከር ጊዜ አታባክን። ፍጠን . . . መተኛት እፈልጋለሁ»።

በጭራሽ! ፍትወተ ሥጋ ልጆችን መውለጃ ብቻ አይደለም።

እግዚአብሔር ስለ ፍትወተ-ሥጋ ያለው ዕቅድ ይህ ነው። ሰውየው ዘመዶቹን ይተዋል። ከሚስቱም ጋር ይተባበራል። በግብረ ሥጋ ግንኙነትም እርስ በርሳቸው ደስ ይሰኛሉ።

ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ግብረ-ሥጋን ያዘጋጀው ለጋብቻ ነው። ጀርባቸውን ለእግዚአብሔር በሚሰጡና ከጋብቻ ውጭ ፍትወትን በሚፈጽሙ ላይ ምን ይመጣባቸዋል። ኃጢአታቸው በትዳራቸውና በልጆቻቸው ላይ ኃዘንን ያስከትላል።

ከጋብቻ ውጪ ከማንም ጋር ፍትወተ-ሥጋን ባለመፈጸም እግዚአብሔርን የሚታዘዙ ሰዎች ደስተኞች ናቸው።

**በጋብቻ ውስጥ ታላቁን ደስታ የሚጨብጡት ባልና ሚስት እርስ በርስ በመፋቀር የግብረ -ሥጋ ግንኙነትንም በራሳቸው ብቻ በመወሰን እግዚአብሔርን የሚታዘዙ ናቸው።**

በመላው ዓለም ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን ገሸሽ በማድረግና የሩካቤ ሥጋ ኃጢአት በመፈጸም ይኖራሉ። ሆኖም የፍርድ ቀን እየመጣ ነው። እግዚአብሔር ሁሉም ሰው ከኃጢአቱ እንዲመለስና የክርስቶስ መሥዋዕትነት ካለፈው በደል አንጽቶ በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ጻድቅ እንደሚያደርገው እንዲያምን እያዘዘ ነው።

እነዚህን ጥቅሶች በጥንቃቄ አጥኑ።

> «ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች. . . ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች . . . ወይም ሰካሮች. . . የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል. . . ጸድቃችኋል» (1ኛ ቆሮንቶስ 6:9–11)።

## ሚስትህ መኻን ብትሆን

ሴምና ልድያ ለምክር አገልግሎት ወደ ቤታችን መጡ። ልድያም እንዲህ አለችን። «ልጅ የለኝም፤ ሁለት ዶክተሮችን አማክሬ ነበር። እነርሱም ፈጽሞ መጸነስ እንደማልችል ነገሩኝ። ሴምና እኔ ተአምር ለማየት ጸልየን ነበር፤ የእግዚአብሔር ምላሽ ግን «አይሆንም» የሚል ይመስላል። አሁን በየቀኑ አለቅሳለሁ። ሴም ጥሩ ባል ነው። በምንም ሁኔታ ውስጥ ይወድደኛል። እኔ ግን ዋጋ -ቢስነት ይሰማኛል።»

እኛም እንዲህ መለስንላት። «ልድያ፡- አንቺ ዋጋ ቢስ አይደለሽም። የሚስት ተቀዳሚ ኃላፊነት ልጆችን መውለድ አይደለም። ዋናው ኃላፊነቷ ለባልዋ ወዳጅ መሆን ነው። ጋብቻ ማለትም ልጆችን መውለድ (ማፍራት) ብቻ አይደለም። ጋብቻ ወዳጅነት ነው። ስለሆነም አንቺና ሴም ወዳጆች በመሆን ደስ መሰኘት አለባችሁ። በእርስ በርስ ነፃ ውይይትና በሁለታችሁ የግብረ–ሥጋ ግንኙነትም ደስ ተሰኙ። ደግሞ አብዛኛውን ጊዜያችሁን እግዚአብሔርን ለማገልገል ተጠቀሙበት። ለጌታም እንዲህ በሉት ‹ወደፊትም ልጅ ባትሰጠን

እንኳ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በትጋት እናገለግልሃለን። ልጅ በማትሰጥ ጊዜ አንተ የራስህ በቂ ምክንያት አለህ። ምንም ዓይነት ክፉ ተግባር አትፈጽምም። እናምንሃለን።»

ባልና ሚስት ልጆችን መውለድ ካልቻሉ ቅር መሰኘታቸው ያለ ነገር ነው። ያም ሆኖ ግን ብዙ ልጅ አልባ ጥንዶች ታላቅ ደስታን ይለማመዳሉ። እንዴት ብለን ብንጠይቅ መልሱ ብዙ ጊዜያቸውን ለክርስቶስ በመስጠት መሆኑን እናያለን። አንዳንዶች አረጋውያንን፥ ሕሙማንንና፥ የአካል ጉዳተኞችን በመንከባከብ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ። ሌሎች ደግሞ ዕጓለ–ማውታ የሆኑ ሕፃናትን ወደ ቤታቸው ይወስዱና እንደ ራሳቸው ልጆች በመቁጠር ይወድዷቸዋል።

ልጆችን ባለመውለዳቸው ያጡትን ደስታ ክርስቶስን ሲያገለግሉ ሳለ ያገኙታል።

## ሚስትህ የአንተ እኩያ አጋርህ ናት።

የሴቲቱ ሰውነት በጣም ትናንሽ የሆኑ ዕንቁላሎችን ያመነጫል። እነዚህ ዕንቁላሎች በጣም ትናንሽ ከመሆናቸው የተነሣ በአጉሊ መነጽር (ማይክሮስኮፕ) ካልሆነ በስተቀር አይታዩም። ከባልዋ ጋር የግብረ–ሥጋ ግንኙነት በምታደርግ ጊዜ ከእርሱ የወንዴ ዘር አንዱን ከእርስዋ ዕንቁላል አንዱን ለመስበር ይሳካለት ይሆናል።

ዕንቁላል ብቻውን ሕይወት የለውም። የወንዴ ዘር ፈሳሽም ለብቻው ሕይወት – አልባ ነው። ግን ሲዋሃዱ ሕይወት ያለውን ዘር ይፈጥራሉ። ያ ዘር በእርግጥ አንድ ፍሬ ሕፃን ነው። ከዘጠኝ ወር በኋላ ሕፃኑ/ንዋ ይወለዳል/ትወለዳለች።

እነዚህ እውነታዎች ባልና ሚስት እኩያ አጋሮች መሆናቸውን ያሳያሉ። ግማሹ ዘር ከባልየው ሲመጣ ግማሹ ደግሞ ከሚስትየዋ ይገኛል።



እነዚህ እውነቶች ቀላል ይመስላሉ። ነገር ግን ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት በምድር ላይ የሚያውቃቸው ሰው አልነበረም። አዎን፥ ከሁለት ምእተ-ዓመታት በፊት ማንም (ከእግዚአብሔር በስተቀር) የሴቷ ሰውነት ዕንቁላል እንደሚያመነጭ አያውቅም ነበር። በእነዚያ ዘመናት በአውሮፓ፥ አፍሪካ፥ አሜሪካ፥ እስያ . . . የሚኖሩ ሁሉ «የማሳ አስተሳሰብ»ን በማራመድ ስሕተት ይፈጽሙ ነበር።

## የማሳ አስተሳሰብ *

የማሳ አስተሳሰብ እንዲህ ይላል «ዘሩ የሚመጣው ከወንድየው ነው። ሚስት ዘሮች የሚያድጉባት ቦታ ብቻ ነች። ስለዚህም እንደ ማሳ ትቆጠራለች። እርሱ ደግሞ ዘርን እንደሚተክል ገበሬ ነው።»

## የማሳ አስተሳሰብ




---

* ይህን ስሕተት ለመጀመሪያ ጊዜ «የማሳ አስተሳሰብ» ብለው የሰየሙት ዋልተር ትሮቢሽ ናቸው። ይህም አግብቼሻለሁ በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 29 ላይ ይገኛል።

## የማሳ አስተሳሰብ የተሳሳተ ነው!

የዛሬ 200 ዓመት አጉሊ መነጽሮች ሲፈለሰፉ ሳይንቲስቶች የማሳ አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ስሕተት መሆኑን ደረሱበት። እውነቱ ግን፡-

ሀ) የሴቲቱ ሰውነት የዘሩ ግማሽ የሆነውን ዕንቁላል ያመርታል።

ለ) የወንዱ ሰውነት ዘሮችን አያመርትም። የዘር ፈሳሾችን ብቻ ያመነጫል። የወንዱ ዘር ፈሳሽ ደግሞ የዘሩ ግማሽ ክፍል ብቻ ነው። የዘር ፈሳሾቹ እንደ አበባ ብናኝ ናቸው። ዕንቁላል ካላገኙ የወንዱ የዘር ፈሳሽ ምንም ሊሆን አይችልም።

ሐ) የወንድ ዘር ፈሳሽ 23 ሐብለ-በራሒ አለው። የሴቷ ዕንቁላልም እንዲሁ ነው። በአንድ ላይ ሆነው 46 ሐብለ-በራሒ ያለው ሕፃን ይፈጥራሉ። ስለሆነም ወንድና ሴት እኩያ አጋሮች ናቸው። ለዚህም ነው ሕፃኑ በከፊል አባቱን በከፊልም እናቱን የሚመስለው።

ሳይንቲስቶች የማሳ አስተሳሰብ የተሳሳተ መሆኑን በደረሱበት ጊዜ እግዚአብሔር አልተደነቀም። የማሳ አስተሳሰብ በፍጹም የእግዚአብሔር አስተሳሰብ አልነበረም። እግዚአብሔር ከመጀመሪያው «ሰው ዘሮቹ የሚያድጉበት ስፍራ ያስፈልገዋል፤ ማሳን እናዘጋጅለት» በማለት አልተናገረም።

ይልቁንም አለ፡- «የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» (ዘፍጥረት 2፡18)።

ስለሆነም ሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ የማሳ አስተሳሰብ ስሕተት እንደሆነ ይስማማሉ። ሚስት አጋር እንጂ ማሳ አይደለችም።

## ብዙ ልማዶች የመጡት ከማሳ አስተሳሰብ ነው።

ዛሬ ሰው ሁሉ የማሳ አስተሳሰብ ስሕተት መሆኑን ተረድቷል ለማለት ይቻላል። ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሳይንስም ጭምር ይህን ተምሯል። ስለሆነም የማሳ አስተሳሰብ እየሞተ ነው። ሆኖም እስካሁን ሙሉ በሙሉ አልሞተም። የማሳን አስተሳሰብ በማመን በዓለም ዙሪያ ባሉ አገሮች ብዙ ሰዎች በመቶ የሚቆጠሩ ዓመታትን አሳልፈዋል። ስለሆነም በእርሱ ላይ የተመሠረቱ ብዙ ልማዶች አሉ።

አዎን በመላው አውሮፓ፥ አፍሪካ፥ አሜሪካ፥ እስያና በሁሉም ስፍራ በርካታ ልማዶችን እናገኛለን። የመጡትም ከማሳ አስተሳሰብ ነው። ገጽ 41 እነዚህን ልማዶች ከእግዚአብሔር ዕቅዶች ጋር ያነጻጽራል።



የማሳ አስተሳሰብ



የእግዚአብሔር ዕቅድ

| ከማሳ አስተሳሰብ የመጡ ልማዶች | የእግዚአብሔር እቅድ |
|---|---|
| የማሳ አስተሳሰብ፡- ማሳ ፍራፍሬን እንደሚያፈራ ሁሉ የሚስት ድርሻ ልጆችን መውለድ ነው ወደሚል ልማድ ያመራል። | በእግዚአብሔር ዕቅድ ሚስት አጋር/ወዳጅ ነች። ጋብቻ ልጅ ባይገኝበትም የተባረከ ነው (ዘፍጥ. 2:24)። |
| በማሳ አስተሳሰብ ገበሬ በርካታ ማሳዎች ሊኖሩት እንደሚችል ሁሉ ባልም በርካታ ሚስቶች ሊኖረው ይችላል። | የእግዚአብሔር ዕቅድ ለአንድ ባል አንድ ሚስት ነው (ማቴ. 19:6)። ባልየው ሲሞት ሚስት ደግማ ማግባት ትችላለች (ሮሜ 7:3፤ 1ኛ ጢሞ. 5:14)። |
| ገበሬ የማሳው ኃላፊ፤ ባልም የሚስቱ የበላይ ነው። እንደ ሕፃን ሊቀጣት፥ ሥርዓት ሊያስተምራትና ከባድ ሥራም ሊያሠራት ይችላል። | ስለ ሚስትህ ፍላጎቶች አስብ። እርስዋ ደካማ ነች። እንደ አጋርህ ተንከባከባት። በትክክል ብትንከባከባት ጸሎትህን የሚከለክል ምንም ነገር አይኖርም (1ኛ ጴጥ. 3:7)። |
| ባል በሚሞት ጊዜ ሚስት ገንዘቡን/ ንብረቱን አትወርስም። | ባል በሚሞት ጊዜ ገንዘቡን/ንብረቱን ሚስትየዋ ትወርሳለች (ሩት 4:3)። |
| ሁሉም ገበሬ ማሳ እንዳለውና ሁሉም ማሳ ባለቤት እንዳለው | አንድ ሰው ለማግባትም ሆነ ብቻውን ለመኖር መምረጥ |

ሁሉ በማሳ አስተሳሰብ ሁሉም ሰው ማግባት አለበት።

ይችላል። በላጤነት የሚኖሩ ሰዎች ለእግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ (1ኛ ቆሮ. 7:26-38)።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ አንዳንድ ሰዎች የማሳ አስተሳሰብን አራምደዋል። ለምሳሌ ሰሎሞን በርካታ ሚስቶች (ማሳዎች) ነበሩት። ራሔል ልጆች ስላልነበሩዋት ራስዋን ዋጋ -ቢስ አድርጋ ቆጠረች (ዘፍጥ. 30:1)። አብርሃም ልጅ ለማግኘት አጋርን (ሁለተኛዋን ማሳ) ተጠቀመ (ዘፍጥ. 16:3-5)።

«የእነዚህን ሰዎች ምሳሌ ተከተሉ!» የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለን? በጭራሽ! ይልቁንም ብዙ ጥቅሶች የሚናገሩት እግዚአብሔር ከባሎች እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ እንደሚጠብቅ ነው- *«ሚስቴ ለእኔ ቅርብ ዘመዴና የተመረጠች ጓደኛዬ ናት። አንድ ሚስት አለችኝ። ስለዚህ ዘመዶቼን ሁሉ እተዋለሁ፤ በእርስዋም እጣበቃለሁ። እርስዋ ማሳ ብቻ አይደለችም፤ አጋሬ ናት። እግዚአብሔር ልጆችን ቢሰጠን የመውለዱን ድርሻ ትወስዳለች። ልጆች የማይኖሩን ቢሆን እንኳ አሁንም እወዳታለሁ። በምንም ሁኔታ ውስጥ አብረን እግዚአብሔርን እናገለግላለን» (ማቴዎስ 19:4-6፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 7:2፡5፤ ኤፌሶን 5:28-33፤ 1ኛ ጴጥሮስ 3:7፤ 1ኛ ሳሙኤል 1:8)።*

*እግዚአብሔር ሚስቶች ሁሉ «ልጆች መውለድ ባልችል እንኳ ዋጋ-ቢስ አይደለሁም። እግዚአብሔርን አገለግላለሁ። ባሌንም በአክብሮት/በፍቅር እይዘዋለሁ» የሚል መረዳት እንዲኖራቸው ይፈልጋል (1ኛ ጴጥሮስ 3:5-6)።*




## ምዕራፍ 6

# ኤድስ?

**ኤድስ በግብረ- ሥጋ ግንኙነት ይተላለፋል የሚባለው በእርግጥ እውነት ነውን?**

አዎን፡- ብዙ ሰዎች ኤድስ የያዛቸው በሽታው ካለበት ሰው ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በመፈጸማቸው ነው።

ሌሎች ሰዎች ግን በተለያየ መንገድ ኤድስ ይይዛቸዋል። ለምሳሌ አንዳንዶች የኤድስ ቫይረስ ያለበትን ሰው ደም በመንካት በሽታው ይተላለፍባቸዋል። ሌሎች ደግሞ እንደ ምላጭና መርፌ ያሉትን በደም የተበከሉ መሣሪያዎች በመንካት ሊይዛቸው ይችላል። ስለሆነም ሁላችንም የማንንም ደም ከመንካት መቆጠብ አለብን።

ያም ሆኖ ኤድስ በተለይ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት እንደሚተላለፍ አንዘንጋ። በእርግጥም 95% የሚሆኑት ሰዎች ኤድስ የሚይዛቸው በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ነው (ከ5% ያነሱት ደግሞ በደም ንክኪ ይተላለፍባቸዋል።) በተለምዶ የኤድስ ቫይረስ ወደ ሰውነት የሚገባው በወንድ ወይም በሴት ብልት፥ በፊንጢጣ ወይም በአፍ በኩል ነው።

## አንድ ሰው ኤድስ ሊኖርበትና ላይታወቀው ይችላልን?

አዎን፥ ናታን በትምህርት ቤት ሳለ ከሁለት ልጃገረዶች ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ፈጽሞ ነበር። ከሁለቱ አንድዋ ደግሞ የኤድስ ቫይረስ ተሸካሚ ነበረች። በግንኙነቱ ወቅት ቫይረሱ ወደ ናታን ተላለፈ። ስለዚህም የቫይረሱ ተጠቂ ሆነ።

ከዚያ በኋላ ለረዥም ጊዜ ናታን ጤነኝነት እየተሰማው ቆየ። «ኤድስ እንደሌለብኝ እርግጠኛ ነኝ፤ አልታመምኩም፤ ጤንነት ይሰማኛል» እያለ ለራሱ ይነግር ነበር።

ሆኖም፥ ቫይረሱ ቀስ በቀስ በሰውነቱ ውስጥ እየተሰራጨ ነበር። ከስድስት ዓመታት በኋላ ክብደቱ መቀነስ ጀመረ። በተለያዩ የሰውነቱ ክፍሎች ላይ ቁስሎች ታዩበት። ያን ጊዜ ኤድስ እንዳለበት ተገነዘበ።

## ብዙ ሴቶች ኤድስ የሚይዛቸው ለምንድን ነው?

«አንድ የሚያስፈልገኝ ነገር ቢኖር በእውነትና በእርግጥ የሚንከባከበኝ ሰው ነው» ስትል አሰበች ሎይስ።

እንዲህም በማለት ለራስዋ ቃል መግባት ይኖርባት ነበር። «ከፍተኛ የመፈቀር ፍላጎት ቢሰማኝም እንኳ ከጋብቻ በፊት ሰውነቴን ለማንም አሳልፌ በመስጠት ኃጢአትን አላደርግም» ሎይስ ግን እንዲህ አላደረገችም። በዚያ ፈንታ «በእውነት እወድሻለሁ. . . እስኪ ይህን ውብ ገላሽን ፍቀጂልኝ» ላላት ሰው ራስዋን ሰጠች።

መጀመሪያ ላይ ስለ ኤድስ አስባ ነበር። ኋላ ግን «ይህ ሰው ጤናማ ይመስላል» ስትል ለራስዋ ነገረች።

---

* ለዚህ ምዕራፍ የተጠቀምነው አብዛኛው አሳብ የተወሰደው «ፍቅርና ጋብቻ» ከተሰኘው መጽሐፋችን ነው።

እርሱ ራሱ የማያውቀው ቢሆንም እንኳ ሰውየው የኤድስ ቫይረስ ነበረበት። ከሎይስ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በፈጸመ ጊዜ ቫይረሱ ከእርሱ ወደ እርስዋ ተላለፈ።

በእርግጥ ከሎይስ የፈለገው አንድና ብቸኛ ነገር ከእርስዋ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ነበር። ያንን ካገኘ በኋላ ትቷት በመሄድ ሌሎች ልጃገረዶችን ማታለል ጀመረ።

ሎይስ ልብዋ ተሰበረ። ከዚያም «እወድሻለሁ. . . አንቺም መውደድሽን በተግባር አሳዪኝ» የሚል ሌላ ሰው ገጠማት።

የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ፈጸሙ። ኤድስንም አጋባችበት። ከአምስት ዓመታት በኋላ ሎይስ ያስቀምጣት ጀመር። ተቅማጡም ከሳምንት ወደ ሳምንት አላቋረጠም። «አዝናለሁ ሎይስ፣- ኤድስ አለብሽ» አላት የመረመራት ዶክተር።

እንዴት ያለ ፍርሃት ወደቀባት! «አሁኑኑ ብሞት ምን አለበት» ስትል አለቀሰች። ሆኖም የመጨረሻው የፍርድ ቀን የበለጠ አስፈራት።

እንደ ሎይስ ያሉትን እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?

በኤድስ ለሚሠቃዩ ሰዎች ልናደርግላቸው የምንችለው ብዙ ነገር አለ። ወደ ቤታችን ወስደን ልንከባከባቸው እንችላለን። ለኤድስ ሕሙማን እርዳታ በሚያደርጉ ክሊኒኮች ውስጥ መሥራትም ያው ነው። ይህን በሙሉ ጊዜያችንም ይሁን በከፊል እየተከፈለንም ይሁን በነፃ ልናደርገው እንችላለን። ለታመሙትና ወደ ሞትም ለተቃረቡት እንክብካቤ ማድረግ የሚገባን እኛ ክርስቲያኖች መሆናችንን ኢየሱስ ተናግሮአል (ሉቃስ 10:30-37)።

እየተንከባከብናቸው ሳለ ደግሞ እንዴት ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት እንደሚችሉ ልንነግራቸው ይገባል። «ላይሞቱ ይችላሉ» ብለን ለራሳችን ከመንገር እንቆጠብ። ስለ ዘላለም ሕይወት ለእነርሱ ከመንገር መዘግየት የለብንም። ለምን? ምክንያቱም «ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ ተመድቦባቸዋል» (ዕብ. 9:27)።

ኤድስ ያለበት ሰው «ከኃጢአት የተነሣ እግዚአብሔር ወደ ገሃነም እሳት ይልከኛል» እያለ ያስብ ይሆናል። እኛ ግን የምንነግራቸው አለን።

### መልካሙ የምሥራች

እኛ ሁላችን ኃጢአት ስለሠራን ወደ ገሃነመ እሳት መሄድ ይገባናል። ግን ይቅርታን እናገኝ ዘንድ ኢየሱስ ኃጢአታችንን ተሸከመ። ስለ እኛም ተሰቃየ (ዮሐ. 3:16)።

ኢየሱስን እንደ ጌታና አዳኝ ብትቀበሉት ግን ከእርሱ ሥራ የተነሣ ይቅርታን ታገኛላችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማይም ትገባላችሁ (1ኛ ዮሐ. 5:13)።

## ወንድሜን ኤድስ ይዞታል? በሽታው ወደ እኔ ይተላለፍ ይሆን?

አይሆንም፥ በዚህ ያን ያህል አደጋ የለም። ከወንድምህ ጋር በአንድ ሳህን ብትበሉ፥ አንድ መጸዳጃ ቤት ብትጠቀሙ፥ የምትታጠቡበት ባኞ ቤት አንድ ቢሆን፥ በአንድ ቤት ውስጥ ያለውን አየር ብትተነፍሱ፥ ብትጨባበጡና ብትተቃቀፉ ኤድስ ወደ አንተ አይተላለፍም።

ነገር ግን ደሙን በመንካት ወይም እንደ መርፌ ያሉና ደም የነኩ ስለታም ነገሮችን በመንካት ኤድስ ሊይዝህ ይችላል።

ራስህን ለኤድስ ሳታጋልጥ እንዴት ወንድምህን መንከባከብ እንደምትችል አንድ ዶክተር ወይም ነርስ በትክክል ሊነግሩህ ይችላሉ።

## እንዴት ከኤድስ መሸሽ እችላለሁ?

የሌላን ሰው ደም ወይም ደም የነካውን ማንኛውንም ነገር አትንኩ። ማለት ያለብን አንድ ነገር ይሄ ነው።

ግን ኤድስ ብዙውን ጊዜ የሚስፋፋው ከደም ንክኪ ይልቅ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ነው። ስለሆነም ልንለው የሚገባን ዋና ነገር ይህ ነው። የኤድስ ቫይረስ ካለበት ማንኛውም ሰው ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አትፈጽሙ።

ችግሩ ግን አንድን ሰው ተመልክታችሁ እርሱ ወይም እርሷ ቫይረሱ እንደሌለባቸው የምታውቁበት መንገድ አለመኖሩ ነው።

ስለሆነም በርካታ የፍትወተ-ሥጋ ጓደኞች አይኑሯችሁ። በእርግጥም ከኤድስ ለመሸሽ የተሻለው መንገድ ይህ ነው። ከጋብቻ አጋራችሁ ጋር ብቻ የግብረ -ሥጋ ግንኙነትን ፈጽሙ።

ይህ ማለት ደግሞ፡-

1) ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አትፈጽሙ።

2) ከጋብቻ በኋላ ለባልሽ/ ለሚስትህ ታማኝ ሁኚ/ን።

3) የግብረ -ሰዶምን ኃጢአት አትፈጽም።

«ከኤድስ ለመሸሽ የተሻለው መንገድ» መጽሐፍ ቅዱስን ታዘዙ! የሚል መሆኑ አስደናቂ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

1) ከጋብቻ በፊት ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ሽሽ (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡22)።

2) ከጋብቻ በኋላ ከሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ።

ባገባሃት ልጃገረድ ደስ ተሰኝ።

እንደ ዋላ ውብ ናት።

ጡትዋ ያርካህ

ፍቅርዋ በደስታ ይሙላህ።

ፍቅርህን ለሌላ ሴት ለምን ታጋራለህ. . . ?

እግዚአብሔር የምታደርገውን ሁሉ እንደሚመለከት

አስተውል።

ኃጢአተኛውን ኃጢአቱ ታሳድደዋለች. . .

ስለማይሰማ እርሱ ይሞታል (ምሳሌ 5፡18-23)።





3) የግብረ-ሰዶም ኃጢአት፡- አንድ ወንድ ከሴትዋ ጋር እንደሚተኛ ሁሉ ከወንድ ጋር ከተኛ ሁለቱም ኃጢአተኞች ናቸው። ሁለቱም ሞት ይገባቸዋል (ዘሌዋውያን 20፡13)።

የእኔ ፍርሃት፥ምናልባት የማገባት ልጃገረድ የኤድስ ቫይረስ ይኖርባትና ወደ እኔና ወደ ልጆቻችን ታስተላልፍ ይሆናል የሚል ነው።

ስለዚህ ጉዳይ ልታደርገው የምትችላቸው ሁለት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) በጥንቃቄ ምረጥ፡- ሚስትህን በምትመርጥ ጊዜ አትቸኩል። ባሕርይዋን አጥና። ራስህን «ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልትፈጽም የምትችል ዓይነት ልጃገረድ (እናም የኤድስ ቫይረስ ሊኖርባት የሚችል) ናትን? የዚያ ዓይነት ልጃገረድ ላለመሆንዋ መሆን የምችለውን ያህል እርግጠኛ ነኝ?» ብለህ ጠይቅ።

በእርግጥ በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ግን ስለ አንዲት ልጃገረድ ማወቅ አስቸጋሪ ነው ብለህ ካሰብክ አምስት ወይም አሥር የወሲብ ወዳጆች ላሉአቸው ሰዎች ይህ ምን ያህል አደጋች እንደሚሆን ገምት! አምስቱ ወይም አሥሩ ጓደኞቻቸው ኤድስ እንደሌለባቸው እንዴት እርግጠኛ መሆን ይችላሉ? አይችሉም! ለዚህም ነው በርካታ የግብረ-ሥጋ ወዳጆች ያሏቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ ኤድስ የሚይዛቸው።

ለ) ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ሂዱ፡- አንዲትን ልጃገረድ ከማግባትህ በፊት አብራችሁ ወደ ሆስፒታል ብትሄዱና የጤና ባለሙያ ስለ ኤድስም ሆነ ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ምርመራ ቢያደርግላችሁ መልካም ነው። (ገጽ 115) ይህ ማለት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ማለት ነው እንጂ እርስ በርስ አትተማመኑም ማለት አይደለም።

## በኃጢአቱ ሳቢያ ኤድስ የያዘውን ሰው ልረዳው ይገባኛል ወይስ ስለ ኃጢአቱ እንዲሠቃይ ልተወው?

አትፍረዱ! እርዱት! መልካሙን የምሥራች ንገሩት። ክርስቶስ ይፍረድበት።

> ለሁሉም ሰዎች መልካምን አድርጉ (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡15)።
> ክርስቶስ በሁሉም ሰው ላይ ይፈርዳል (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡10)።

## በዚህ ዘመን ብዙ የማያምኑ ሰዎች ክርስቶስን ለመታዘዝ አይወድዱም። ታዲያ እንዴት ከኤድስ ሊያመልጡ ይችላሉ?

የሚቀጥለው ሠንጠረዥ የእነርሱን ምላሽ ፈሪሃ- እግዚአብሔር ካለበት ምላሽ ጋር ያነጻጽራል።

| የማያምኑ ሰዎች ምላሽ | የክርስቲያን ምላሽ |
|---|---|
| ከኤድስ ለመሸሽ | ከኤድስ ለመሸሽ |
| 1) የግብረ-ሥጋ ግንኙነት | 1) ከጋብቻ በፊት የግብረ -ሥጋ |

ወዳጆቻችሁን በጥንቃቄ ምረጡ። አንድን ሰው ከላይ በመመልከት ብቻ እርሱ/እርስዋ የኤድስ ቫይረስ እንደሌለባቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ስለሆነም በርካታ የግብረ- ሥጋ ጓደኞች አይኑሩዋችሁ።

2) አንድ ወንድ/ ሴት በርካታ የግብረ-ሥጋ ጓደኞች እንዳሉት/ሏት ካወቃችሁ ከእርሱ/ስዋ ጋር ግንኙነት አትፈጽሙ።

3) የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በፈጸማችሁ ቁጥር የእርሱ የዘር/የእርስዋ የብልት ፈሳሽ እንዲነካችሁ አትፍቀዱ። ሁልጊዜ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ በኮንዶም ተጠቀሙ።

4) የማንንም ደም አትንኩ።

ግንኙነት ባለመፈጸም እግዚአብሔርን ታዘዙ።

2) ባል/ሚስት በምትመርጡ ጊዜ ይህን ጥያቄ ለራሳችሁ አቅርቡ፥ ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ባለመፈጸም እግዚአብሔርን እንደሚታዘዝ/ እንደምትታዘዝ መሆን የምችለውን ያህል እርግጠኛ ነኝን?

ደግሞም ከጋብቻ በፊት ሁለታችሁም ወደ ሆስፒታል ሄዳችሁ የኤድስና ሌሎችም የአባላዘር በሽታዎች ምርመራ ብትደርጉ መልካም አሳብ ነው።

3) ከጋብቻ በኋላ ከባላችሁ/ ከሚስታችሁ ጋር ብቻ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን በመፈጸም እግዚአብሔርን ታዘዙ። ለዝሙትና ለግብረ-ሰዶም ኃጢአት ፈተና ምላሻችሁ በጽናት «እምቢ» ይሁን።

4) የማንንም ደም አትንኩ።

«የማያምኑ ሰዎች ምላሽ» ያዘለው አንዱ ችግር ኮንዶሞች ሁልጊዜ ኤድስን ያለመከላከላቸው ነው። ኮንዶሞች የሚችሉት የመያዝን ዕድል መቀነስ ብቻ ነው። ዶክተሮች ሁልጊዜ በኮንዶም የሚጠቀሙ 100 የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በመረመሩ ጊዜ ኮንዶም ቢጠቀሙም እንኳ 17 ያህሉ የኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ እንዳለባቸው ደርሰውበታል።

በኮንዶም እየተጠቀመም/ችም እንኳ አንድ ወንድ/ሴት ኤድስ የሚይዘው/ዛት ከሆነ ይህ አንድን ነገር ያረጋግጣል።

# ከወጣቶች
# የተላኩ ደብዳቤዎች

**ናታን፡-** የአጎቴ ልጅ ሦስት ልጃገረዶችን አስረግዞአል። ግን ሁሉንም «ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አልፈጸምኩም» በማለት ክዷል።

ንስሐ እንዲገባና ክርስቶስን እንዲቀበል ለሁለት ዓመታት ያህል ሳበረታታው ቆየሁ። እናም ዛሬ አሳቤን ለመቀበል ወስኗል። ጥሩ የጸሎት ጊዜ ነበረን። በኋላም «አዎ፥ እውነት ነው. . . እነዚያን ልጃገረዶች ያስረገዝኩ እኔ ነኝ» ብሎ ነገረኝ።

እኔም «ይህንን ጥፋትህን አምነህ እነርሱን በገንዘብ መርዳት መጀመር አለብህ» አልኩት።

እርሱም «ለምንድን ነው ለእነዚያ ሴቶችና ለልጆቻቸው ገንዘብ መስጠት ያለብኝ? ያ ሁሉ የሆነው እኮ ንስሐ ከመግባቴ በፊት ነው። እግዚአብሔር ይቅር ካለኝ ኃጢአቴን አይረሳውም እንዴ?» ብሎ ጠየቀኝ።

እነርሱን መርዳት ግዴታው እንደሆነ እንዴት ላስረዳው እችላለሁ?

**ውድ ናታን፥**

ሁለት ጠቃሚ ጥቅሶችን እነሆ፡-

ከወንዶችም ሆነ ከሴቶች ማንኛውም ሰው ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ባለመገኘት በማንም ሰው ላይ በደል ቢፈጽም፥ ኃጢአቱን ይናዘዝ፤ ስለ በደል ሊከፈል በሚገባው ዋጋ ላይ ከመቶ ሃያ እጅ በመጨመር ለተበደለው ሰው ካሣ ይስጥ ዘኁልቁ 5፡6–7 በአዲሱ ትርጉም)።

እግዚአብሔር የሚረሳው ኃጢአታችንን እንጂ የእናቶችንና የልጆችን መሠረታዊ ፍላጎቶች አይደለም።

**ሣራ፡-** 16 ዓመቴ ነው። መስተዋት ባየሁ ቁጥር ራሴን እጠላለሁ። ፊቴ ላይ ብጉር አለብኝ። ጡቶቼም ትላልቅ ናቸው። ጡቶቼ ከዚህ በላይ ያድጋሉ ብዬም እፈራለሁ፥ እንደ እናቴ ትላልቅ ጡቶች እንዲኖሩኝ አልወድም። ምን ማድረግ ይሻለኛል?

**ውድ ሣራ፥**

መስተዋት ሲመለከቱ ራሳቸውን የሚጠሉ ወጣቶች ስንት ናቸው ቢባል መልሱ አብዛኛዎቹ ነው!

በእርግጥ፥ አብዛኛዎቹ በአፍላ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች «ቆዳዬ ለስላሳ አይደለም፥ በጣም ወፍራም ነኝ፥ ቆዳዬ በጣም ነጭ ነው ወይም በጣም ጥቁር ነው» ብለው ያስባሉ።

መጽሔቶች «ብጉር አስቀያሚ ነው፥ የእኛን ክሬሞችና ቅባቶች ግዙ!» የሚሉ ቆንጆ ጅትን ያወጣሉ።

ክሬሞችና ቅባቶችን የሚያመርቱ ኩባንያዎችም ወጣቶች አስቀያሚ ነኝ የሚል ስሜት እንዲያድርባቸው ይፈልጋሉ። አዎን፦ ወጣቶች «እኔ አስቀያሚ ስለሆንኩ ቆንጆ የሚያደርጉኝን ነገሮች መግዛት አለብኝ!» ብለው እንዲያስቡ ለማድረግ ይሞክራሉ።

ስለዚህ ሣራ፥ ብቻሽን አይደለሽም። በርካታ ወጣቶች «አስቀያሚ ነኝ» ብለው ስለሚያስቡ ጊዜአቸውን በኀዘን ያሳልፋሉ።

ምክራችን ይህ ነው፤

## 1. አመለካከትሽን ለመቀየር ጥቂት ጊዜ ውሰጂ።

ሀ) ብጉር፦ በቀን ሁለት ጊዜ ፊትሽን በሳሙናና ለብ ባለ ውኃ ታጠቢ። በእርግጥ ተራ ሳሙና ማንኛውም ዓይነት ክሬምም ሆነ ቅባት የሚረዱትን ያህል ይጠቅማል። ይሁን እንጂ፥ በየቀኑ በሳሙና መታጠብ ብጉሮችን ሁሉ ያስወግዳል ብለን ተስፋ አንሰጥሽም። ብዙ ወጣቶች ብጉር አለባቸው፤ ግን በተለምዶ 25 ዓመት ሲሆናቸው ይጠፋል።

ለ) ትላልቅ ጡቶች፦ ጠቅላላው ክብደትሽ ከተገቢው በላይ ከሆነ፥ በትክክል በመመገብ፥ ከባድ ሥራና ረጅም የእግር ጉዞ የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ መቀነስ ትችያለሽ።

ክብደትሽ ተመጣጣኝ ሆኖ ሳለ ጡቶችሽ ግን ትላልቅ ከሆኑ፥ ለመቀነስ የሚያስችል ምንም ዓይነት ዘዴ የለም። ስለዚህ ለምን ትጨነቂያለሽ?

## 2. እግዚአብሔርን በማገልገል ተጠመጂ።

እግዚአብሔርን በተለያዩ መንገዶች ስታገለግይ፥ አንዳንድ ችሎታዎች እንዳሉሽ ልትገነዘቢ ትችያለሽ- ይህም ምናልባት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ለልጆች የመንገር ወይም በሆስፒታል ውስጥ የሚመሰክር ቡድንን የማደራጀት ችሎታ ሊሆን ይችላል። ከሌሎች ወጣቶች ጋር በኅብረት ስትሠሪ፥ ሌሎችን በመርዳትሽ ትደሰቻለሽ። «አስቀያሚ» የምትሉት ነገርም ያን ያህል አሳሳቢ እንዳልሆነ ሁላችሁም በሚገባ መረዳት ትችላላችሁ።

ራሔል፦ 16 ዓመት ሊሞላኝ ነው። የወር አበባ ባለማየቴ እጨነቃለሁ። ጡቶቼም እስካሁን ትናንሽ ናቸው። ይህ ይስተካከል ይሆን?

ውድ ራሔል፥

አዎ፥ ይስተካከላል። አትጨነቂ። አንዳንድ ልጃገረዶች የእድገት ለውጥ የሚያዩት በ10 ዓመታቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ እስከ 17 ዓመታቸው ሊቆዩ ይችላሉ። አንዳንድ ወንዶች በ11 ዓመታቸው የዕድገት ለውጥ ሲያሳዩ ሌሎቹ እስከ 19 ዓመታቸው ድረስ ይቆያሉ።

አንድ ሰው በ10፥ በ17 ወይም በ19 ዓመቱ የእድገት ለውጥ ቢያይም ልዩነት የለውም። ሆኖም ቶሎ የሚጀምሩት ከሚዘገዩት የተሻለ ጥቅም አያገኙም።

ሉቃስ፦ የ15 ዓመት ልጅ ነኝ። ታዲያ ልጃገረዶችን ስመለከት «አቤት እግሮቿ . . . አቤት ተክለ–ሰውነቷ. . . እንዴት ታምራለች?» ስል ራሴን አገኘዋለሁ።

ለምንድን ነው እንዲህ ያሉ አሳቦች የሚመጡብኝ? በእርግጥ ክርስቲያን ነኝ?

ውድ ሉቃስ

ከ10 ዓመት በታች የሆኑ ወንዶች ለልጃገረዶች የሚያሳዩት ዝንባሌ አነስተኛ ነው። በአሥራዎቹ ውስጥ ሲሆኑ ግን ሁሉም ወንድ ልጆች «እእምሮዬ ስለ ልጃገረዶች ማሰብ ይወዳል!» ይላሉ።

እንደዚያ የሚሆነው ለምንድን ነው? ምክንያቱ፥ እግዚአብሔር «ፒቱታሪ» የተባለ ዕጢ ጭንቅላትህ ውስጥ በማስቀመጡ ነው። በመጀመሪያዎቹ 9 የሕይወት ዘመንህ ይህ ዕጢ ምንም ዓይነት ሥራ የለውም። ከዚያ በኋላ ከ10 እስከ 19 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ይህ ዕጢ ፈሳሽ ቅመም (ሆርሞን) እያመነጨ ወደ ሁሉም የሰውነት ክፍሎችህ ማሰራጨት ይጀምራል። ሆርሞኖቹም ሰውነትህን «እስከ አሁን ልጅ ነበርክ፤ አሁን ግን ወደ አቅመ - አዳም መጠጋት የምትጀምርበት ጊዜ ነው» እያሉ ይነግሩታል።

ከዚያም በብብቶችህ ውስጥና በብልትህ አካባቢ ፀጉር ያድጋል። ድምፅህ መጎርነን ይጀምራል፤ ጡንቻዎችህም እንደ አዋቂ ሰው ጡንቻዎች ይጠነከራሉ።

የአንዲት ልጃገረድም «ፒቱታሪ» ዕጢ ወደ ሙሉ ሴትነት እንድትለወጥ የሚያደርጉ ፈሳሽ ቅመሞችን (ሆርሞን) አመንጭቶ

ይልካል። ከዚህም የተነሣ የወር አበባ ታያለች፥ ዳሌዎቿ ይሰፋሉ፥ ጡቶቿም ያድጋሉ።

ሉቃስ፥ አሁን አስተውል። ሆርሞኖች የሚደርሱት አካልን ብቻ ሳይሆን አእምሮንም ጭምር ነው። ለዚህ ነው በአንተ ዕድሜ ያሉ ወንዶች ስለ ልጃገረዶች ማሰብ የሚጀምሩት (ልጃገረዶችም ስለ ወንዶች ልጆች ማሰብ የሚጀምሩት)።

17 ዓመት ሲሞላህ ለልጃገረዶች የሚኖርህ ዝንባሌ አሁን ካለህ ይልቅ ይበረታል። 19 ሲሆንህማ የባሰ ይሆናል! ለምን? ምክንያቱም በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የፒቱታሪ ዕጢ የሆርሞን ምርቱን ስለሚጨምር ነው።

አስተውል፡- የእግዚአብሔር ዕቅድ ይህ ነው፤ አንድ ልጅ ወደ ሙሉ ሰውነት ሲያድግ፥ የአንዲት ወጣት ሴት አፍቃሪ ባል መሆን እስከሚችል ድረስ ለልጃገረዶች ያለው ዝንባሌ እያደገ መቀጠል አለበት።

ሰይጣን በአንተ ዕድሜ ያሉ ወንድ ልጆችን ለማታለል ይሞክራል። «አንተ ልጅ፥ ስለ ልጃገረዶች ብዙ ታስባለህ፤ እግዚአብሔርም አዝኖብሃል። ከአሁን በኋላ ክርስቲያን አይደለህም። እንደ አንተ ያለ ብልሹ ልጅ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ የለበትም» በማለት በጆሮአቸው ያንሾካሹካል።

ሉቃስ፥ ሰይጣንን አትስማው። ሁለት ነገሮችን ብቻ አድርግ።

1. «ከልጅነት ወደ ሙሉ ሰውነት በምለወጥባቸው ዓመታት ለልጃገረዶች ያለኝ ዝንባሌ ያድጋል። ያም ደግሞ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዳላዘነብኝ በሚገባ መገንዘብ አለብኝ። አሁንም ቢሆን ክርስቲያን ነኝ።

   «ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ፍትወተ-ሥጋ የመፈጸም አሳብ ወደ አእምሮዬ ሲመጣ፥ እግዚአብሔርን እንዲረዳኝ እጠይቀዋለሁ፥ ራሴንም በሥራ አጠምደዋለሁ። ያን ጊዜ አእምሮዬ እንደዚያ ያሉ ነገሮችን ለማሰብ ጊዜ አይኖረውም። ከልጃገረዶች ጋር ኃጢአት ለመሥራት ቀርቶ እንዲያ ለማሰብም እንኳ አልፈልግም» ብለህ ለራስህ ንገረው።

2. «ሆርሞኖቼ ጠንካራ ስሜትን ቢፈጥሩብኝም እንኳ፥ እስከማገባበት ቀን ድረስ ከማንም ጋር ፍትወተ - ሥጋ ባለመፈጸም ልታዘዝህ እፈልጋለሁ፤ ከዚያም በኋላ ፍትወተ- ሥጋ የምፈጽመው ከሚስቴ ጋር ብቻ ይሆናል» ብለህ ለእግዚአብሔር ንገረው

እንድርያስ፡- እኔ የ 15 ዓመት ወጣት ነኝ። በጓደኛዬ መጽሐፍ ላይ እንዲህ የሚል ነገር አነበብኩ። «አንድ ወንድ ልጅ ፍትወተ ሥጋ ካልፈጸመ የዘር ፈሳሹ በሰውነቱ ውስጥ ይከማቻል፤ ይህም የዘር ፈሳሹ ደካማ እንዲሆን ያደርገዋል።» ይህ እውነት ነውን?

ውድ እንድርያስ፡-

አይደለም፤ ይህ ሐሰት ነው። እውነታው ከ11-19 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል የወንዶች ሰውነት የዘር ፈሳሽ ማመንጨት መጀመሩ ነው።

አንዳንድ ወንዶች ግን ዘራቸውን በልጃገረዶች ውስጥ ያፈስሳሉ። (ማለትም ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ይፈጽማሉ።) ይህ ከእግዚአብሔር ሕግ ተጻራሪ ነው። የእርሱ ሕግ «ከጋብቻ ውጭ የተፈጸመ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው» ይላልና።

እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የወሰነ ወጣት እስከ ጋብቻው ቀን ድረስ ብልቱን በማንኛዋም ልጃገረድ ብልት ውስጥ አያስገባም። ታዲያ የዘር ፈሳሹ ምን ይሆናል? በሰውነቱ ውስጥ ይጠራቀማልን? አይደለም። ከጊዜ ወደ ጊዜ የዘር ፈሳሹ በብልቱ በኩል ይወጣል። መጠኑም አንድ ማንኪያ ያህል ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ በቀን ወይም በማታ የሕልም ወቅት የሚከናወን ነው። የዘር ፈሳሹ ተስፈንጥሮ በመውጣት አንሶላውን ያረጥባል። ይህ ኃጢአት አይደለም። «የግብረ-ሥጋ ግንኙነት » ሊባልም አይችልም። የዘር ፈሳሹ ሰውነቱን ለቅቆ ወጣ እንጂ።

እናም እንድርያስ የጓደኛህ መጽሐፍ አባባል ትክክል አይደለም። የዘር ፈሳሽ ለረዥም ጊዜ በሰውነት ውስጥ አይከማችም። ስለሆነም አትጨነቅ። እስከምታገባበት ቀን ድረስ ከማንም ጋር ፍትወተ -ሥጋ ባለመፈጸም እግዚአብሔርን ታዘዝ (1ኛ ተሰሎንቄ 4፡3)።

ስምዖን፡- ከሴት ጓደኛዬ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ብፈጽም ኃጢአት ነውን? በኮንዶም ብጠቀምስ፤ ይህም ኃጢአት ነው?

ውድ ስምዖን፥

አዎን፥ ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው።

የእግዚአብሔር ሕጎች እነዚህ ናቸው፡-










«የግብረ—ሥጋ ግንኙነት» ማለት ብልትህን በሴት ብልት ውስጥ ማስገባት ነው። በኮንዶም ብትጠቀምም እንኳ ከጋብቻ በፊት የተፈጸመ የግብረ—ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው።

መላ አካልህን የሰጠህ እግዚአብሔር ነው። አካልህን ለተጠቀምክበት አኳኋን ደግሞ አንድ ቀን እርሱ ፍርድን ይሰጥሃል።

> «መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡10)።

ማርታ፦ «ፍትወተ—ሥጋ ተፈጥሮአዊ ነው፤ ማንም እንደ ኃጢአት ሊቆጥረው አይገባም» እያሉ ጓደኞቼ ይነግሩኛል።

ውድ ማርታ፥

ማንም ሰው «ፍትወተ—ሥጋ ተፈጥሮአዊ ነው» ሲል በአና ላይ የደረሰውን ያስታውሰናል።

አና በዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን በምትከታተልበት ወቅት አንዳንድ ልጃገረዶች እንዲህ ይሏት ነበር። «ማንኛውም ሰው የግብረ -ሥጋ ግንኙነት ያስፈልገዋል። ታዲያ አንቺ ከወንዶች ጋር ለመውጣት እሺ የማትይው ለምንድን ነው? ይህን ኋላ— ቀር አመለካከትሽን ካላስወገድሽ በስተቀር በሕይወትሽ ደስታን አትቀምሺም።»

አና ግን ቤተሰቦቿ ስለ እርሷ የንጽሕና ሕይወት ያላቸውን አመኔታ ታውቅ ነበር።

ከዚያም አንድ ሰው እርሷን የመቅረብ ዝንባሌ አሳየ። «እስከተዋደድን ድረስ ፍቅራችንን በሰውነታችንም ብንገልጽ ችግር የለውም» በማለት ብዙም ሳይቆይ የግብረ—ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ጠየቃት።

አና ነገሩን ከጓደኞቿ ጋር ተወያየችበት። ብዙዎች ጓደኞቿ «በእርግጥም. . . ሁለት ሰዎች ከተዋደዱ፣ የግብረ -ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽሙ. . . ያለ ነው» አሏት።

አና የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ ባትፈልግም እንኳ በሌላ ወገን የወንድ ጓደኛዋ እንዳይተዋት ስጋት ገባት።

በሌላ ጊዜ ይህንኑ ጥያቄ ደግሞ አነሣባት። «ከእኔው ጋር እንዲቆይ የሚፈልገውን ላደርግለት ይገባኛል» ስትል ራስዋን አሳመነች።

በሚቀጥለው ዉት የሕሊና ወቀሳ አስቸገራት። እርስዋ ግን እንዲህ በማለት ራስዋን አጽናናች። «ከወንድ ጓደኛዬ ጋር የግብረ- ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ኃጢአት አይደለም፣ ያለ ነው።»

በዚህም መሠረት የሚከተለውን ማስታወሻ ጽፎ እስከላከላት ቀን ድረስ የእርሱን ጥያቄ ማስተናገዱን ቀጠለች። «ደህና ሰንብቺ፣ ሌላ ልጃገረድ ለማግባት ወስኛለሁ።»

አና እንዴት አዝና ይሆን! በሚቀጥለው ወር ማርገዝዋን ተገነዘበች።

የግብረ -ሥጋ ግንኙነት ተፈጥሮአዊ ነው? አዎን፥ ነገር ግን በሰዎች ዘንድ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ቅደም ተከተሉ እንዲህ ነው።




ኢሳይያስ፥ «መጽሐፍ ቅዱስ ከጋብቻ በፊት የግብረ -ሥጋ ግንኙነት እንዳንፈጽም ይነግረናል» በማለት በዩኒቨርሲቲያችን ስትናገር ሰማሁ።

አንድ ጥያቄ ልጠይቅ፦ አንተና ባለቤትህ ከመጋባታችሁ በፊት እንዲህ አላደረጋችሁም?

ውድ ኢሳይያስ፥

ጥያቄህን በጋራ ለመመለስ እንሞክራለን።

ካሮልና ብሩስ፦ ከመጋባታችን በፊት እርስ በርሳችንም ሆነ ከሌሎች ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አልፈጸምንም።

ካሮል፦ የጋብቻችን ምሽት ለእኔም ሆነ ለካሮል የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም የመጀመሪያችን ነበር። ያ ደግሞ አዲስ፥ ያልተበከለ፣ ትኩስና አስደናቂ አደረገው። «ብሩስ ከሌሎች ልጃገረዶች ጋር ያወዳድረኝ ይሆን?» ብዬ አልተጨነቅሁም።

ብሩስ፦ እኔም «በዚሁ ጉዳይ ልምድ ስለሌለኝ ካሮል ዝቅ አድርጋ ትመለከተኝ ይሆን?» ብዬ አልሰጋሁም።

ካሮል፦ ብሩስ አስቀድሞ ይህን ስላልተለማመደ እንዴት ደስ አለኝ! የሠርግ ዕለትን ምሽት አዲስ፥ ትኩስና አስደናቂ የሚያደርገው ምን መሰላችሁ? «ልምድ አልባ» መሆን ነው።

ካሌብ፦ አንዳንድ ወንዶች ፍትወተ-ሥጋ ባማራቸው ቁጥር ያገኟትን ልጃገረድ ይጠይቃሉ።

እኔስ በክርስቲያንነቴ ሰውነቴን ፍትወት ሲያሰኘው ምን ማድረግ እችላለሁ? ያን ስሜት ለማጥፋት አብዝቼ መጽሐፍ ቅዱሴን ማንበብ ይኖርብኝ ይሆን?

ውድ ካሌብ፥

ወጣት እንደ መሆንህ መጠን ጠንካራ የፍትወት ፍላጎት ይኖርሃል። ክርስቲያን ወጣቶችም የዚሁ ዓይነት ስሜት አላቸው።

ነገር ግን እግዚአብሔር ማንኛውም ፈተና ከአቅማችን በላይ እንዲበረታ አይፈቅድም። ክርስቲያን ምን ጊዜም «አይሆንም» ማለት ይችላል።

ለክፉ ምኞቶች «አይሆንም» የሚል ምላሽ የሚሰጡ በርካታ ክርስቲያን ወጣቶች በዓለም ዙሪያ ይገኛሉ። አንተም ትችላለህ!




«ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህ ጸጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ‹ክደን› . . . ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርን በመምሰል በአሁኑ ዘመን ‹እንድንኖር ያስተምረናል» (ቲቶ 2፡12)።

ካሌብ፥ «አይሆንም» ለማለት የሚረዱህ አራት ነጥቦች እነዚህ ናቸው።

## 1) ስለምታየው ነገር ተጠንቀቅ።

ሰዎች የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት የሚፈጽሙበትን የቴሌቪዥን ፕሮግራም የምታይ ወይም የተራቆቱ ልጃገረዶችን ምስል

የምትመለከት ከሆነ የፍትወት ምኞትህን ለመቆጣጠር የበለጠ ትቸገራለህ። ስለዚህ በዓይኖችህ መልካሙን ነገር እንጂ ክፋትን አትይባቸው።

## 2) በቤተ ክርስቲያንህ አብዝተህ አገልግል።

ዝም ብለህ ተቀምጠህ ስለ ግብረ-ሥጋ ግንኙነት አታስብ። በቤተ ክርስቲያንህ አገልግሎት ይብዛልህ። በኅብረት ዝማሬ ቡድን ውስጥ ተሳተፍ፥ ወይም የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት ተለማመድ። ከሌሎች ወጣቶች ጋር በመሆንና ከቤት ወደ ቤት በመዘዋወር መስክር። በአገርህ የተለያዩ ክፍላተ-አገርና ወደ ሌሎችም አገሮች ወንጌልን ለማዳረስ ራስህን ስጥ።

«ለእግዚአብሔር ተቀኙ፤ ይህንም በምድር ሁሉ ላይ አስታውቁ» (ኢሳይያስ 12፡5)።

## 3) በርትተህ ሥራ፤ በስፖርትም ተሳተፍ።

በቤትህ ቤተሰቦችህን እርዳ። በአትክልት ቦታ ሥራ። ቤቱን ጠግን። ጠቃሚ ነገሮችን ገንባ። አዎን፥ በየዕለቱ በርትተህ ሥራ።

በተጨማሪም ቴኒስ፥ እግር ኳስ ወይም የምትወደውን ዓይነት ስፖርት አዘውትር።

ከዚያ በኋላ እንዲህ ስትል ራስህን ታገኘዋለህ። «በሥራ ከተጠመድኩ የፍትወት ምኞቴን መቆጣጠር አያስቸግረኝም።»

## 4) ወደ እግዚአብሔር በመጠጋት እደግ።

መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ አጥና። አብዝተህ ጸልይ። ጥሩ መጻሕፍትን አንብብ። ለጓደኞችህ መስክር።

---

**ካሌብ «ያንን የፍትወት ስሜት ለመቋቋም አብዝቼ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብኝ ይሆን?» ስትል በደብዳቤህ ጠይቀሃል። መልሳችን፡- አዎን በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስህን አጥና የሚል ነው። ነገር ግን የፈለገውን ያህል መጽሐፍ ቅዱስህን ብታነብ አንዳንድ ጊዜ የፍትወት ስሜት ሊኖርህ እንደሚችል እወቅ። እንደገናም ምንም እንኳ የጠቆምንህን ነገሮች ሁሉ (ከባድ ሥራ፥ ስፖርት፥ ዝማሬ፥ ወዘተ. . .) ብትሠራም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ጠንካራ የፍትወት ፈተና ሊገጥምህ ይችላል።**

በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ምን ማድረግ ትችላለህ?

«አይሆንም» ማለት ትችላለህ (ፊልጵስዩስ 4፡13)።

«አይሆንም» ማለት አስቸጋሪ ነው። ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር ድልን መጨበጥ ትችላለህ። ፈተናው በገጠመህ ቁጥር እርሱ መውጫውን መንገድ ያዘጋጅልሃል።


ክርስቲያን ግን ሰው ነው፤
ማምለጥን ሊመርጥ ይችላልና።
ፈተና
«ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና
አልደረሰባችሁም፤
ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ
ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥
ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው
ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል» (1ኛ
ቆሮንቶስ 10:13)።

ሊዎናርዶ፡- በዩኒቨርሲቲያችን የክርስቲያናዊ ወንጌል ስርጭት ስብሰባ ላይ አንዲት (የዶክትሬት ምሩቅ) ሴት እንዲህ አለችን። «እርግዝናንና ኤድስን ለመከላከል ኮንዶምን በጥንቃቄ እስከተጠቀማችሁ ድረስ ከጋብቻ በፊት የምትፈጽሙት የፍትወተ-ሥጋ ግንኙነት ከጥፋት አይቆጠርም።»

እኛም «መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚነግረን ከፍትወታዊ ጋጠ-ወጥነት እንድንሸሽ ነው» ስንል መለስንላት።

እርሷ ግን «መጽሐፍ ቅዱስን በግሪክ ቋንቋ ብታነቡት ይህ ትእዛዝ የተሰጠው ለባለትዳሮች እንደሆነ ትረዳላችሁ። ያላገቡ ሰዎች ፍትወታዊ ጋጠ-ወጥነት እንዳይፈጽሙ አልታዘዙም። ስለሆነም ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ፍትወተ-ሥጋ ኃጢአት አይደለም» ስትል መለሰች።

ትክክል ናት ወይ?

ውድ ሊዎናርዶ፥

በፍጹም፥ ትክክል አይደለችም። 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡2፥ 8 እና 9ን አንብብ። እነዚህ ቁጥሮች የተጻፉት ላላገቡት ነው። ያላገቡ ሰዎች ራሳቸውን ለመግዛት መጠንቀቅ እንዳለባቸው ይናገራሉ። ግን ራስን መግዛት ከተሳናቸው ወይም ከተቸገሩ ደግሞ ማግባት አለባቸው።

ስለሆነም ከጋብቻ በፊት የፍትወተ -ሥጋ ግንኙነት የሚለው ጥያቄ መነሣት የለበትም። ኃጢአት ነው።

ሊዎናርዶ መጽሐፍ ቅዱሳችን ሰዎች ሊያታልሉን እንደሚሞክሩ ይናገራል። እኛ ግን «በተረዳነው መኖርን መቀጠል» አለብን። (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡14)።

ኢዩኤል፡- የ16 ዓመት ወጣት ነኝ። የዘር ፈሳሽ በወጣኝ ጊዜ ሁሉ በደለኝነት ይሰማኛል።

እውነተኛ ክርስቲያን ነኝ፤ አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኔ እሰብካለሁ፤ በትምህርት ቤትም ለጓደኞቼ ስለ ክርስቶስና የዘላለም ሕይወትን ስለማግኘት እነግራቸዋለሁ።

ከማንም ጋር የግብረ- ሥጋ ግንኙነት ባለመፈጸም እግዚአብሔርን ታዝዣለሁ። እስከማገባ ድረስ እየጠበቅሁ ነው።

አሁን ችግሬ በአንዳንድ ምሽቶች በሕልሜ ከሴት ጋር ግብረ-ሥጋን ስፈጽም አያለሁ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወደፊት ስለማገባት ሚስት ሳስብ የዘር ፈሳሼ ከብልቴ ይፈስሳል።

ሁልጊዜ ያስጨንቀኛል. . . . ይህ ኃጢአት ነውን?

«የግብረ -ሥጋ ግንኙነት» ሊባል ይችላል?

«የግብረ-ሥጋ ግንኙነት» የሚለው ቃልስ ፍቺው ምንድን ነው?

ውድ ኢዩኤል፡

መጽሐፍ ቅዱስ ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት እንዳንፈጽም ይነግረናል። ይህ ማለት እስከ ሠርግ ዕለት ድረስ ብልትህን ወደ ማንኛውም ሰው ሰውነት ማስገባት የለብህም ማለት ነው።

በሠርግህ ዕለት ግን ብልትህን ወደ ሚስትህ ብልት ውስጥ ታስገባለህ። ያ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ነው። ሁለታችሁ በየጊዜው በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ደስ መሰኘት ትችላላችሁ። ነገር ግን ከሚስትህ ሌላ ከማንም ጋር የግብረ -ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የለብህም (1ኛ ቆሮንቶስ 6:15-18)።

ኢዮኤል አሁን ደግሞ በሰውነትህ ውስጥ ምን እየተከናወነ እንዳለ ልንገልጽልህ እንፈልጋለን።

ከልጅነት ወደ ሙሉ ሰውነት ወደምትሸጋገርበት ዕድሜ ደርሰሃል። ሰውነትህም የዘር ፈሳሽን ማመንጨት ጀምሯል። አንዳንድ ጊዜ ያ የዘር ፈሳሽ ከብልትህ ሊፈስስ ይችላል። በአንተ ዕድሜ ላሉ ወንዶች ልጆች ይህ የተለመደ ነው።

ስለሆነም ይህ ሲያጋጥምህ አንድ ስሕተት የፈጸምክ መስሎ አይሰማህ። ኃጢአት አይደለም።

ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ስለሚፈጸም የግብረ -ሥጋ ግንኙነት ብታልምም ኃጢአት አይደለም። እናም የዘር ፈሳሽህ ከብልትህ ቢፈስስ ኃጢአት አይደለም። እንዲህ የሚልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የለም። ስለሆነም በደለኝነት ሊሰማህ አይገባም።

የበደለኝነት ስሜት ሊሰማቸው የሚገባ ሰዎች ቢኖሩ እነዚህ ከጋብቻ ውጪ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙት ናቸው። ይህ ኃጢአት ነው (ምሳሌ 7:6-25)።

ኢዩኤል አንተ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት አልፈጸምክም።

ምናልባትም ሰይጣን እንዲህ በማለት በጆሮህ አንሾካሹኮ ይሆናል። «ኢዩኤል፡- አንተ መስበክም ሆነ መመስከር አይገባህም፤ መጥፎ ልጅ ነህ።»

ሰይጣንን አትስማው። ሕልሞችም ሆኑ የዘር ፈሳሽ ከብልት መውጣት ኃጢአት አይደሉም። ስለሆነም አትጨነቅ።



የሠርግ ቀን

እግዚአብሔርን ማገልገልህን ቀጥል፤ እስከ ሠርግህ ቀን ድረስ ከማንም ጋር የግብረ -ሥጋ ግንኙነት ባለመፈጸም ለእርሱ መታዘዝህን ግፋበት።

ሚርየም፦ ማንኛውም ወንድ ለፍትወተ-ሥጋ ሲጠይቀኝ ምላሼ «አይሆንም» የሚል ነው። ነገር ግን አንዳንዴ በሕልሜ ፍትወት ቢጤ ይሰማኛል። ከዚያም ደስታ ይወርረኝና ወደ እርካታ እደርሳለሁ። በምሽት ብቻም ሳይሆን አንዳንዴ በቀንም የዚሁ ዓይነት የሚያረካ ስሜት አጋጥሞኝ ያውቃል።

በቤተ ክርስቲያናችን የወንጌል ስርጭት አስተባባሪ ነኝ። እግዚአብሔርን በጣም እወደዋለሁ። በእነዚህ ስሜቶች አሳዛኝ ኃጢአት እየፈጸምኩ ሳይሆን አይቀርም የሚል ፍርሃት አለብኝ።

ውድ ሚርየም፥

ምንም ኃጢአት አልፈጸምሽም። ይህ ኃጢአት ነው የሚል አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የለም። ስለሆነም አትጨነቂ።

ለፍትወተ-ሥጋ ለሚጠይቁሽ ሁሉ «አይሆንም» ማለትሽን እስከ ሠርግሽ ዕለት ቀጥዪ። ከጋብቻ በኋላም ከባልሽ በስተቀር ለማንኛውም ሰው «አይሆንም» በዪ። ደግሞም ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በጋራ እግዚአብሔርን ማገልገል ቀጥዪ (መኃልየ መኃልይ 8፡8-10፥፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡4-5፤ ሮሜ 12፡1)።

ሉቃስ፦ እኔና ታላቅ ወንድሜ በአንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በመማር ላይ እንገኛለን። እርሱም «ለጋብቻ ለመዘጋጀት በተቻለን መጠን ከበርካታ ልጃገረዶች ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምምድ ማድረግ አለብን» ይለኛል።

የእግዚአብሔርን ሕግ በማስታውሰውም ጊዜ «በጌታ ላይ ፊታችንን አናዞርም፤ ግን ልምምድ ብቻ ነው» ይላል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ይናገራል። «የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ልምድ ማዳበር የወደፊቱን ትዳርህን ለማሻሻል ይጠቅማል።»

ምን ማድረግ አለብኝ?

ውድ ሉቃስ፥

ወንድምህ እንዲያታልልህ አትፍቀድ። «በልጃገረዶች ላይ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምምድ ማድረግ ኃጢአት ነው (2ኛ ሳሙኤል 13:11–13)። ወንድምህ «በጌታ ላይ ፊታችንን አናዞርም» ይላል። ግን ኢየሱስ «ስለ ምን ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም» ይላል (ሉቃስ 6:46)።

ወንድምህ እንዲህም ብሏል «የግብረ- ሥጋ ግንኙነትን ልምድ ማዳበር የወደፊቱን ትዳርህን ለማሻሻል ይጠቅማል»። መጽሐፍ ቅዱስ ግን «ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና» ነው የሚለው (ገላትያ 6:7)። ይህ ማለት ደግሞ ከጋብቻችን በፊት ኃጢአትን ከዘራን በኋላ መልካም ጋብቻ ማጨድ አንችልም ማለት ነው።

የማኅበራዊ ሳይንስ ጠቢባን የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት እያረጋገጡ ነው። ለምሳሌ ያህል ቲምና ቤቨርሊ ላሄይ * የግብረ- ሥጋ ግንኙነት ልምድ ለጋብቻ ይጠቅም እንደሆነ አጥንተው ነበር። ለዚህም በሺህ ለሚቆጠሩ ባልና ሚስቶች የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንሥተዋል።

1) በጋብቻችሁ ውስጥ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ደስ ትሰኛላችሁን?

2) ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምድ ነበራችሁን?



በውጤቱም፡- «አይ፥ የግብረ - ሥጋ ግንኙነት ደስ አያሰኘንም» ያሉት «አዎን፥ ከጋብቻችን በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምምድ ነበረን» ያሉት ሆነው ተገኝተዋል።



እንዲሁም በአብዛኛው «አዎን፡- በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ደስ እንሰኛለን» ባዮቹ «ከጋብቻችን በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አልፈጸምንም፤ በሠርጋችን ዕለት ደናግል ነበርን» ብለዋል።

* LaHaye, Tim & Beverly. The Act of Marriage, Zondervan, p210

ሌሎችም የማኅበራዊ ሳይንስ ጠቢባን ተመሳሳይ ግኝትን ጨብጠዋል። በኔብራስካ ዩኒቨርሲቲ የተካሄደው ጥናት «ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ለትዳር የሚበጅ እንዳልሆነ» ደርሶበታል።

ስለሆነም ዶክተር ፒ.ፓፔኑ እንዲህ ጽፈዋል፦

«በጣም የተዋጣላቸው ትዳሮች የሚመሠረቱት በሁለት ከጋብቻ በፊት በግብረ-ሥጋ ባልተነካኩ ወንድና ሴት መካከል እንደሆነ በተለያዩ ሰዎች የተደረጉ ጥናቶች ይስማማሉ።»+

ደስታ የራቀው ጋብቻ፦ አንድ ምሽት ቶም እና ባለቤቱ ዩኒስ በእንግዳ ማረፊያ ክፍላቸው ይዝናኑ ነበር። ሕፃናቱ ተኝተዋል። ቶም ጋዜጣ እያነበበ ሲሆን ዩኒስ ደግሞ ሹራብ ትሠራለች።

«አድምጪኝ» አለ ቶም «አንድ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ‹ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ለተወጠነው ጋብቻ የሚጠቅም ልምምድ እንዳይደለ› ደረሰበት ይላል። ሰውየው ጤነኛ አይመስለኝም፤ እኔና አንቺ ከጋብቻ በፊት የግብረ -ሥጋ ግንኙነት ስንፈጽም ውብ ነበር!»

ለተወሰኑ ደቂቃዎች በክፍሉ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ። ከዚያም ዩኒስ ረጋ ብላ እንዲህ ተናገረች። «ካነሳውስ አይቀር አሁን መናገር አለብኝ፤ አንድም ቀን ውብ መሆኑን አስቤ አላውቅም።»

«ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?» ሲል ጠየቃት ቶም።

ዩኒስ ጥያቄውን ስትመልስ አሁንም ድምጽዋ ረጋ ያለ ነበረ። «ለማለት የፈለግሁት . . .ሁልጊዜም ሰዎች የምናደርገውን ያውቁብናል የሚል ፍርሃት ነበረብኝ። ወይም ደግሞ ሳላረካህ እቀርና ትተኸኝ ትሄዳለህ የሚል ፍርሃት ነበረብኝ። ነገር ግን ከሁሉ የሚልቀው ፍርሃቴ ከጋብቻ በፊት እንዳላረግዝ ነበር . . .»

«ቆይ እስኪ አንዴ» አለ ቶም አቋርጧት «እንዳላረግዝ ስትዪ ምን ለማለት ፈልገሽ ነው? ሁልጊዜም ኮንዶም እጠቀም ነበረ።»

---

+ Popenoe, P.*Are Virgins Out of Date?* Editions Trobisch, p15.

«ልክ ነህ፡- ግን እነዚህ ነገሮች ሁልጊዜም ውጤታማ ላይሆኑ ይችላሉ፣ እባክህ አትናደድ፣ የአንተ ስሕተት ነበር እያልኩ አይደለም፣ ለማለት የፈለግሁት. . . ውብ አልነበረም. . . . ለእኔ።»

ለረዥም ጊዜያት ጸጥታ ሰፈነ።

በመጨረሻም ቶም ጥያቄ ሰነዘረ። «አሁን ከተጋባን በኋላ እንኳ በግብረ ሥጋ ግንኙነታችን ደስ የማትሰኚው ለዚህ ነው ማለት ነው?»

«እንደዚያ ይመስለኛል፣ ግን ሁልጊዜም ይህንን እንዳልነግርህ እፈራ ነበር።» በእንባ የራሰችው ዩኒስ ከዚህ ሌላ መናገር አልቻለችም።

የእኛ ምክር፡- «የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ልምድ ማዳበር የወደፊቱን ትዳር ለማዳበር ይጠቅማል» የሚሉህን ሰዎች አትመን። እግዚአብሔር ግን እንዲህ ሲልህ እመነው። «መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ» (ኤርምያስ 7፡23)።

ኢዮስያስ፡- ለአምስት ዓመታት ያህል ካገኘኋቸው ልጃገረዶች ሁሉ ጋር እተኛ ነበር። አሁን ይህን የአኗኗር ዘይቤ መተውና ክርስቲያን መሆን እፈልጋለሁ።

መጀመሪያ መውሰድ ያለብኝ ርምጃ ምን እንደሆነ አላውቅም። ከጋብቻ በፊት የማደርገውን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በማቆም ልሞክረው ይሆን?

ውድ ኢዮስያስ፥

አይደለም። «ከጋብቻ በፊት የሚደረግን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መተው» የመጀመሪያው እርምጃ ሊሆን አይችልም። መጀመሪያ ልትወስደው የሚገባህ እርምጃ ክርስቲያን መሆን ነው። ክርስቲያን ለመሆን በወሰንክ ቀን ሀ) ይቅርታ፥ ለ) የዘላለም ሕይወት፥ እና ሐ) መንፈስ ቅዱስን ትቀበላለህ። መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ይሰጥሃል። በእርሱ ኃይል ከጋብቻ በፊት የሚደረግን የግብረ-ሥጋ ግንኙነትና ሌሎችንም ማንኛውም ዓይነት ኃጢአቶች የመተው ችሎታ ይኖርሃል።

እና እንዴት ክርስቲያን መሆን ትችላለህ? ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ቀጥተኛ ምላሽ እነሆ።

# እንዴት ክርስቲያን መሆንና ክርስቲያናዊ ሕይወትን መኖር እንደሚቻል

[ሀ] በዓለማችን ያሉ ሁሉም አገሮች መልካሙን የምሥራች ይሰሙ ዘንድ እርሱ ወደ ምድር እንደመጣ ኢየሱስ ተናግሯል። [ለ] መልካሙ የምሥራቹ ምንድን ነው? ዜናው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንድትኖር የሚፈልግ መሆኑ ነው። ነገር ግን አንድ ችግር አለ። የእርሱን ሕጎች ተላልፈሃል። በእርግጥ እኛ ሁላችን ሕግጋቱን ተላልፈናል። ስለሆነም ከሞትን በኋላ ለዘላለም ከእርሱ መለየት ይገባናል። [ሐ] ነገር ግን እግዚአብሔር ያንን ችግር አስወግዶታል። ልጁን (ኢየሱስን) የእኛን ኃጢአት እንዲሸከምና በእኛም ፈንታ እንዲሠቃይ ላከው።

ሀ) ማርቆስ 16:15
ለ) ሮሜ 3:23
ዕብ. 9:27
ሐ) ሮሜ 5:8
ሮሜ 6:23
መ) ዮሐንስ 3:16
ሠ) ራእይ 3:20
ረ) ዮሐንስ 1:12
ሰ) 2ኛ ቆሮ. 5:17
ገላትያ 5:22
ሸ) 1ኛ ዮሐ. 1:9
1ኛ ዮሐ. 5:13

[መ] አሁን እግዚአብሔር ኢየሱስን ለመቀበል የሚመርጥ ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንደሚቀበል ቃል ገብቷል። [ሠ] «የሚመርጥ» የሚለውን ቃል ልብ በል። እግዚአብሔር አያስገድድም። የዘላለምን ሕይወት መቀበል የሚፈልግ ሰው ሁሉ ኢየሱስን እንደ ጌታና አዳኙ ለመቀበል መምረጥ አለበት። [ረ] አንድ ሰው ያን በሚፈጽም ጊዜ እውነተኛ ክርስቲያን ይሆናል።

[ሰ] «እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን ከኃጢአት ነፃ ያወጣል። ስለሆነም ከዚያ በኋላ ኃጢአት አይገዛቸውም።» «አይሆንም» ለማለት ነፃ ናቸው። በእግዚአብሔር ኃይል በትዕግሥትና በርኅራኄ ማደግ ይችላሉ። [ሸ] በሚወድቁ ጊዜ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸዋል። እናም የመንግሥተ –ሰማያትን ተስፋ ይሰጣቸዋል።

ይህ መልካም የምሥራች አይደለምን?

ኢዮስያስ ዛሬ ኢየሱስን ለመቀበል መምረጥ ትችላለህ። እርሱም የአንተ ወዳጅ ለመሆን ይፈልጋል። እርሱን ለመቀበል እንደምትወስንም ተስፋ ያደርጋል።

ዛሬውኑ ክርስቲያን ለመሆን ከፈለግህ አሁኑኑ ልትጸልየው የምትችለው ጸሎት ይኸው።

## ጌታን ለመቀበል የሚደረግ ጸሎት

እግዚአብሔር ሆይ፥ ሕግህን ተላልፌአለሁና ቅጣት ይገባኛል። በእኔ ፈንታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደተሠቃየ አምናለሁ። አሁን እርሱን እንደ ጌታዬና እንደ አዳኜ አድርጌ ልቀበለው መርጫለሁ።

እባክህ ዛሬ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ።

ለዘላለም በመንግሥተ-ሰማይ ስለምኖር አመሰግንሃለሁ። ይህም እኔ ከፈጸምኳቸው መልካም ሥራዎች የተነሣ ሳይሆን ኢየሱስ ዕዳዬን ስለከፈለ ነው።

ጌታ ሆይ፥ ከዛሬ ጀምሬ ለአንተ መኖር እፈልጋለሁ።

ይህን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጸልያለሁ። አሜን።

ኢዮስያስ፥ አሁን ይህንን ጸሎት ከልብህ ጸልየህ ከሆነ ከዛሬ ጀምሮ ክርስቲያን ሆነሃል። አሁን የዘላለም ሕይወትን አግኝተሃል። እናም መንፈስ ቅዱስ ወደ ልብህ ገብቷል። ለአንተ ቢሰማህም ባይሰማህም እርሱ በዚያ አለ። አዲስ ሕይወት መኖር ትችል ዘንድ ብቃትን ይሰጥሃል።

ጠንካራ ክርስቲያን ወደ መሆን ታድግ ዘንድ የሚረዱህ አንዳንድ ነጥቦች ደግሞ እነሆ:- መጽሐፍ ቅዱስህን በየዕለቱ አጥና! መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ወደምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ሂድ። ተጠመቅ! ገጽ-የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ጨምሮ በተጠቀሱት በሌሎች ኃጢአቶች ላይ ፊትህን አዙር [60]። የዘላለምን ሕይወት እንዴት እንዳገኘህ ለጓደኞችህ ሁሉ ንገር። እነርሱም ክርስቶስን እንዲከተሉ አበረታታቸው።

እንዲሁም መልካሙን የምሥራች ለሕዝብ ሁሉ ለማዳረስ ከቤተ-ክርስቲያንህ ጋር ተባበር (ማቴዎስ 28፡19)።

መልካሙን የምሥራች ወደ

- ተለያዩ የአገርህ ክፍሎች (ክፍላተ አገር) እና
- ወደ ሌላውም ዓለም አድርስ!



«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም . . . በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ» (የሐዋርያት ሥራ 1:8)።

በክርስቲያን ሕይወት እንዴት መቀጠል እንደምትችል የበለጠ ለማወቅ ከገጽ 132 እስከ 158 ተመልከት።

ጌዴዎን፡— ለብዙ ዓመታት ከጓደኞቼ ጋር እግር ኳስ በመጫወት ደስ እሰኝ ነበር። ተጫውተን ስናበቃ መጠጥ እንጠጣለን። ባለፈው ሳምንት ጌታን ተቀበልኩ። እናም አሁን ከእነርሱ ጋር እንደማልጠጣ ነገርኳቸው። ጓደኛቸው መሆኔን ልቀጥል ወይ?

ውድ ጌዴዎን፥

አዎን! ለእነርሱም ኢየሱስ ያስፈልጋቸዋል። አትተዋቸው። ጓደኝነትህን ቀጥል! መስክርላቸው። እንዴት የዘላለምን ሕይወት እንዳገኘህም ንገራቸው።



ለመመስከር የሚመረጠው ዘዴ በአንድ ጊዜ ለአንድ ሰው መንገር ነው። ከጓደኞችህ በመጀመሪያ ለየትኛው መመስከር እንዳለብህ እግዚአብሔርን ጠይቀው። ለዚያ ሰው መስክርለት! ከዚያም ለሌላው የመመስከር ዕድልን ይሰጥህ ዘንድ እግዚአብሔርን ጠይቅ። ለሁሉም መስክረህ እስክትጨርስ. . . እንዲሁ ቀጥል። አንዳንዶቹ ጌታን እንደሚቀበሉ ተስፋ አድርግ።

ነገር ግን ተጠንቀቅ! ጓደኞችህ ወደ ኃጢአት እንዲጎትቱህ አትፍቀድላቸው። እግር ኳስ መጫወት ኃጢአት አይደለም። መጠጣት ግን ኃጢአት ነው (ኤፌሶን 5:18)።

«አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ» (ይሁዳ 1:23)።

ሎይስ፡- መሞት እፈልጋለሁ! በትምህርት ቤት ሳለሁ የወንድ ጓደኛ ነበረኝ። ከእርሱ ጋር ፍትወተ-ሥጋ ለመፈጸም ዕቅድ አልነበረኝም። አንድ ቀን ግን እየተሳሳምን ሳለ ስሜቴ በጣም ናረ። «በእውነት እወድሻለሁ» ሲለኝ አመንኩትና ግንኙነት እንድናደርግ ፈቀድኩለት።

ከቆይታ በኋላ «አርግዣለሁ» ብዬ ነገርኩት። እርሱም «ያ የራስሽ ችግር ነው፤ ደግሜ ላይሽ አልፈልግም» አለኝ።

ከጓደኞቼ አንዷ እንዴት ማስወረድ እንደሚቻል ነገረችኝ። የራሴን ልጅ የመግደሉን አሳብ ባልወደውም እንኳ በዚህኛው ዕድሜዬ መውለድ አልፈለግሁም። ስለዚህ ፈጸምኩት።

ከሳምንት በኋላ በሆዴ ውስጥ ሕመም ይሰማኝ ጀመረ። ወላጆቼም ወደ ሆስፒታል ወሰዱኝ። ከምርመራ በኋላ ዶክተሩ እንዲህ አላቸው። «ልጃችሁ ውርጃ ፈጽማለች። አሁን ስታስወርድ ስሕተት እንደተፈጸመ ደርሼበታለሁ። የማኅፀንዋ ቧንቧ ተጎድቷል። ቀዶ-ሕክምና ላደርግላት ይገባኛል፤ ያለበለዚያ ትሞታለች።»

በሚቀጥለው ቀን ዶክተሩ የማኅፀኔን ቧንቧ ማስወገድ እንደሚኖርበት ነርስዋ ነገረችኝ።

ከዚያ በኋላ መውለድ እንደማልችል ስረዳ «አ፡- ምናለበት እንድሞት ብትተውኝ?» እያልኩ አለቀስኩ።

ወደ ትምህርት ቤቴ ስመለስ ጓደኞቼ የማስወረዴን ዜና እንደ ሰሙ ተረዳሁኝ። በጥሩ ሰላምታ ቢቀበሉኝም ቅሉ ለእኔ ዝቅተኛ ግምት እንደሚኖራቸው አውቅ ነበር። ከጓደኞቼ ጋር የማሳልፈውን ጊዜ ትቼ ብቻዬን በቤት ውስጥ መቀመጥ ጀመርኩ። ቤተሰቦቼ እንኳ የራቁኝና ፍቅራቸውም የቀዘቀዘ መሰለ።

አሁን በአንድ ሱቅ ውስጥ እየሠራሁ ነው። አንዱና ዋናው ምኞቴ ማግባት ነው። ግን ወንዶች ሁሉ መውለድ እንደማልችል ሰምተዋል።

ብዙ ጊዜ በልጅነቴ አደርግ እንደነበረው ወደ ኢየሱስ ለመጸለይ እሞክራለሁ። ግን እርሱም ገሸሽ እንደሚያደርገኝ እርግጠኛ ነኝ። ታዲያ ሁሉ ሰው ካገለለኝ መኖሬን መቀጠል ያለብኝ ለምንድን ነው?

ውድ ሎይስ፥

ደብዳቤሽ አንድን ሰው ያስታውሰናል። እርሱም ቤቱን ትቶ ከከተማ ውጭ ለመኖር የተገደደው ነው። ምክንያቱም የለምጽ በሽታ ነበረበት። ሊጠጋውም ሆነ ሊነካው የሚወድድ አልነበረም።

አንድ ቀን ግን ይህ ሰው ኢየሱስን አየው። «ኢየሱስ ልታነጻኝ ትችላለህ!» ብሎም ጮኸ (ማርቆስ 1፡41)።

ኢየሱስም *ዳሰሰው* ከዚያም «ንጻ!» አለው።

ስሚ ሎይስ፦ ኢየሱስ ገሸሽ አያደርግሽም። ሊነካሽና ይቅር ሊልሽ ይፈልጋል።

አሁኑኑ «ኢየሱስ፦ ልታነጻኝ ትችላለህ!» ትይው ዘንድ እየጠበቀሽ ነው።

ይህንን በምታደርጊ ጊዜ ይቅርታን ትቀበያለሽ። ከዚያ በኋላ በየጠዋቱ ራስሽን እንዲህ ልትይው ይገባል። «እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤ አሁን ወደ መንግሥተ-ሰማይ እንደምሄድ አውቃለሁ። ዛሬ እና በየዕለቱ ታላቁን ጌታ ማገልገል እፈልጋለሁ።»

ሎይስ፦ «ሕይወት ቀላል ይሆንልሻል» ማለት አንችልም። ምክንያቱም ኃጢአትን ዘርተሻል። እናም አንዳንድ ችግሮችን ማጨድሽ አይቀርም። እነዚህም ልጅ-አልባ መሆንን የመሳሰሉ ናቸው (ገላትያ 6፡7)። አሁንም ግን እግዚአብሔር ለሕይወትሽ መልካም ዕቅድ አለው (ኤርምያስ 29፡11)። አንቺ አሁን የተጋፈጥሽውን ዓይነት ችግር የሚገፉና በደርዘን የሚቆጠሩ ወጣቶችን ለመርዳት እንኳ ሊጠቀምብሽ ይችላል።

ምናልባትም ሳታገቢ ትኖሪ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን ይችላል። እንደዚያ ከሆነ በሙሉ ልብሽ አገልግይው። እርሱ ደስታን ይሰጥሻል! (1ኛ ቆሮንቶስ 7፡34)።

ወይም እግዚአብሔር ባል አዘጋጅቶልሽ ይሆናል። ያም ባል ሚስት ልጆችን የምትወልድ ብቻ ሳትሆን ጓደኛ እንደሆነች የሚረዳ ነው። እናም አንቺና ባለቤትሽ ክርስቶስን በጋራ ማገልገል ትችላላችሁ። ዕጓለ-ማውታ የሆኑ ልጆችን ወደ ቤታችሁ ማምጣትና እንደ ራሳችሁ ልጆች በፍቅር ማሳደግም ትችላላችሁ።

በዚህ ጊዜ ሕይወትሽ እንደተሰበረ ሸክላ ነው። ኢየሱስ ስባሪዎቹን ማንሣትና ውብ አድርጎ መሥራት ይፈልጋል። ብቻ ጠይቂው። እርሱ ይፈጽመዋል!

ርብቃ፦ ኢየሱስ ዛሬ ወደ ምድር ሲመለከት አብያተ-ክርስቲያናት በቀዳሚነት እንዲፈጽሙ የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ውድ ርብቃ፥

*ቀዳሚ ምኞቱ ይህ እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ክርስቶስ የእኛ ቤተ-ክርስቲያናት መልካሙን የምሥራች ወደ ራሳችን ሕዝቦችና ወደ ሌሎችም አገሮች በማድረስ ሥራ እንዲተጉ ይፈልጋል።*

# ኢየሱስም አለ፦

«እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ. . . እያጠመቃችኋቸው . . . ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው (ማቴዎስ 18:19-20)።




«እነሆ እላችኋለሁ፥ ዓይናችሁን አንሡ፥ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ» (ዮሐንስ 4:35)።

«ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፥ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት» (ማቴዎስ 9:37-38)።

«ልጄ ሆይ ዛሬ ሂድና (ሂጂና) በወይኔ አትክልት ሥራ (ሥሪ)» (ማቴዎስ 21:28)።




«መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም. . . በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (የሐዋርያት ሥራ 1:8)።

«ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን. . . የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል» (ማቴዎስ 19:29)።

«. . . ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ» (ማቴዎስ 6:19)።




«በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት. . . በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል. . .እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ» (ሉቃስ 24:47-48)።

በጣም የሚያሳዝነው አንዳንድ ቤተ-ክርቲያናት ወንጌልን ወደ ሌሎች ለማድረስ የሚያደርጉት ጥረት ደካማ መሆኑ ነው። ያም ሆኖ ወንጌል እጅግ የሚያስፈልጋቸው ሕዝቦች አሉ። ለምሳሌ ያህል በምዕራብ ቻይና ‹ኢየሱስ› የሚለውን ስም ያልሰሙ አሥር ሚሊዮን ሰዎች አሉ።

በሞዛምቢክ ሰሜናዊ ግዛት ከ 50,000 የሚበልጡ ሰዎች በራሳቸው ቋንቋ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ አላዩም።

99% የሚሆነው የሶማሊያ ሕዝብ ሙስሊም ነው። እምነታቸውም እንዲህ ይላል። «ኢየሱስ ለማንም ሰው ኃጢአት አልሞተም።»

ተመሳሳይ ሁኔታ የሚንጸባረቅባቸው ሃያ የሚሆኑ አገሮች በምድራችን አሉ።

ቤተ-ክርስቲያናት ሠራተኞችን ይልኩ ዘንድ እኛ ክርስቲያኖች መጸለይና ከገንዘባችን ብዙውን ለዚሁ መደገፊያ መስጠት አለብን። እናም እያንዳንዳችን እግዚአብሔርን «ጌታ ሆይ፥ እኔን የትም ቦታ ላከኝ!» ልንለው ይገባል (ኢሳይያስ 6፡8፤ የሐዋርያት ሥራ 13፡2)።




ዶሪን፡- ክርስቶስን እወድዳለሁ። አንድ ወንድ ለጋብቻ ሲጠይቀኝ «እሺ» ወይም «አይሆንም»፥ ከማለቴ በፊት ስለዚያ ሰው ምን ማወቅ ይኖርብኛል?

ውድ ዶሪን፥

ማግባት ለአንቺ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ብቻ አድርገሽ አታስቢ። «ባላገባ ክርስቶስን በተሻለ መልኩ ማገልገል እችላለሁን? ወይስ አግብቼ ከባለቤቴ ጋር ክርስቶስን በጋራ ማገልገል ይኖርብኝ ይሆን?» ብለሽ ራስሽን ጠይቂ (1ኛ ቆሮንቶስ 7፡32-35 ተመልከቺ)።

እንድታገቢ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ከተረዳሽ ደግሞ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለራስሽ አቅርቢ። ይህም ለጋብቻ ስለሚጠይቅሽ ማንኛውም ሰው ነው።

1) እግዚአብሔርን የሚወድድና የሚያገለግል እውነተኛ ክርስቲያን ነውን?

2) የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ አለውን?

3) ምን ያህል ራስ ወዳድ ነው?

4) ለዘመዶቹና ለባልንጀሮቹ ክርስቶስን እንደሚወድድ የመንገር ድፍረት አለውን?

5) ገንዘቡን በሙሉ ለራሱ ይጠቀምበታል ወይስ አብዛኛውን እግዚአብሔርን ለማገልገል ያውለዋል?

6) ባለቤቱ ልጅ ባትወልድለት እንኳ ከፍቺ ይልቅ በጋብቻ አብሮ መኖርን ይመርጣል?

7) ችግር በሚገጥመው ጊዜ በእግዚአብሔር ይታመናል ወይስ ሙታንን ወደሚጠሩ መናፍስት ሳቢዎች ይሄዳል?

8) ጠጪ ነው? ሚስቱን ለመምታት ይከጅላል?

9) ከሌሎች ልጃገረዶች ጋር ለመውጣት «እንቢ» ይላልን? (ከጋብቻ በፊት ከማንኛውም ሴት ጋር ለመውጣት «እንቢ» የማይል ከሆነ በጋብቻም ውስጥ ታማኝነቱን እንደሚያጎድል ይገመታል።) [ገጽ156-159]

ሣራ፡— ራሴን ለመግደል እፈልግ ነበር፤ ዛሬ ግን ከመጋቢያችን ባለቤት ፍቅር የተሞላበትን ደብዳቤ ተቀበልኩ። እናም ለሌሎች ወጣቶች ታቀርቡት ዘንድ የደብዳቤውን ቅጂ ልኬላችኋለሁ።

**የመጋቢው ሚስት ደብዳቤ የሚከተለው ነው።**

ተወዳጅዋ ሣራ፥

ልጄ ሆይ፥ እንደምወድሽ ታውቂ ዘንድ እወዳለሁ። ልጃገረዶች ሊያደርጉት አይገባም ያልኩሽን ነገር ብትፈጽሚም እንኳ አሁንም እወድሻለሁ።

ደብዳቤሽ በደረሰኝ ጊዜ አለቀስሁ። ከልጁ ጋር የግብረ— ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም በመስማማትሽ ምን ያህል እንዳዘንሽ አውቃለሁ። አርግዤ ይሆን በሚለው አሳብም ምን ያህል እንደፈራሽ ይሰማኛል።

*የሆነ ሆኖ፥ ሣራ እወድሻለሁ፤ እግዚአብሔርም ይወድሻል!* ኃጢአትን ሠርተሻል፤ ከኃጢአትሽ የተነሣም ወደ ገሃነም

መሄድ ይገባኛል። ሁላችንም ከኃጢአታችን የተነሣ ገሃነም ይገባናል። ነገር ግን ይህንን አንብቢ፡—

«. . . ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ» (1ኛ ቆሮንቶስ 15:3)።

« እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ» (ኢሳይያስ 53:5)።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ. . .» (ዮሐንስ 3:16)።

ልጂ ሆይ፡— እነዚህ ቁጥሮች የፈጸምሽውን ኃጢአት ዕዳ ክርስቶስ እንደ ከፈለ ያውጃሉ። አመኚው!

ይህንን ጸሎት እንጸልይ፡— «አባት ሆይ፥ አንተ ቅዱስ ነህ። ኃጢአትንም ትጸየፋለህ። ነገር ግን በጣም ስለምትወደን በእኛ ምትክ ይሠቃይ ዘንድ ክርስቶስን ላክኸው። ልጅህ ሣራ ንስሐ መግባትና በክርስቶስ ማመንን መርጣለች። እናም ይቅር እንድትላት እንጠይቅሃለን። በፊቷ ባለው ዘመን ወደ መሰል ኃጢአት እንዳትመለስና እንዳትወድቅ ሥጋዊ ፍላጎቷን መቆጣጠር ትችል ዘንድ እባክህ እርዳት። እርግዝም ከሆነ ልጅን በማሳደግ ሂደት በምትጋፈጠው ችግር ሁሉ አንተ አብረሃት ትሆናለህ። የኢየሱስን መሥዋዕትነት በማመናችን ብቻ ስለ ሰጠኸን የዘላለም ሕይወት እናመሰግናለን! አሜን።

የተስፋ ቃል ለሣራ፡—
«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡—
ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ፤
በስምህም ጠርቼሃለሁ፥
አንተ የእኔ ነህ»
(ኢሳይያስ 43:1)።

አቤሴሎም፡— ዕድሜዬ 24 ሲሆን ሴት ጓደኛዬ ደግሞ 22 ዓመቷ ነው። በሚቀጥለው ዓመት ለመጋባት ዐቅደናል። ሁለታችንም ደናግል ነን። እስከ ሠርጋችን ቀን ድረስ እንዲሁ በመቆየት ጌታችንን ለመታዘዝ እንፈልጋለን።

አሁን ችግራችን በተገናኘን ቁጥር ሰዋራ ስፍራ መፈለጋችን ነው። ከዚያ በኋላ እንሳሳማለን፤ ጡቶቿን አሻሽላታለሁ፤ አንዳችን የሌላችንን የጾታ ብልቶች እንነካካለን።

በሚቀጥለው ቀን ከፍተኛ የበደለኝነት ስሜት ይሰማናል። ስለሆነም በጸሎት ከእግዚአብሔር ይቅርታ እንጠይቃለን። ከዚያ በኋላ እርግፍ

አድርገን እንተወዋለን. . . ለጥቂት ቀናት. . . ከዚያ እንደገና ያንኑ ነገር ስንፈጽም ራሳችንን እናገኘዋለን።

ይህንን ስናመዛዝነው እስከ ሠርጋችን ቀን ድረስ ደናግል ሆነን መቆየት መቻላችንን እንጠራጠራለን።

ውድ አቤሴሎም፥

ጋብቻ ወዳጅነት ነው። ስለሆነም ለራስህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማቅረብ ይኖርብሃል። «ይህች ልጃገረድ የእኔ የቅርብ ወዳጅ መሆን ትችላለችን? አብረን ስንንሸራሸርና ነፃ ሆነን ስንነጋገር ደስተኞች ነንን? ደስታና ኀዘኔን ነፃ ሆኜ ልነግራት እችላለሁን? እርስዋስ ጥልቅ ስሜቶቿን ለእኔ በነጻነት ማካፈል ትችላለችን? እግዚአብሔርን አብረን በማገልገል ደስ ይለናልን? የቅርብ ወዳጄ እርሷ ናትን?»

በመሳሳምና በመተሻሸት የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ በጭራሽ ማግኘት አትችልም። በእውነቱ ከሆነ ወዳጅነት የሚጎለብተው አንድ ወጣትና አንዲት ልጃገረድ የማይነካኩ ከሆነ ነው።

ስለሆነም አቤሴሎም ማስታወሻ እንድትጽፍላት አሳባችንን እናካፍልሃለን። እንዲህ የሚል ሊሆንም ይችላል።

> *ወዳጅነታችን እንዲያድግ ዕድል እንስጠው።በምሥጢር በመገናኘት ፈንታ ብርድ ልብስና ምግብ የመሳሰሉትን በማደል መበለቶችን ከሚያገለግሉት ወጣቶች ጋር እንቀላቀል።*

ኤልሳቤጥ፦ ሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ አንዲት ጓደኛዬ ስለ ዘላለም ሕይወት ነገረችኝ። እኔም ጌታን በመቀበል ልከተለው ወሰንኩ። በሚቀጥለው ዓመት ወደ ሌላ ትልቅ ዩኒቨርሲቲ ተዛወርኩ። በዚያም ተማሪዎች በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ምን እንደምሠራ ጠየቁኝ።

እኔም «አልጠጣም፤ ለኢየሱስ እኖራለሁ» አልኳቸው።

ከእነርሱም ብዙዎቹ ጌታን እንደሚወድዱ በተረዳሁ ጊዜ በጣም ደስ አለኝ! በአምስት ዓመት የዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ «አላጨሁም»። ይልቁንም ለእግዚአብሔር ይህን ነገርኩት። «እንዳገባ የምትወድድ ከሆነ እባክህ ትክክለኛውን ሰው አገናኘኝ።» ደግሞም እንዲህ ስል ቃል ገባሁኝ፤ «እስከማገባ ቀን ድረስ ማንንም ወንድ ለመሳም እንኳ አልፈቅድም።»

አንድ በጣም የምወደው ሰው ነበር። እርሱ እግዚአብሔር ለእኔ የመደበው ሰው እንደሆነ በምሥጢር ተስፋ ሳደርግ ቆየሁ። ቆይቶ ግን አንድ ቀን «ሌላ ሴት ላገባ ነው» የሚል ደብዳቤ ጻፈልኝ።

ደጋግሜ አለቀስሁ። እንደዚያም ሆኖ በልቤ ሰላም ነበረኝ። እግዚአብሔር እረኛዬ እንደሆነና እንደሚመራኝም አውቃለሁና።

ከስድስት ወራት በኋላ ከኢዩኤል ጋር ተዋወቅሁ። ወዳጅነታችን ቀስ በቀስ ነገር ግን በአስገራሚ ሁኔታ አደገ። እንዴት ያለ ብርቱ ክርስቲያን ነው!

አንድ ቀን ኢዩኤል እንዲህ አለኝ። «ልነግርሽ የሚገባኝ ነገር አለ። እስከ ጋብቻዬ ቀን ድረስ ማንኛዋንም ልጃገረድ እንደማልስም ለእግዚአብሔር ቃል ገብቻለሁ።»

እኔም እንዲህ መለስኩለት። «እኔም ልነግርህ ይገባኛል። እስከ ሠርጌ ቀን ድረስ ማንኛውም ወንድ ላለመሳም ለእግዚአብሔር ቃል ገብቻለሁ።»

በደስታ ሣቅን። እግዚአብሔርን አመሰገንን። ከዚያ በኋላ ኢዩኤል እንዲህ አለኝ። «ደስ እያለኝ ቃልሽን እንድትጠብቂ እረዳሻለሁ።»

ፈጸመው!

ከአራት ዓመታት በፊት ተጋባን። አሁን የሁለት ዓመት ሴትና ትንሽ ወንድ ልጆች አሉን።

ኢዩኤልና እኔ አንዳንዴ እንጋጫለን። (የተጋቡ ሁሉ የዚህ ዓይነት ችግር እንዳለባቸው አምናለሁ።) ነገር ግን አንዳችን ለሌላችን ያለን ፍቅር አልቀነሰም። እንዴት ያለ ጣፋጭ ደስታ እንጋራለን!

አሁን ቤተ ክርስቲያናችን እኛንና አንድ ሌላ ቤተሰብን ለወንጌል ስርጭትና ለቤተ ክርስቲያን ተከላ ተግባር ወደ ሞዛምቢክ ልትልከን ነው። ይህ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ግን የተወደደው ጌታችን ከእኛ ጋር ይሆናል።

ውድ ኤልሳቤጥ፥

አበረታች የሆነው ደብዳቤሽ የሚቀጥለውን ጥቅስ አስታወሰን።

«የሠራዊት አምላክ ሆይ፥ በአንተ የታመነ ሰው

ምስጉን ነው» [መዝሙር (84)፡12]።

ሴም፡— ከሁለት ሳምንት በኋላ የምታምር ክርስቲያን ልጃገረድ አገባለሁ። አሁን በጣም የምወዳት ቢሆንም ምናልባት ከጥቂት ዓመታት በኋላ ፍቅሬ እንዳይጨለጥ ጨንቆኛል።

ውድ ሴም፥

እንዲህ ዓይነቱ ጭንቀት ሊከብህ አይገባም። በፈለግህ ጊዜ ሁሉ መውደድ ትችላለህ። ፍቅር ምርጫ ነው።



እግዚአብሔር «ፍቅር እንዳይሟጠጥ ሞክር» ብሎ አያውቅም። ይልቁንም «ሚስትህን ውደድ» ይላል። ስለሆነም በምታገባ ጊዜ በየዕለቱ ሚስትህን ለመውደድ መምረጥ አለብህ።

**ፍቅር፡—** «ሚስትህን ውደድ» ማለት

✓ልጆቿን ስትንከባከብ እርዳት።

✓እንደ ጓደኛ አነጋግራት፤ ችግሮቿን አድምጥ።

✓ከራስህ አስቀድመህ የእርሷን ፍላጎቶች አስብ።

✓ገንዘብህን በደስታ ከእርሷ ጋር ተካፈል።

✓በቤት ውስጥ ዝም ብለህ በምቹ ወንበር ላይ በመቀመጥ ፈንታ ተነሥተህ በሥራ አግዛት።

ሴም የአንተ ችግር ይህ ነው። ፍቅር ምን እንደሆነ አታውቅም። ፍቅር ስሜት ብቻ እንደሆነ ስለምታምን ያ ስሜት እንዳይጠፋ ትፈራለህ።

እውነቱ ግን፡—

**ፍቅር** ስሜት አይደለም።

**ፍቅር** ድርጊት ነው!

«ሚስትህን ውደድ» የሚለው ትእዛዝ ስለ ስሜት አይደለም።

ነገር ግን *የድርጊት* ትእዛዝ ነው።

ስሜቶችህን መምረጥ አትችልም።

*የምታደርገውን* ግን መምረጥ ትችላለህ።

ፍቅርህን የሚገልጥ ነገር ለሚስትህ ብታደርግላት

ያንንም በየዕለቱ፥ ከዓመት ወደ ዓመት. . . ሞት እስኪለያችሁ ድረስ ብትቀጥል

ጋብቻህ ደስታ የሞላበት ይሆናል።

*ስሜቶች፡—* የፍቅር ስሜት እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው። ሁላችንም ይህ ስሜት በየዕለቱ እንዲኖረን እንወዳለን። ነገር ግን ስሜቶች ይነሣሉ፤ ይወድቃሉ። በመልካም ጋብቻ ውስጥ እንኳ ስሜቶች አንድ ቀን ከፍ በሌላው ቀን ዝቅ. . . ከፍ. . .ዝቅ. . . የሚሉ ናቸው።

ሴም፥ እባክህ በሚቀጥለው ዓመት ጻፍልን። በደብዳቤህ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ነገር ሊኖር እንደሚችል ተስፋ እናደርጋለን።

ውድ ካሮልና ብሩስ

ብዙ ቀናት ልቤ ስለተወዳጇ ሚስቴ በፍቅር ስሜት ይሞላል። ከዚያ በኋላ ለእርሷ መልካም ነገር ማድረግ ቀላል ነው። ከርሷ ጋር ሳህኖችን ሳጥብ እንኳ በጣም ደስ ይለኛል።

ነገር ግን አንዳንድ ቀን በሥራ ቦታ በጣም ይደክመኝና በጣም ዝዬ ቤት እገባለሁ። በእነዚህ ቀናት ለሚስቴ የሚኖረኝ የፍቅር ስሜት አናሳ ነው። ያም ሆኖ ግን ምርጫዬ እርሷን ማፍቀር ነው! በርኅራኄ አነጋግራት ዘንድ እጨነቃለሁ። እናም ልጆቻችንን በማጠብ ብሎም በማስተኛት እረዳታለሁ።

ምንም ዓይነት ስሜት ቢኖረኝ ለሚስቴ መልካምን ለማድረግ እመርጣለሁ። ያን በማደርግ ጊዜ ደግሞ ስሜቶቼ እንደገና ለፍቅር መነሣሣት ይጀምራሉ።

ብዙ ወጣቶች ፍቅርን እንደሚገባ አይረዱትም። «ካገባሁ በኋላ በየዕለቱ በልቤ ውስጥ የፍቅር ስሜት ይኖረኛል፥ እነዚህ ስሜቶች ከጠፉ ግን ፍቅሬ ተሟጥጧል ማለት ነው። ያኔ መፍትኄው ፍቺ ነው» ብለው ያስባሉ።

እንዲህ ዓይነቱን እሳቤ የሚቀስሙት ከቴሌቪዥንና ከመጽሔቶች ነው።

ለእነዚህ ወጣቶች እንዲህ እንላቸዋለን። «ቴሌቪዥኑን አጥፉት፤ እነዚያን መጽሔቶችም ወደ ቆሻሻ መጣያ ወርውሯቸው። መጽሐፍ ቅዱስን አንብቡ! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ባልና ሚስት እንዲዋደዱ የሰጠውን ትእዛዝ ታገኛላችሁ። ስሜቶቻቸው ይሙቅ ወይም ይቀዝቅዝ ግን እንዲዋደዱ የግድ ነው!»

መጽሐፍ ቅዱስን የሚታዘዙ ባልና ሚስት በፍቅር የተሞላ ጋብቻ ውስጥ ይኖራሉ። ለምን? ምክንያቱም ስሜታቸው በቀዘቀዘ ዕለት እንኳ አንዱ ለሌላው በጎ ማድረግን ይመርጣሉ። ስለሆነም ስለ ፍቅር ያላቸው ስሜት ዝቅ እንዳለ አይቆይም።



መዋደድን እንመርጣለን

አበኔር፦ አንድ ጊዜ ካገባሁ በኋላ በሌሎች ሴቶች መስሕብ አልያዝም የሚል ተስፋ ነበረኝ። ግን ይህ እየሆነ ነው።

ብሩስ ጥሩ ሚስት ያለህ ቢሆንም እንኳ በሌሎች ሴቶች ተስበህ ታውቅ ይሆን?



ውድ አበኔር፥

አዎን፥ ብዙ ጊዜ «ብሩስ ያቺን ቆንጆ ሴት ተመልከት፤ እርሷን ማሸነፍ አለብህ» የሚል ስሜት ይሞላኛል።



ነገር ግን ያ ስሜት ውስጤን እንዲቆጣጠር አልፈቅድለትም። ራሴንም «ሚስቴን እስከ ሞት ድረስ ላፈቅራት ቃል ገብቻለሁ። ለሌላ ሴት ለተሰማኝ ስሜት ራሴን ካስገዛሁ የቤቴ፥ የባለቤቴና፥ የልጆቼ ጉዳይ እንዴት ይሆናል?» በማለት አሳስበዋለሁ።

አበኔር፡- ሌላ ሴት አይተህ ስታሰኝህ ሚስትህን ለመውደድ ምረጥ (ምሳሌ 5:18-21)።

## ፍቅር ምርጫ እንጂ ስሜት አይደለም!

ጋቪን፡- ከሁለት ዓመት በፊት ጌታን ተቀብዬ ነበር። ለጥቂት ወራት ጥሩ ክርስቲያናዊ ሕይወት ገፋሁኝ። ከዚያም ወደ ኋላ ተመልሼ ከልጃገረዶች ጋር ዝሙት መፈጸም ጀመርኩኝ። ዛሬ ግን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና ደግሜም ላልተወው ወሰንኩ። ግን ስጋት አለብኝ። እግዚአብሔር ይቅር ሊለኝ ይችላልን? መልሶስ ይቀበለኛል?

ውድ ጋቪን፥

ኢየሱስ ለምን ወደ ምድር መጣ? በአንተ ምትክ ሥቃይ መሸከምን ስለመረጠ ነው! ኢየሱስ ስለ አንተ ኃጢአት ሥቃይን እስከ ተቀበለ ድረስ አንተ ዳግም መሠቃየት የለብህም። ይቅርታን መቀበል ትችላለህ (ኢሳይያስ 53:5-6፤ ሉቃስ 15:11-32)።

ስለሆነም ተናዘዝ። ከዚያ በኋላ ኢየሱስ እንዳነጻህ እመን (1ኛ ዮሐንስ 1:8-10)።

አስታውስ፥ ኢየሱስ አዳኝ ብቻ አይደለም። *አዳኝና ጌታ ነው።* ጌታ እስከሆነ ድረስ ለእርሱ ታዘዝ! (1ኛ ዮሐንስ 2:1-6)።

**ይቅርታ በኃጢአት ለመቀጠል የሚረዳ ፈቃድ አይደለም። ይቅርታ በተለወጠ ሕይወት ጎዳና ስንጓዝ በንጽሕና የሚጠብቀን መታጠብ ነው።**

ኢየሱስ «ደሜ የሚፈስሰው ብዙዎች የኃጢአትን ይቅርታ እንዲያገኙ ነው» ብሎአል (ማቴዎስ 20:28)።

ጳውሎስም «በኢየሱስ በኩል ይቅርታን መቀበል እንደምትችሉ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ» ይላል (የሐዋርያት ሥራ 28:18)።

«ኃጢአቱን የሚደብቅ ሰው አይለማም። ቢናዘዝና ኃጢአት ማድረግን ቢተው ግን ምሕረትን ይቀበላል» (ምሳሌ 28:13)።

«በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም» (ሮሜ 6:1-2)።

«ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፥ አሮጌው ነገር አልፎአል፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17)።

ዲቦራ፦ እኔና ባለቤቴ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በርትተን እናገለግላለን። እርሱ ዲያቆን ሲሆን እኔ ደግሞ የሴቶች ኅብረት ጸሐፊ ነኝ።

ዓርብ ከሰዓት በኋላ ወደ ቤቴ ስገባ የልጆቻችን ሞግዚት እያለቀሰች ወደ እኔ መጣች። ባሌ እንዴት ከእርሷ ጋር እንደ ተኛ ስትነግረኝ እኔም ራሴ አለቀስሁ።

ያቺን ልጃገረድ በቀጥታ ወደ መጋቢያችን ወሰድኋት። የሆነውንም ነገረችው። በዚያው ምሽት ባለቤቴን አነጋገረው።

አሁን ባለቤቴ ኃጢአቱን በቤተ ክርስቲያን ፊት ተናዝዟል። ከእኛ ጠና ያሉ ባልና ሚስት በየእሑዱ ለአንድ ዓመት ያህል ምክር እያካፈሉን ነው። እናም በዚሁ ዓመት ባሌ በመሪነት አያገለግልም።

ችግሬ የሚከተለው ነው። አንዳንድ ሴቶች እንዲህ ይላሉ።

«ዲቦራ ግን ለምን ለመጋቢው ነገረች? ትዕግሥተኛ መሆን ነበረባት። ባሎች እንደሆነ ታማኞች አይደሉም?»

ብሩስና ካሮል፡ ነገሩን ማሳወቁ ጥፋት ነበረን?

ውድ ዲቦራ፥

ነገሩን ማሳወቅሽ መልካም ነው። እንዲህ የሚሉት ሴቶች ተሳስተዋል። ክርስቲያን ወንዶች ታማኝ መሆን አለባቸው። እናም ከእነርሱ አንዱ በዝሙት ከወደቀ ቤተ ክርስቲያን በሥነ ሥርዓት ልትቀጣው ይገባል (ማቴዎስ 18፡15–17)።

ከእናንተ ጠና ያሉት ባልና ሚስት እያማከሯችሁ በመሆኑ ደስ ብሎናል። ምክራቸው የሚከተሉትን ለመፈጸም እንዲረዳችሁ እንጸልያለን።

ሀ) ባልሽን ይቅር ትዪው፥ ትወጂውና ታከብሪው ዘንድ።

ለ) ባልሽ ከዚህ በኋላ ታማኝ ይሆን ዘንድ (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡11)።

ሐና፡— ከዓመታት በፊት ባሌ እኔን በመተው ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ገባ ወጣ ማለት ጀመረ። እርሷም በየዕለቱ እኔን እንዲፈታ ትነዘንዘው ነበር።

ቀስ በቀስ ወራት ተቆጠሩ። . . . አስቸጋሪና አስፈሪ ጊዜያት ነበሩ። ለባለቤቴ ስልክ በደወልኩ ቁጥር ስልኩን አንሥታ የምታናግረኝ እርሷ ነበረች። ትስቅብኛለች፤ ደግሞም እንዳነጋግረው አትፈቅድልኝም።

«ባለቤቴ አይወደኝም. . . ማንም የሚወደኝ የለም!» እያልኩ ለራሴ እነግረው ነበር። ሆኖም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ በእግዚአብሔር እንድታመን ረዳኝ። ደግሞም የቤተ ክርስቲያኔ አባላት የሆኑ እኅቶች አበረታቱኝ።

ከአንድ ዓመት በኋላ ባሌ ተመልሶ ወደ እኔ መጣ!

እግዚአብሔርም እጆቼን በፍቅር ዘርግቼ እንድቀበለው ረዳኝ።

ከቤተ ክርስቲያን የምክር አገልግሎትና ተግሣጽን ለመቀበል በጣም ተቸግሮ ነበር። አሁን ግን ትዳራችን በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል።

ልፈታው ባለመከጀሌ እንዴት ደስተኛ ነኝ!

> ማስጠንቀቂያ ለወጣት ወንዶች፡— እግዚአብሔር ይቅር ይላል፥ ሆኖም የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት በሚስትህ፥ በቤተ ክርስቲያንህና በራስህም ሕይወት ላይ የቀናት፥ የዓመታትና የወራትን ኀዘን ያስከትላል (ገላትያ 6፡7)።

ናታን፡— ሚስት እየፈለግሁ ነው። በየዕለቱ ራሴን እንዳሻሽል እንዲረዳኝ እግዚአብሔርን እጠይቀዋለሁ። (ብዙ ላሻሽላቸው

የሚገቡ ጎኖች አሉኝ) ይህም አንድ ሴት ልታገባው የምትመኘውን ዓይነት ወንድ እንድሆን ነው።

አሁን ጥያቄዬ ማንን ላግባ የሚል ነው። እውነተኛ ክርስቲያን የሆኑ በርካታ ልጃገረዶች አውቃለሁ። ለመለከታቸው የሚገቡ ሌሎች ብቃቶች የትኞቹ ናቸው?

ውድ ናታን፥

ወጣት ሳለሁ እኔ በጽሑፍ ያዘጋጀሁት ዝርዝር የሚከተለው ነው።

**በእግዚአብሔር ድጋፍ ሚስቴን ለመምረጥ ስሞክር ስለ እርሷ እንዲህ ለማለት የምችለውን ልጃገረድ እሻለሁ።**

ሀ) ለወንዶች ጥያቄ «አይሆንም» የምትል።

ለ) አጣብቂኝና ወንዶችን የሚፈትን አለባበስ የማትመርጥ።

ሐ) በሆስፒታል ከሚመለከረው ቡድናችን ጋር በደስታ ለማገልገል የምትመርጥ።

መ) ውድ የቤት ዕቃዎችን ከመሸመት ይልቅ በወንጌል ስርጭት መጠመድን የምትወድድ፤ ከገንዘብዋ ቢያንስ 1/10ኛውን ለቤተ ክርስቲያን የምትሰጥ።

ሠ) የጎዱትን ሰዎች ይቅር የምትል።

ረ) እኔ ከእርሷ ጋር ሳወራ ደስ እንደሚለኝ እርሷ ከእኔ ጋር በማውራት ደስ የምትሰኝ፤ የቅርብ ወዳጄ ልትሆን የምትችል።

ሰ) ከእኔ ጋር አብራ መጸለይን የምትወድድ።

ሸ) ብዙ ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ እምብዛም ደስ የማትሰኝ፤ ቢያስፈልግ ሥራዋን ትታ ከቤት በመዋል ልጆቻችንን መንከባከብ የምትችል።

ቀ) ለእንግዶች የሚያስፈልገውን ማዘጋጀት ደስ የሚላት፤ ከተጋባን በኋላ ያልዳኑ ጎረቤቶቻችንን በቤታችን የምትቀበልና በመጽሐፍ ቅዱስ ዙሪያ የምታወያይ።

ናታን፡— የእኔን ዝርዝር መገልበጥ የለብህም። የራስህን አዘጋጅ። በአንተ ዝርዝር ላይ አስፈላጊ መስሎ የሚታይህን ማንኛውም ነገር አክልበት።

ግን ይህንን አስታውስ፥ ከሠርግህ ቀን በኋላ ሁልጊዜም ሚስትህ ያኖርከውን መስፈርት ማሟላት በሚሳናት ወቅት እንኳ በፍቅር የምትታገሥ መሆን አለብህ።

«ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል (ይቅር ይላል፥ ይተዋል)» (1ኛ ጴጥሮስ 4፡8)።

ቪንሰንት፡— የቤተ ክርስቲያናችን አባል በሆነችውና በውብ ልጃገረድ ሩት ፍቅር ተነድፌያለሁ። ባየኋት ቁጥር የልቤ ምት በመጨመር ሊፈንዳ ይደርሳል።

እናቴ ሁልጊዜ «ስሕተት ላይ እንደማትወድቅ አምናለሁ» ትለኛለች። (ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ማለቷ ነው)። ደግሞ እንዲህ ትነግረኛለች። «ልጄ ሆይ፡- የሴት ጓደኛ ለመያዝ ገና ወጣት ነህ፤ በሳል ዕድሜ ላይ እስክትደርስ ቆይ።»

ዕድሜዬ ወደ 17 እየተጠጋ ነው። በሚቀጥለው ዓመትም ዩኒቨርስቲ ለመግባት ተስፋ አደርጋለሁ። ክርስቲያን ከመሆኔም በላይ እናቴን ለመታዘዝ እፈልጋለሁ። ግን የልቤ ምት ይህ ነው። ሩት፥ ሩት፥ ሩት፥ ሩት፥ ሩት።

ውድ ቪንሰንት፥

ያለህበት ዕድሜ ወንድ ልጅ በቀላሉ በልጃገረዶች የሚማረክበት ነው። በተለይም በአንዲት ልጃገረድ መማረክህ አስደናቂ አይሆንም።

ያም ሆኖ ግን እኛ በእናትህ አሳብ እንስማማለን። አንድ ወጣት በአንዲት ልጃገረድ ላይ ፍቅሩን ከመጣሉ በፊት «መብሰል» ይገባዋል።

አንድ ሰው «በሳል» ነው የሚባለው፡—

- የጎዱትን ይቅር ማለት ሲችል።
- ከራስ ወዳድነት ነፃ ሲሆን።
- «ተሳስቻለሁ፤ ይቅርታ» ለማለት ፈቃደኛ ሲሆን።
- ሥራ መያዝና ልጆችን መርዳት ሲችል።
- ገንዘብ መቆጠብና በአግባቡ መጠቀምን ሲያውቅ ነው።

ስለዚህ አስብ። ቪንሰንት፡— በሳል ነህን?

ክርስቲያን እንደ መሆንህ መጠን መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ እየሠራ ወደ ብስለትም እንድታድግ እየረዳህ ነው። ግን ወደ ብስለት ማደግ ጊዜን ይወስዳል (ያዕቆብ 1፡2-4)።

ስለሆነም በአንተ ዕድሜ ላሉ ወጣቶች ምን ጊዜም ይህን እንነግራቸዋለን።

*አትቸኩሉ። በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት አንዲትን ልጃገረድ የሙጥኝ ከማለት ይልቅ ሁሉንም እንደ እኅቶቻችሁ አቅርባቸው። በቤተ ክርስቲያን ሥራዎች ውስጥ ክርስቶስን በጋራ በማገልገል በምታዳብሩት ወዳጅነት ደስ ተሰኙ (1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡1-2)።*

*ዕድሜያችሁ ከፍ ካለና ጊታም በብስለት ለማደግ ከረዳችሁ በኋላ ወደ አንዲት ልጃገረድ የተለየ ዝንባሌ ለማሳየት ዝግጁ ትሆናላችሁ።*

የልቤ ምት «ሩት፡ ሩት፡ ሩት፥ ሩት፤ ሩት!» የሚል ሆኗል ብለሃል። ይሄ ይገባናል። ግን አሁንም የምንልህ «ገና ልጅ ነህና እርሷን የሙጥኝ አትበል» ነው። ይህ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፤ ግን ልታደርገው ትችላለህ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ (ወደ ብስለት ስትጠጋ) ምናልባት የምትስብህም ሆነ ልታገባት የምትፈልገው ሩትን መሆኑን ልትወስን ትችላለህ።

ለጊዜው ግን ዝም ብለህ በቤተ ክርስቲያን ካሉ ወጣቶች ጋር እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ አገልግል።

ፓትሪክ፡— ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ በማስተማር ሥራ ላይ የተሰማራሁና የ26 ዓመት ወጣት ወንደ ላጤ ነኝ።

ከሁለት ወራት በፊት አንዲት ደስ የምትል ሴት ወይዘሮ በትምህርት ቤታችን ሥራ ጀመረች። ስሟ ሚርየም ሲሆን እኔ በማመልከበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታመልካለች።

ከእርሷ ጋር ለመነጋገር ሰፊ ዕድል አላገኘሁም። ነገር ግን ከፉኛ አፍቅሬአታለሁ።

እንዴት እንደምወድዳት አሁኑኑ ልንገራትን?

ውድ ፓትሪክ፥

ዕድሜህ ትንሽ አይደለም፤ ስለዚህ በሳል ነህ ብለን እናምናለን። ነገር ግን «እወድሻለሁ» ለማለት ከክጀልክ በጣም ትፈጥናለህ። ለምን? የሚል ጥያቄ ቢፈጥርብህ ምክንያቱም የምታውቃት ለጥቂት ጊዜ ነው። በዚያ ላይ እርሷን ለማነጋገር ያገኘሃቸው ዕድሎች በጣም ጥቂት ናቸው። ስለሆነም የአንተ «ፍቅር» ሲመዘን «በሚገባ መተዋወቅ» የሚለውን መስፈርት አያሟላም። (ገጽ 29)

ምናልባትም ከስድስት ወራት በኋላ «አሁን በተሻለ መልኩ አውቄያታለሁ፤ የእኔ እንዳልሆነችም ተረድቻለሁ» ብለህ ታስብ ይሆናል።

ወይም . . . ምናልባት ከጥቂት ወራት በኋላ «ሚርየምን ከራስ ወዳድነት በጸዳ መልኩ በእውነት ወድጄያታለሁ» ወደሚል መረዳት ትመጣ ይሆናል። ያኔ እንደምትወድዳት ልትነግራት ትችል ይሆናል።

አሁን ግን ስለ መውደድህ አትናገር፤ ቸኩለሃል።

ዳዊት፡— ወደማገባት ልጃገረድ ይመራኝ ዘንድ እግዚአብሔርን ጠየቅሁት። ቆይቼም የቤተ ክርስቲያኔ አባል የሆነች አንዲት

ልጃገረድ አፈቀርሁ። ሆኖም ስለዚህ ጉዳይ ለእርሷ አልነገርኳትም። የያዘኝ ፍቅር እናንተ ያስተማራችሁንን «የፍቅር መመዘኛዎች» ያልፍ እንደሆነ ለማወቅ መቆየትን መረጥኩ። (ገጽ 25-32)።

እንዳለመታደል ሆኖ ሌላ ሰው ጠለፋት። ያውቃት ዘንድ ጊዜ ከመውሰድ ይልቅ ፈጥኖ እንዲህ ይላት ጀመር «እወድሻለሁ፥ ላገባሽም እፈልጋለሁ።»

ትናንትና እንደምታገባው ቃል ገባችለት።

ልቤ ክፉኛ አዘነ!

እንዲህ ዓይነት ነገር ሲገጥመኝ ደግሞ ይህ ሁለተኛ ጊዜ ነው።

በሚቀጥለው ጊዜ አንዲት ልጃገረድ ከወደድኩ ወዲያውኑ ብነግራት የተሻለ አይሆንምን? ይህንንም ስል ትንሽ ፈጠን ባደርገው አይሻልም ወይ? ለማለት ነው።

ውድ ዳዊት፥

አይሆንም፤ አትችኩል። መጽሐፍ ቅዱስ ባልና ሚስት «ይጣበቃሉ» ይላል። ይህም ማለት የቅርብ ወዳጆች መሆን አለባቸው ማለት ነው። ስለሆነም አንዲትን ሴት ለማግባት ከመወሰንህ በፊት ወዳጅነታችሁ ያድግ ወይም አያድግ እንደሆነ ጊዜ ወስደህ ልብ ማለት ይኖርብሃል።

በሁሉም አብያተ ክርስቲያን ወጣቶችና መሪዎቻቸው በአንድነት ተሰብስበው በአንድ ጥያቄ ላይ መምከር አለባቸው። ይኸውም *አንድ ወጣት ሴቷን «እወድሻለሁ» ከማለቱ በፊት እርሷን ለማወቅ ምን ያህል ጊዜ መታገሥ ይገባዋል የሚለው ነው።*

ከዚያ ውይይት ወጣት ሴቶች ምናልባትም እንዲህ የሚሉ ወጣቶች ወንዶችን ልብ ይሉ ይሆናል።

«ሚስቴ የቅርብ ወዳጄ መሆን እንዳለባት ተገንዝቤያለሁ። ስለሆነም ለአንዲት ልጃገረድ እንደምወዳት ከመንገሬ በፊት ወዳጅነታችን የሚያድግ መሆኑን ጊዜ ወስጄ ማረጋገጥ አለብኝ።»

ዳዊት ይህች ልጅ ሌላ ሰው ለማግባት በመወሰኗ ምን ያህል እንዳዘንክ ይሰማናል። ነገር ግን ደብዳቤህን ስትጀምር «እግዚአብሔር እንዲመራኝ ጠየቅሁት» በማለት እንደሆነ ልብ ብለናል። *ታዲያ* አሁን እርሱ እንደሚመራህ ስለምን ተጠራጠርክ?

ከዚያች ልጃገረድ *ትርቅ* ዘንድ ይህ አንተን የመራበት አኳኋን ሊሆን አይችልምን?

እግዚአብሔር አሁን ድረስ አይወድህምን? *ትክክለኛዋ* የአንተ ጓደኛ እንድትወስድብህ ከቶም እንደማይፈቅድ ማመን አትችልምን?

ዳዊት፥ እንዲህ ብቻ አድርግ። ቅድስና የተሞላበት ሕይወት እየኖርክ በእግዚአብሔር ታመን። ሕይወት ቀና ስትሆንልህ ታመነው፤ ሕይወት አቀበት ስትሆንብህም ታመነው። እርሱ ለአንተ የተሻለ ዕቅድ አለው (ኤርምያስ 29፥11)።

ዴኒስ፡— እግዚአብሔርን እወዳለሁ፤ ከማንም ጋር ፍትወተ-ሥጋ ፈጽሜ አላውቅም። አሁን ሚስት ለማግባት እየከጀልኩ ነው። ሦስት ደስ የሚሉኝ ልጃገረዶች አሉ። አንዷ ጎረቤቴ ስትሆን ሁለቱ በኮሌጅ አብረውኝ ይማራሉ። ከእነዚህ የትኛዋ ለእኔ የሕይወት ዘመን አጋር/ወዳጅ እንደሆነች ለማወቅ እያንዳንዳቸውን ለማጥናት እየሞከርኩ ነው።

ከአንድ በላይ በሆኑ ልጃገረዶች በመሳቤ ተሳስቼ ይሆን? ከእነርሱ አንዷን ሚስቴ እንድትሆን ብጠይቅ ሌሎቹ ኀዘኔታ ይሰማቸዋልን?

ውድ ዴኒስ፥

ለእያንዳንዷ ልጃገረድ ታማኝ ሁን። ማንኛዋም ልጃገረድ ከሌሎቹ ይልቅ ወደ እርሷ እንዳተኮርክ እንዳታስብ ተጠንቀቅ። ልጅቱ ከምትወድዳቸው ልጆች አንዱ ከሆነች «ለእኔ የምትሆኚኝ ብቸኛ ሴት አንቺ ነሽ» አትበላት።

ወጣቶች ታማኝነት ካላሳዩ ሌላው ሰው መጎዳቱ አይቀርም። ለምሳሌ ያህል ኢያሱ ሻሮንን አይወዳትም ነበር። ነገር ግን እንደሚወዳት አስመስሎ የተሳሳተ ስሜትን አሳደረባት። በመጨረሻ ግን «አላገባሽም» ብሎ ሲነግራት አምርራ አለቀሰች።

በዚህ ምድር ኀዘንን ሁሉ ልናስወግድ አንችልም። አንዲት ልጃገረድ አላገባህም ብትለው ወንዱ ተስፋ ሊቆርጥ ይችላል። አንድም የሚጠይቃት ወንድ ያላገኘች ወጣት ደግሞ ተስፋ ልትቆርጥ ትችላለች። ታማኝነታችንን ለመጠበቅ ከተጠነቀቅን ግን የሚከሰተው ተስፋ መቁረጥ አደገኛ አይሆንም።

በርናርድ፡— በእኛ ቤተ ክርስቲያን አንድ ወንድ ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ሲያወራ ከታየ ወደ ኃጢአት ሊወስዳት ነው ብለው ብዙዎች ያስባሉ። ታዲያ አንዲትን ልጃገረድ እንዴት አድርጌ ላጠናት እችላለሁ? እባካችሁ እርዱኝ። ጌታን እወዳለሁ፤ ሚስትም እፈልጋለሁ።

ውድ በርናርድ፥

«ሚስት እፈልጋለሁ» በሚለው ላይ ከማተኮር ይልቅ «እንዴት በተሻለ መልክ እግዚአብሔርን ማገልገል እችላለሁ?» በል።

«ጌታን እወዳለሁ» ብለሃል፡፡ ስለዚህ አገልግለው፡፡

«አንተ ጌታዬ ነህ፤ ፈጽሞ ሚስት ባትሰጠኝም እንኳ አንተን አገለግልሃለሁ» በልና ንገረው፡፡

ከዚያም አንድ ቡድን ለማዋቀር የቤተ ክርስቲያንህን መሪዎች ጠይቅ፡፡ ያም ቡድን፡-

በእስር ቤቶች ወንጌልን የሚያሰራጭ፥

ወይም መበለቶችና ዕጓለ-ማውታን የሚረዳ፥

ወይም ወንጌልን ወደ ሌሎች አገሮች የሚያዳርስ ሊሆን ይችላል፡፡

እርሱን በማገልገል ስትጠመድ አንዲትን ወጣት ሴት ወደ ሕይወትህ እያመጣ እንዳለ ልትገነዘብ ትችል ይሆናል፡፡ ከዚያ በኋላ ሰዎች ከፉ አሳብ እንዳለህ በማይጠረጥሩበት አኳኋን ልታጠናት ትችላለህ፡፡

የቤተ ክርስቲያንህን መሪዎች አክብር፡፡ «አንዲት ልጃገረድን ለማጥናት የሚሞክርን ወጣት ምን እርምጃ እንዲወስድ ትመክሩታላችሁ?» ብለህ ጠይቃቸው፡፡ ስለ ጉዳዩም አብረሃቸው ጸልይ፡፡

ሲልቪያ፡- በቤተ ክርስቲያኔ ያሉ ወንዶችን ላያቸው የሚገባኝ እንደ አናብስት ነው ወይስ እንደ ወንድሞች? ፈጽሜ ልዝጋቸው ወይስ ላነጋግራቸው ለማለት ፈልጌ ነው፡፡

ውድ ሲልቪያ፥

መጽሐፍ ቅዱስ «. . . ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፥ የሸመገሉትን ሴቶች እንደ እናቶች፥ ቆነጃጅቱን፥ እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው» ይላል (1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡1-2)፡፡

ሮዳ፡- በቅርቡ አንድ ወጣት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀላቀለ፡፡ ዛሬ «ስለ ሚስት እየጸለይኩ ሳለ እግዚአብሔር በራእይ አንቺን አሳየኝ!» በማለት አስገረመኝ፡፡

ምን ልመልስለት እችላለሁ? እርሱን በሚገባ አላውቀውም፡፡ ግን «አይሆንም» ለማለት ፈራሁ፡፡

ውድ ሮዳ፥

ተጠንቀቂ! ሰውየው ለራሱ እንዲህ ብሎ ይሆናል፡፡




«እግዚአብሔር አሳየኝ» ለሚል ሰው የእሺታ ምላሽ ለመስጠት አትቸኩዪ።

«ጋብቻ በፍቅር ላይ የተመሠረተ ወዳጅነት ነው፤ አንድን ሰው ለማግባት ከመስማማቴ በፊት ወዳጅነታችን አዳጊ እንደሆነ ጊዜ ወስጄ ማየት ይኖርብኛል» ብለሽ ንገሪው። (ገጽ 22-34 ተመልከቺ።)

> ማስታወሻ ለወንዶች፦ አንዲትን ልጃገረድ ለጋብቻ ስትጠይቁ «እግዚአብሔር ተናገረኝ» አትበሉ። ይልቁንስ በቀጥታ ጠይቋት። እንቢ ብትልም አትጨነቁ። እግዚአብሔር ለእናንተ የተሻለ አሳብ እንዳለው እመኑ።

ሩት፦ ድንግልና ያለኝ የ18 ዓመት ወጣት ነኝ። ከ5 ዓመታት በፊት ኢየሱስን እንደ ግል አዳኜና ጌታዬ ተቀበልኩ። የኃጢአቴን ዋጋ እርሱ እንደከፈለ አምናለሁ። ግን አሁን ወደ ገሃነም የምሄድ እየመሰለኝ ሁልጊዜ እፈራለሁ። መጋቢያችን በቤተ ክርስቲያን ካገለገለ በኋላ ሰዎች ወደፊት እንዲመጡና ጌታን እንዲቀበሉ ሲጋብዝ እወጣለሁ። በየእሑዱ ከፊት ቆሜ ሳለቅስና ኃጢአቴን ስናዘዝ ሲያዩኝ ሰዎች ይገረማሉ።

ዛሬ ከእኅቴ ጋር አስፈሪ ክርክር ገጠምኩ። ፊትዋ በእንባ ታጠበ! በጣም ፈራሁ፤ እናም ይቅርታ ጠየቅኋት። ቀኑን ሙሉ እየደጋገምኩ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለኝ ስጠይቀው ዋልኩ። ነገር ግን እንደማያደምጠኝ ይሰማኛል።

ውድ ሩት፥

እግዚአብሔር ይቅር ብሎሻል፤ ይቅር እንዳለሽ «እንዲሰማሽ» መጠርሽን አቁሚ። ምንም «እንዲሰማሽ» አያሻም። ይቅር እንዳለሽ እግዚአብሔር ቃል ገብቷል። . . . ለምን? ምክንያቱም ኢየሱስ ስለ

አንቺ ኃጢአት ዋጋን እንደከፈለ ስላመንሽ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል እመኚ። ይቅር ስላለሽ አመስግኚው፤ ይቅርታ እንዳደረገልሽ ቢሰማሽም ባይሰማሽም ምንም አይደለም።

ክርስቶስ በመስቀል ከፈጸመው ሥራ የተነሣ ወደ መንግሥተ-ሰማይ እንደምትሄጂ እመኚ። እናም ሌሎች እንዴት ወደዚያ ሊሄዱ እንደሚችሉ በመመስከር ሥራ ተጠመጂ።

አውድሬ፡- በመንግሥት ሆስፒታል ውስጥ የምሠራ ነርስ ነኝ። ከጌታ ድጋፍ የተነሣ እስካሁን ድንግል ነኝ። ባለፈው ዓመት አንድ ደስ የሚል ወንድ ይጽፍልኝና በበዓላት ቀንም ይጎበኘኝ ጀመር። ዛሬ ግን ወደ ሆስፒታላችን መጣና አንዲት ሌላ ልጃገረድን ጠይቆ ሄደ። ወደዚያች ልጃገረድ ክፍል ብገባ ደግሞ ሲሳሳሙ አገኘኋቸው!

እንደሚያገባኝ እርግጠኛ ሆኜ ነበር። አሁን ግን. . . እግዚአብሔር ይህ እንዲሆን እንዴት ይፈቅዳል?

በኃጢአት እንዳልወድቅ ፈርቻለሁ፤ እባካችሁ እርዱኝ።

ውድ አውድሬ፥

«በኃጢአት እንዳልወድቅ ፈርቻለሁ» ስትዪ እንዲህ ለማለት የፈለግሽ ይመስለናል። «በሚቀጥለው ጊዜ ይህ ሰው እኔን የመፈለግ አዝማሚያ ካሳየ ትቶኝ እንዳይሄድ ምናልባትም ፍትወተ-ሥጋ እንዲፈጽም እፈቅድለት ይሆናል።»

ስሚ አውድሬ እግዚአብሔር ዓለምን የሚገዛ ቢሆንም ትታዘዢው ዘንድ ግን አያስገድድሽም። ለመምረጥ ነፃ ነሽ።

እባክሽ በጥንቃቄ ምረጭ።

አስቢ!

ከጋብቻ ውጭ የተፈጸመ ፍትወተ-ሥጋ በእርግጥ ሕይወትሽን ያሻሽለዋልን?

ዘላለማዊነትሽን የተሻለ ያደርገዋልን?

አንድ ወጣት ወንድ ትቶሻል። ግን ይህ ማለት እግዚአብሔር ትቶሻል ማለት አይደለም። እርሱ እረኛሽ ነው፥ እናም አሁን ድረስ ለአንቺ የተሻለ ዕቅድ አለው።

ታገቢ ዘንድ የእርሱ ፈቃድ ከሆነ ትክክለኛውን ሰው በትክክለኛው ጊዜ ይሰጥሻል።

ሳታገቢ እንድትኖሪ የሚወድድ ከሆነ ደግሞ የተቀደሰ ሕይወት ስትኖሪና በትጋት ስታገለግይው የተለየ ደስታን እርሱ ይሰጥሻል።

አውድሬ፡- አሁን እንኳ ከፍተኛ ኀዘን ተሰምቶሻል። ነገር ግን በጭንቀት ተዋልተሽ ቤት ቁጭ አትበዪ። በሥራ ተጠመጂ! እግዚአብሔርን ከሚያገለግሉ ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት አድርጊ።

እንደገናም በምትሠሪበት ሆስፒታል ውስጥ ሥራሽን በሚገባ አከናውኚ፥ ለሥራ ባልደረቦችሽና ለሕሙማን ርኅሩኅ ሁኚ። በክርስቶስ በኩል ስለሚገኘው ዘላለማዊ ሕይወት መልካሙን የምሥራች በፍቅር ንገሪያቸው።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስሽን ለማንበብ ጊዜ ውሰጂ። እንደ ኤርምያስ 29፡11–13 እና ምሳሌ 3፡5–8 ያሉት ጥቅሶች ልብሽን ሊያበረቱ ይችላሉ።

ዮሐና፡– የሕይወት ዘመኔን በሙሉ በብቸኝነት እንዳልጨርሰው እፈራለሁ። ዕድሜዬ 28 ነው። ለአራት ዓመታት ያህል ትክክለኛውን ሰው እንዲሰጠኝ ወደ እግዚአብሔር የጸለይኩ ቢሆንም እስካሁን ማንም ወንድ ብቅ አላለም።

ውድ ዮሐና፡– መጠየቅሽን ቀጥይ። ግን ሁሌም ጸሎትሽን «የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ» በማለት ማጠቃለልን አትርሺ (ሉቃስ 22፡42)።

ምናልባትም እንድታገቢ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል፤ ወይም ምናልባት ለብቻሽ እንድትሆኚ ፈቅዶ ይሆናል። አለማግባት ከማግባት የተሻለ ሊሆን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

«. . . ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል፤ ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፥ ልቡም ተከፍሎአል። ያልተጋባች ሴትና ድንግል በሥጋም በነፍስም እንዲቀደሱ የጌታን ነገር ያስባሉ የተጋባች ግን ባልዋን እንዴት ደስ እንድታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች። ይህንም ለራሳችሁ ጥቅም እላለሁ፤ በአገባብ እንድትኖሩ ሳትባክኑም በጌታ እንድትጸኑ ነው እንጂ ላጠምዳችሁ ብዬ አይደለም» (1ኛ ቆሮንቶስ 7፡ 32–35)።

አየሽ ዮሐና፥ እግዚአብሔር ይወድሻል። ለአንቺ የሚሻልሽ ማግባት ይሁን አለማግባት እርሱ ያውቃል። እመኚው! እንደዚህም ጸልዪ።

አባት ሆይ፥ መልካም ክርስቲያን ባል እንድትሰጠኝ እጸልያለሁ፤ ግን ሳላገባ እንድኖር የአንተ ፈቃድ ከሆነ ይህን እቀበላለሁ። አንተ ጌታ ነህ!

ባል ብትሰጠኝ ደስ ይለኛል፤ ከእርሱም ጋር ሆኜ አንተን አገለግላለሁ።

ባል ፈጽሞ ባትሰጠኝ

አሁንም ደስ ይለኛል፤ በታማኝነትም አገለግልሃለሁ።

አምንሃለሁ፣ የአንተ ፈቃድ ከሁሉ የተሻለ ነው።

የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ።

*«የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ»* ለማለት አስቸጋሪ ነው። ግን ዮሐና ልትይ የምትችዪው የተሻለ ቃላት እነዚህ እንደሆኑ አስተውዪ። ኢየሱስ እንዲህ ሲል ቃል ገብቷል። «የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ ነው፤ እኅቴም. . .» (ማርቆስ 3:35)።

የራሷን ፈቃድ የፈጸመች ሴት ደብዳቤ ይኸውልሽ።

> ውድ ብሩስና ካሮል፥
>
> ልጃገረድ ሳለሁ ፈጽሞ ባል ባላገኝ እንኳ በስፍራ ሁሉ ወንጌልን ለማሰራጨት ቃል ገባሁ።
>
> ቆይቶ ግን አንድን ሰው ለማግባት ወሰንኩ። ሰውየው የሰንበት ክርስቲያን (ክርስቶስን የማያገለግል) እንደሆነ አውቅ ነበር።
>
> ላለፉት ሃያ ዓመት ውጥንቅጥ በሆነ ትዳር እንገኛለን። ለወጣቶች የመናገር ዕድል ባገኘሁ ቁጥር «የራሳችሁን ፈቃድ አታድርጉ፤ በእግዚአብሔር ታመኑ የእርሱንም ፈቃድ ፈጽሙ» እላቸዋለሁ።

በርኒስ፡— እንድርያስ ደስ የሚል ሰው ነው። በየእሑዱ ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል። ትናንትና እንዳገባው ጠየቀኝ። ችግሩ ግን ክርስቲያን መሆኑን እጠራጠራለሁ። እግዚአብሔርን ሲያገለግል አጋጥሞኝ አያውቅም። በዚህም ላይ አንዳንድ ኃጢአቶችን ለመተው ፈቃደኛ አይደለም።

ግን በጣም ግሩም ሰው ነው፤ ባገባው ክርስቶስን እንዲወድድና እንዲታዘዝ እረዳዋለሁ።

ክርስቲያን ያልሆነን ሰው እንዳላገባ በግልጽ የሚናገረኝን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አላገኘሁም። ደግሞ ያልዳኑ ባሎች ያሏቸውን በርካታ ክርስቲያን እኅቶች አያለሁ።

ስለሆነም እንድርያስን ባገባ ኃጢአት ይሆን እንደሁ ምልክት እንዲሰጠኝ እግዚአብሔርን እየጠበቅሁ ነው።

ውድ በርኒስ፥

ምልክት መጠበቅሽን አቁሚ፤ የሚቀጥለውን ጥቅስ በሥራ ላይ አውዪ።

> «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?» (2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14)።

ይህ ጥቅስ ግልጽ ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ያልሆነ ማንኛውንም ሰው ማግባት የለብሽም።

«ያልዳኑ ባሎች ያሏቸውን በርካታ ክርስቲያን እኅቶች አያለሁ» ብለሻል። ይህ እውነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር. . . አትተወው ይላል» (1ኛ ቆሮንቶስ 7፡13)።

ነገር ግን በርኒስ አንቺ ያገባሽ ሰው አይደለሽም። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ለአንቺ የሚለው «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመጂ» ነው።

በርኒስ አሁን ለአንቺ የምንመክርሽ እንዲህ ነው።

ከእንድርያስ ጋር በቅንነት እውነትን ተነጋገሪ። «እኔ የምፈልገው እውነተኛ ክርስቲያን የሆነና ክርስቶስን አብሮኝ የሚያገለግል ባል ነው» ብለሽ ንገሪው።

በእውነት እግዚአብሔርን ከሚወዱ ወንዶች ጋር ወደሚገናኝበት ፕሮግራም ውሰጂው። ለዚህም ምክንያትሽ «ጌታን እንዲቀበልና ከዚያ በኋላ እንዳገባው እፈልጋለሁ» የሚል መሆን የለበትም። «ቢያገባኝም ባያገባኝም . . . የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኝ እፈለጋለሁ» የሚል ምክንያት ሊኖርሽ ይገባል።

ምናልባት ኃጢአቶቹን ሊናዘዝና ወደ ክርስቶስ ሊመለስ ይችላል። ግን በርኒስ መጠንቀቅ ይኖርብሻል። ማንኛውም ወንድ አንዲት ሴት እንድታገባው ሲል ብቻ በክርስትና ሊያስመስል ይችላል።

ለምሳሌ ያህል ሳም የሚባል ሰው በአንድ ወቅት እንዲህ ነገረን።

«ብሩስና ካሮል እናንተ ከጻፋችሁት መጽሐፍ የተነሣ ሚስት ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖብኛል።»

«እንዴት እባክህ» ስንል ጠየቅነው።

«ምክንያቱም» አለ ሳም «ከእኔ ጋር ወደ አልጋ ይነዱ የነበሩትን ልጃገረዶች ማግባት አልፈልግም። ታማኝ የሆነች ክርስቲያን ሚስት

እሻለሁ። ነገር ግን ክርስቲያን እስካልሆንኩኝ ድረስ ክርስቲያን ሴቶች አይቀበሉኝም።»

እኛም እንዲህ አልነው። «አድምጥ ሳም፥ በእርግጥም አንተ ክርስቲያን መሆን አለብህ። ይህም ጥሩ ሚስት እንድታገኝ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለ አንተ ልጁን ስለሰጠ ነው። በእርሱ እመን፤ ከኃጢአትህም ተመለስ፤ እርሱ የዘላለምን ሕይወት ቃል ኪዳን ሰጥቶሃል።»

«አይሆንም» አለ ሳም አቋርጦን «ንስሐ ለመግባት አልተዘጋጀሁም፤ ያቀድኩት ለተወሰኑ ወራት የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችን መካፈል፥ አንዲት ክርስቲያን ልጃገረድ መተዋወቅና እርሷን ማግባት ነው። ከዚያ ማለትም ከሠርጋችን በኋላ በተለያየ ሥራ እኔ በማልኖርበት ጊዜ እርሷ ምሽቶቹን በቤተ ክርስቲያን ማሳለፍ ትችላለች።

* * * * *

አየሽ በርኒስ። እንደ ሳም ያሉ ብዙ ወንዶች አሉ። ስለዚህም ነው «ተጠንቀቂ!» የምንልሽ።

ምናልባትም እንድርያስ «ትናንትና ክርስቶስን ለመቀበል ውሳኔ አድርጌያለሁ. . . እባክሽ አሁን እንደምታገቢኝ ቃል ግቢልኝ» ሊልሽ ይችላል።

እንደዚህ ካለ ምላሽ ከመስጠትሽ በፊት ረዘም ያለ ጊዜ ውሰጂ። በዚያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ምናልባትም ክርስቶስን እንደሚወድድ እያስመሰለ መሆኑን ልትደርሽበት ትችያለሽ።

ነገር ግን በእርግጥ ክርስቶስን እንደተቀበለ ከተረዳሽና ፍቅርሽም መመዘኛዎቹን ሁሉ ካለፈ (ገጽ25-33) ልታገቢው ትችይ ይሆናል።

ምሕረት፦ አንድ ደስ የሚል ወጣት ወድዶኛል። እማማ ግን የእኔና የእርሱን ቅርርቦሽ አልደገፈችም። ምክንያቱም ክርስቲያን ስላልሆነ ብቻ ነው።

ውድ ምሕረት፥

እናትሽ ትወድሻለች። ስለሆነም ልታድንሽ ፈልጋለች። የእናትሽን ምክር ስሚ፤ እናም 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14ን አንብቢ።

ማርታ፦ በትምህርት ቤት ሳለሁ ቁርጠኛ ክርስቲያን ነበርኩ። የምኖረውም ለኢየሱስ ብቻ ነበር። ከትምህርት ቤት ከወጣሁ

በኋላ ግን ወደ ኋላ መመለስ ጀመርኩ። በ19 ዓመቴ ዐነስኩ። ከሚቀጥለውም ዓመት ከዚያው ሰው አረገዝኩ። እርሱ ክርስቲያን አይደለም።

አሁን ሁለት ነገሮች ተከስተዋል። አንደኛ ወደ ኢየሱስ ለመመለስና በቀረው ዘመኔ በእርሱ መንገድ ለመኖር ወስኛለሁ። ሁለተኛ ሰውየው አሁን እንዳገባው ጠይቆኛል።

እርሱን ላግባው? ሁሉ ነገሩን እወድለታለሁ (ከጠጪነቱና ኢየሱስን ካለመውደዱ በስተቀር)።

ሳላገባው ብቀር ልጆቼ አባት–የለሽ ይሆናሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14 ላይ «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ» እንደሚል አውቃለሁ። ግን አንዳንዴ ሳስበው ልጆች እስከወለድን ድረስ አስቀድሞ የተጠመድን ይመስለኛል።

ውድ ማርታ፤

ሁልጊዜም ለወጣት ክርስቲያኖች የምንናገረው ይህንን ነው፤ «ከእናንተ በማይተናነስ አኳኋን ጌታን የሚወድን ሰው አግቡ»።

የአንቺን ጉዳይ በተመለከተ ግን ከእርሱ ወልደሻልና ልትሄጂባቸው የምትችዪ ሁለት አማራጭ መንገዶች ይታዩናል።

**አማራጭ** 1) «ጌታ ሆይ፤ በአንተ ላይ ጀርባዬን በማዞሬ እንደበደልኩ እናዘዛለሁ። እባክህን ይቅር በለኝ። አሁን ለልጆቼ ስል ይህን ሰው ማግባት እንዳለብኝ አስባለሁ። አንተን የማይወድ ባል ላላት ሴት ሕይወት አስቸጋሪ እንደሚሆን ይገባኛል። ሕይወቴን አዳጋች ያደረገው የራሴ ኃጢአት ነው። ከዚህ በኋላ ከመንገድህ ወደ ኋላ መመለስ በጭራሽ አልሻም» በማለት ልትጸልዪ ትችያለሽ።

**አማራጭ** 2) «ጌታ ሆይ፤ ኃጢአቴን እናዘዛለሁ፤ ከአሁን በኋላ ወደ ኋላ መመለስ አልፈልግም። ለአንተ ፍቅር የሌለውን ይህንን ሰው ማግባት እንደሌለብኝ አስባለሁ። ልጆቼ አባት–የለሽ መሆናቸው እንደሚከብድባቸውም እረዳለሁ። እባክህ ጥሩ አሳዳጊ እሆናቸው ዘንድ እርዳኝ» ብለሽ ጸልዪ።

ማርታ፤ በምትመርጪ ጊዜ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ይሁን።

«ወደ ኢየሱስ ለመመለስና በቀረው ዘመኔ በእርሱ መንገድ ለመኖር ወስኛለሁ» የሚለው የደብዳቤሽን ክፍል እንደወደድነው

መግለጽ የግድ ይሆናል። በፍርድ ቀን እግዚአብሔር እንዲህ ይልሻል። «ማርታ ልጄ ሆይ፥ ኃጢአትን ፈጽመሽ ነበር፤ ነገር ግን በክርስቶስ ካለሽ እምነት የተነሣ ታጠበ። ወደ ዘላለም ሕይወት ግቢ»።

ያም ሆኖ ግን በምድር ላይ ሳለሽ የፈጸምሽው ኃጢአት ሌሎች ችግሮችን ሊያስከትልብሽ ይችላል። ይህም ልጆችን ስታሳድጊ ወይም ምናልባት በትዳርሽ ላይ ይሆናል።

ኃጢአት ምንጊዜም ችግርን ይወልዳል (ገላትያ 6:7)። ስለሆነም ማርታ እንዲህ አድርጊ:-

*ልጆችሽ ሲያድጉ ወደ ኋላ መመለስሽ ያመጣውን መከራ በማንሣት አስጠንቅቂያቸው፤ በክርስትናቸው በድፍረት ወደፊት እንዲገሠግሡ እንጂ እንዳይመለሱ አበረታቺያቸው።*

አንጄላ:- ከማግባቴ በፊት የሳምንቱን መጨረሻ በክርስቶስ አገልግሎት አሳልፍ ነበር። አልፎ ተርፎ የምልክት ቋንቋ ተምሬ መስማት ለተሳናቸው ወገኖች ስለ ዘላለም ሕይወት እነግራቸው ነበር።

ለሦስት ዓመታት ያህል አንድ ሰው እንዳገባው ሲለምነኝ ቆየ። ምንም እንኳ ከጌታ ጋር የተጣበቀ ባይሆንም ክርስቲያን ይመስለኝ ነበር። «ባላገባው እድሜ ልኬን ብቸኛ እሆናለሁ. . .እናም ደስታ ይርቀኛል» በማለት ለራሴ በመንገሬ ስሕተትን ፈጸምኩ።

አገባሁት። ይህም የሆነው ከሁለት ዓመት በፊት ነበር። በእርግጥም አስቸጋሪ ጊዜ ነው ልል ይገባኛል! በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችን ይካፈላል፤ ነገር ግን በአገልግሎት ፈጽሞ አይተባበረኝም። አሁንማ ክርስቲያን መሆኑንም መጠራጠር ጀምሬያለሁ።

እስከማውቀው ድረስ ከሌሎች ልጃገረዶች ጋር አይወጣም። ግን ብዙ ጊዜ «ከጓደኞቼ ጋር ቢራ ስንቀማምስ ነበር» እያለ አምሽቶ ይመጣል።

ተረብሻለሁ። ብዙ ጊዜም አላናግረውም።

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያን እንዲሆን ብለምነውም ይህ ውጤት አላመጣም። እናም አልሳካ ሲለኝ እንባ ይቀድመኛል።

ለእኔ ተስፋ ይኖር ይሆን?

ውድ አንጂላ፣

አዎን አለ። ባልሽ ክርስቲያን ይሆን ዘንድ ማስገደድ አትችይም። ነገር ግን እንዲሆን ልታበረታቺው ትችያለሽ። እንዴት ብትይ እንደሚከተለው ነው።

ሀ) ይቅርታ አድርጊለት። በደብዳቤሽ ላይ «ብዙ ጊዜም አላናግረውም» ብለሻል። እግዚአብሔር ባልሽን ይቅር ትዪው ዘንድ ይፈልጋል። እናም ይቅር ካልሽው ያለምንም መራርነት ከእርሱ ጋር መነጋገር ትችያለሽ።

ለ) ጸልዪለት። እንደገናም የቅድስና ሕይወት ለመኖር ብትጠነቀቂ ጸሎትሽ የበለጠ ኃይልን እንደሚያደርግ አስታውሺ (ያዕቆብ 5፡16)።

ሐ) መልካም ያልሆነን ነገር ለባልሽ እንደተናገርሽ ስታስቢ ይህንን ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ተናዘዢ። ከዚያም ለባልሽ «ተበሳጭቼ የማይገባ ነገር ስለተናገርኩህ አዝናለሁ፣ እግዚአብሔርን ይቅር እንዲለኝ ጠይቄዋለሁ። አሁን አንተም እባክህ ይቅር በለኝ» በይው።

አንድ ቀን ባልሽ እንዲህ ይልሽ ዘንድ እንጸልያለን። «እናንተ ክርስቲያኖች ፍጹማን ነን እንደማትሉ ተገንዝቤአለሁ። ስሕተቶቻችሁን ትቀበላላችሁ። ያም ሆኖ ግን እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት እንደሰጣችሁ እርግጠኞች ናችሁ። እኔስ እንዴት ክርስቲያን መሆንና የዘላለምን ሕይወት ማግኘት እችላለሁ?»

ያኔ ስለ ክርስቶስ ልትነግሪው ትችያለሽ፣ ነገር ግን እስኪጠይቅሽ ድረስ ብዙም አትናገሪ።

«እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ
አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥
በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን
እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው
ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡1)።

በእርግጥ ባልሽ ክርስቶስን ለመቀበል ይወስናል ብለን ተስፋ ልንሰጥሽ አንችልም። ምናልባትም በእግዚአብሔር ላይ ጀርባውን ሊያዞር፥ በመሻሻልም ፈንታ ሊብስበት ይችላል። ጠጥቶና ሰክሮ ወደ ቤት በመምጣት በሚያስቅቅ አኳኋን ሊመታሽ ይጀምር ይሆናል። ምናልባትም ሌሎች ሴቶችን/ልጃገረዶችን ማውጣት ሊጀምር ይችላል። ከዚህም የተነሣ ልትፈቺው ትፈልጊ ይሆናል።

1ኛ ቆሮንቶስ 7፡10–11 በመሠረቱ ሚስት ባልዋን መፍታት እንደሌለባት ይናገራል። ግን ደግሞ በመቀጠል እንዲህ ይላል «ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ትታረቅ»።

አሁን አስተውዪ አንጂላ። ዛሬ ልታደርጊው የሚገባሽ ነገር ይህ ነው። በየሳምንቱ ከአንቺ ጋር የጸሎት ኅብረት ማድረግ የሚችሉ ሁለት ክርስቲያን ሴቶችን ፈልጊ። አንዳቸው የሌላውን ምሥጢር መጠበቅ የሚችሉትን ምረጪ። በየሳምንቱ በተገናኛችሁ ቁጥር ችግሮችሽን ትነግሪያቸዋለሽ፤ እነርሱም ምክርን ይለግሡሻል፥ ይጸልዩልሻል። ከዚያም በእነርሱ ላይ ስላሉ ችግሮች አብረሻቸው ልትጸልዪ ትችያለሽ። ባልሽን ለመፍታት ውሳኔ ላይ ብትደርሽ እንኳ እነዚህ ሴቶች ትልቅ ድጋፍ ይሆኑሻል።



«እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም» (ገላትያ 6፡2)።

«እያንዳንዱ ስለሌላው ይጸልይ» (ያዕቆብ 5፡16)።

«አንዱም ሌላውን ያንጸው» (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡11)።

አማንዳ፡– በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የወደድኩትን ሰው አገባለሁ። ከቤተሰቦቻችን ርቀን በአንድ መንደር ውስጥ እንሠራለን። እርሱ እኔ በምካፈልበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሪነት ያገለግላል።

ዛሬ እርሱ በሚኖርበት ቤት አብሬው መኖር እንድጀምር ጠየቀኝ። ምን እንደምመልስለት አላውቅሁም። ከእርሱም ሆነ ከማንኛውም ወንድ ጋር የግብረ –ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም። እስከምንጋባ ቀን ድረስ የግብረ–ሥጋ ግንኙነት እንፈጽማለን ብዬ አላስብኩም ነበር።

አሁን እንጀምረው? ምንስ ልመልስለት እችላለሁ?

ውድ አማንዳ፥

በቀጥታ «አይሆንም» በዪው። በእርግጥ ክርስቲያን ከሆነ ጌታን እንዲታዘዝ ስለረዳሽው ያመሰግንሻል (1ኛ ዮሐንስ 3፡9)።

ትቶሽ ከሄደ ግን ይህ እውነተኛ ክርስቲያን አለመሆኑን ያመለክታል (1ኛ ዮሐንስ 2፡3–6)።

ኤውንቄ፡– ባለፈው ዓመት ለአንድ ክርስቲያን ወንድም የጋብቻ ቃልኪዳን ገባሁ። ከቃል ኪዳኑ በኋላ ከእኔ ጋር ፍትወተ–ሥጋ

እንዲፈጽም ፈቀድኩለት። «የሚያገባኝ እርሱ እስከሆነ ድረስ ምንም ችግር አያመጣም» ስል ራሴን አጽናናሁ።

አሁን አርግዣለሁ፤ የምኖረውም ከቤተሰቦቼ ጋር ነው። እርሱስ ምን እያደረገ ይመስላችኋል? ከአዳዲስ ሴት ጓደኞቹ ጋር ሥራ በዝቶበታል!

ልጃገረዶችን እንደ ሸሚዝ እንደሚቀያይር ሰምቻለሁ። እስከ ዛሬ እውነተኛ ክርስቲያን የነበረ መሆኑም አጠራጥሮኛል።

ሊያገባኝ እንደማይፈልግ ግልጽ አድርጎልኛል። ከመጀመሪያውም ፈጽሞ ጋብቻን እንዳላለመ ገምቻለሁ። ግን ተጠቀመብኝ።

እኔ በዚህ ጉዳይ ለሕይወቴ ሙሉ የሚሆን ትምህርት አግኝቻለሁ። ከአሁን በኋላ በጭራሽ ደግሜ ፊቴን በእግዚአብሔር ላይ አላዞርም።

በዚህ ሳምንት ኃጢአቴን ለእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያኔ አባላት ፊት ተናዘዝኩ። ኢየሱስ ራሱን በመሥዋዕትነት ከማቅረቡ የተነሣ እግዚአብሔር ይቅር እንዳለኝ አምናለሁ።

ግን በየዕለቱ ጭንቀትና ብቸኝነት ይሰማኛል። የትኞቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንዳነብ ትመክሩኛላችሁ?

ውድ ኤውንቄ፦

እኛ እንወድሻለን፤ ደግሞም እግዚአብሔር ይወድሻል!

በኢየሱስ ክርስቶስ ካለሽ እምነት የተነሣ ይቅርታ እንደምታገኚ መጽሐፍ ቅዱስ ይስማማል። ኤውንቄ አሁን በእግዚአብሔር ላይ ዳግመኛ ጀርባሽን ላለማዞር ባደረግሽው ውሳኔ ግፊ።

አንዳንድ ታላላቅ ጥቅሶችን እነሆ፦ እነዚህን ጥቅሶች ከሁለት ወይም ሦስት ክርስቲያን ሴቶች ጋር አጥኚያቸው። [መዝሙር (51)፤ 1ኛ ዮሐንስ 1፡9፥ መዝሙር (103)፡12፥ 1ኛ ሳሙኤል 12፡20-25፥ ምሳሌ 28፡13፤ ዮሐንስ 5፡14፤ የሐዋርያት ሥራ 26፡20፤ ቆላስይስ 3፡5-19]።

ማስታወሻ፡- ከላይ የሰፈሩትን ሁለት ደብዳቤዎች የተቀበልነው በአንድ ቀን ነው። አንዱ የአማንዳ ሲሆን ሌላው ሌውንቄ ነበር)።

በመጀመሪያ የአማንዳን ደብዳቤ አነበብን። ያገባኛል ብላ ካሰበችው ሰው ጋር የፍትወተ-ሥጋ ልምምድን ለመጀመር ፈልጋ ነበር።

ከዚያ በኋላ የሌውንቄን ደብዳቤ አነበብን። ያገባኛል ብላ ካላሰበችው ሰው ጋር ፍትወተ-ሥጋ በመፈጸሟ አሁን ሕይወቷ ችግር ውስጥ ወድቋል።

የእግዚአብሔር ሕግ፡- አንድን ሰው ልታገቡት እንደሆነ «ብታውቁ» እንኳ እስካልተጋባችሁ ድረስ ፍትወተ-ሥጋ አትፈጽሙ የሚል ነው።

የእግዚአብሔርን ሕግ የሚተላለፉ
ሰዎች በምድር በሚኖሩት ሕይወት ላይ
ተጨማሪ ችግርን ያመጣሉ
[መዝሙር (19)፡7-11 ተመልከት።]

ያዕቆብ፡- የወጣቶች አገልግሎት የሚመራው ወንድም አጭቶ ነበር። ዛሬ ግን «ላላገባሽ ወስኛለሁ» በማለት ለልጅቷ ነገራት።

የእጮኛነት ቃልኪዳኑን አፍርሶአልና፤ በአገልግሎት መሪነት እንዲቀጥል ልንፈቅድለት ይገባልን?

ውድ ያዕቆብ፥

አዎን፥ በመሪነቱ እንዲቀጥል ፍቀዱለት።

ጋብቻ እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ለመሆን የሚደረግ ቃል ኪዳን ነው። እጮኛነት ግን ቃል ኪዳን አይደለም፤ «አንዳችን ለሌላችን የተገባን ነንን?» ብሎ ለመተያየት የሚወሰድ ጊዜ ነው።

በእጮኛነት ገደብ ውስጥ ሳላችሁ «እርሱ/ሷ በእውነትና በእርግጥ አይወደኝም/አትወደኝም» ወይም «ያስመስላል/ታስመስላለች እንጂ

ክርስቶስን አይወድም/አትወድም» ወደሚለው መደምደሚያ ከደረሳችሁ እጮኝነትን ማቋረጥ ይመረጣል።

መፋታት ኃጢአት ነው (ማቴዎስ 19:9)።

እጮኝነትን ማቋረጥ እጅግ የሚጎዳ ነገር ነው፥ ነገር ግን ኃጢአት አይደለም። በእርግጥም የተቋረጠ እጮኝነት በኀዘን ከተሞላ ጋብቻ የተሻለ ነው።

ልድያ፦ የማገባው በሚቀጥለው ወር ነው። ገና በዩኒቨርሲቲ ስላለሁ ከወደፊቱ ባሌ ጋር ቢያንስ ለሁለት ዓመታት ላለመውለድ ተስማምተናል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያናችን «የቤተሰብ ምጣኔ» ኃጢአት ነው የሚል አቋም አላት።

ታዲያ እንዴት ሳንወልድ መቆየት እንችላለን? ከተጋባን በኋላ ከአንድ ዓመት በላይ ለብቻው እንዲተኛ ልጠይቀውን?

ውድ ልድያ፥

ካገባሽ በኋላ ከባልሽ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ፈጽሚ። በሌላ አልጋ ላይ እንዲተኛ አትጠይቂው። መጽሐፍ ቅዱስ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን በተመለከተ ባልና ሚስት አንዱ ሌላውን ሊያረኩ ይገባል ይላል።

> ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥
>
> እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ . . .
>
> እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤
>
> ራሳችሁን ስለ አለመግዛት. . . እንዳይፈታተናችሁ. . . »
>
> (1ኛ ቆሮንቶስ 7:3-5)።

አሁን እንዲህ ብላችሁ ልትጠይቁን ትሞክሩ ይሆናል። የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ከፈጸምን የመውለጃችንን ጊዜ እንዴት ልናዘገየው እንችላለን?

መልሱ፦ የቤተሰብ ምጣኔን ተጠቀሙ የሚል ይሆናል። ልብ አድርጊ ልድያ፦ በምድራችን ላይ «የቤተሰብ ምጣኔ ኃጢአት ነው» የምትል አንድ እንኳ ቤተ ክርስቲያን የለችም። ግን አንዳንዶቹ «የተወሰኑት የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎች ኃጢአት ናቸው» ይላሉ እንጂ የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን «ዘዴዎቹ ሁሉ ኃጢአቶች ናቸው» አትልም። ስለሆነም ልድያ የቤተ ክርስቲያንሽን መሪዎች እንዲህ ብለሽ ጠይቂያቸው። «የእኛ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎች የትኞቹ ናቸው?»

የሠርጋችሁ ዕለት ጥቂት ቀናት ብቻ ስለቀሩት «የጋብቻ እንቆቅልሾችና መፍትሔዎቻቸው» የሚለውን መጽሐፋችንን አንብቢው። በዚያ ላይ «ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ» የተሰኘውን ዘዴ አብራርተናል። ሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች ይህን ዘዴ ይቀበሉታል። (ገጽ )

ጽርስቅላ፥ መልካም ሰብዕና ካለው ክርስቲያን ወንድም ጋር ተጫጭተናል። ሁለታችንም ደናግል ነን። ሠርጋችንም ከሁለት ወራት በኋላ ነው።

ፍትወተ-ሥጋ እንዴት መፈጸም እንዳለብኝ ስለማላውቅ ፈርቻለሁ። እንዴት ልለምድ እችላለሁ? በዚሁ ላይ ያተኮሩ የቪዲዮ ፊልሞችን መመልከት ይኖርብኝ ይሆን?

ውድ ጽርስቅላ፥

ፈጽሞ፦ በፍትወተ-ሥጋ ላይ የሚያተኩሩ የቪዲዮ ፊልሞችን መመልከት ከጥቅሙ-ጉዳቱ ያመዝናል።

አትጨነቂ ጽርስቅላ «ከጋብቻ በኋላ አንቺና ባልሽ ደስ እያላችሁ ትለማመዱታላችሁ። ፍትወተ-ሥጋ የሚለውን አሳብ አትፍሪው። ባልሽን በመውደድ ብቻ ደስ ተሰኚበት። እርሱም አንቺን በመውደድ ደስ ይሰኝ። ደስ ስለሚላችሁና ስለማትወዱትም ነገር አንዳችሁ ለሌላችሁ ንገሩ። ነፃ ሁኑ። ሁለታችሁንም ደስ የሚያሰኛችሁን ነገር ሁሉ ፈጽሙ። ለባልና ሚስት የእግዚአብሔር ሕግ፦ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ (በማንኛውምና በምትወዱት መንገድ) ግን በራሳችሁ መካከል ብቻ አድርጉት የሚል ነው።

አንዳችሁ ከሌላኛው ስትማሩ ጋብቻችሁ ውብ ይሆናል። . . . ስታወሩ፥ ስትስቁ፥ ስትዋደዱ. . . በተለይም ከሁለት አንዳችሁ በሌላ «አፍቃሪ» በኩል «እንዳልተማራችሁ» ስታውቁ!

> እንዳችው ሌላው እንዴት ደስ እንደሚያሰኝ በተማሩ መጠን በባልና ሚስት መካከል ያለው ፍቅር ጥልቀቱ እየጨመረ ይሄዳል።

(ስለ ፍትወተ-ሥጋ መጠነኛና መሠረታዊ ግንዛቤ ይዛችሁ ወደ ጋብቻ መግባት ከፈለጋችሁ ግን ሠርጋችሁ ጥቂት ቀናት ሲቀረው ‹የጋብቻ እንቆቅልሾችና መፍትሔዎቻቸው› የተሰኘውን መጽሐፋችንን አንብቡት።)

ኢየሱ፡- እኔና ባለቤቴ በባለሙያነት የምንሠራ ሲሆን ጠቀም ያለ ደመወዝ እናገኛለን። ያም ሆኖ ጋብቻችን ችግር የሞላበት በመሆኑ ደስተኞች አይደለንም።

ከመተዋወቃችን በፊት ሚስቴ ከሁለት ወንዶች ጋር ትወጣ እንደነበረ እስካወቅሁበት ቀን ድረስ ትዳራችን መልካም ነበር። አሁን አንደኛው ሰው እኔ ባለሁበት ቢሮ ውስጥ ይሠራል።

በጸጥታ በምሆንበት ጊዜ ሚስቴ በእነዚህ ሰዎች ፊት ዕርቃን-ሥጋዋን ቆማ በዓይነ-ሕሊናዬ አያታለሁ። ይህ ያስጠላኛል።

ቀንና ሌሊት ራሴን እንዲህ እጠይቀዋለሁ።

ሀ) በአልጋ ውስጥ ስንሆን ከሁለቱ ስለ አንዱ ታስብ ይሆን?

ለ) እነዚህ ሰዎች እኔና ሚስቴን በአንድነት ሲያዩን ያኔ እንዴት እንደተደሰቱባት ትዝ ይላቸዋልን?

ሐ) ከሁለት አንዳቸውን ስናገኝ እርሷ ምን ይሰማት ይሆን?

እንዲህ ትለኛለች። «በጣም አዝናለሁ። ልጃገረድ ሳለሁ ፍርሃቴ ‹ትዳር አልይዝ ይሆንን?› የሚል ነበር። ስለሆነም እንዲህ ማሰብ ጀመርኩ ‹ባል እንዳገኝ ከወንድ ጋር ለመተኛት ፈቃደኛ መሆን አለብኝ›።

እኔ ደግሞ «የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ወደ ጋብቻ የሚያስገባ በር አይደለም» እላታለሁ።

እርስዋም እንዲህ ትመልስልኛለች። «ይህ እውነት እንደሆነ አሁን ገብቶኛል። ግን አንተ ይህን ለእኔ እንዴት ልታስተምረኝ ትችላለህ? በሠርጋችን ዕለት ምሽት ለግብረ-ሥጋ ግንኙነት አዲስ አለመሆንህን አውቄአለሁ። ከእኔ ጋር ከመተዋወቅህ በፊት ከሌሎች ልጃገረዶች ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈጸምህን ትክዳለህ?»

እውነት ነው። ሚስቴን ስተዋወቃት ድንግል አልነበርኩም። ከእርስዋ የተሻለ ሕይወትም አላሳለፍኩም።

ግን ሚስቴን ስተዋወቃት ድንግል እንድትሆን እመኝ ነበር። ከዚያ በእርሷ ሕይወት ‹ብቸኛው ሰው› እሆናለሁ።

ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ስጦታ ማለትም ‹ድንግልና› ሁለታችንም አፍርሰን ነበር።

በጋብቻችን የመጀመሪያ ሁለት ዓመታት ከሚስቴ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ደስ ያሰኘኝ ነበር። ነገር ግን ያለፈ ታሪኳን ከደረስኩበት ወዲህ ሥቃይ ሆኖብኛል።

አሁንም ቢሆን በልቤ ሚስቴንና ልጆቻችንን እወዳለሁ። ትዳራችን ከእንግዲህ ተስፋ ይኖረው ይሆን?

ውድ ኢያሱ፥

አዎን አለው! አንተና ሚስትህ አንድ ነገር ያስፈልጋችኋል። ያም ይቅር መባባል ነው።

ሁለታችሁም ከእግዚአብሔር ይቅርታን መቀበል ይኖርባችኋል። ከዚያ በኋላ ደግሞ እርስ በርስ ይቅር መባባል አለባችሁ (ማቴዎስ 18፡21-35)።

ሌላ መልስ የለንም።

የእግዚአብሔርን ይቅርታ መቀበል የምትችሉበት ብቸኛ መንገድ ደግሞ ክርስቶስን የግል አዳኛችሁና ጌታችሁ በማድረግ ነው።

> ማስታወሻ - በዚህ ስፍራ ኢያሱና ባለቤቱ እንዴት ክርስቲያን መሆን እንደሚችሉ ገልጸንላቸዋል (ከገጽ 67-69 ተመልከት)። ከዚያም እንዲህ አልናቸው።

አንተና ባለቤትህ ጌታን ስትቀበሉ ይቅር ይላችኋል፤ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣችኋል። ያን ጊዜ እናንተ ይቅር ከመባባልም አልፋችሁ ደግማችሁ ከጋብቻ ውጭ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ላለመፈጸምም አንዳችሁ ለአንዳችሁ ቃል ትገባላችሁ።

ከዚያም በኋላ ሁለታችሁም ከሌሎች የቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት ጋር በመሆን ክርስቶስን ማገልገል ትጀምራላችሁ።

**በዓለም ላይ ከሁሉ የላቁ ደስተኛ ባለትዳሮች**

**እነርሱ በታማኝነት እየኖሩ አብረው ክርስቶስን የሚያገለግሉ**

**ባልና ሚስት ናቸው።**

አንተና ባለቤትህ ክርስቶስን በማገልገል ሥራ ሲበዛላችሁ ደግሞ ልጆቻችሁን መርዳት አትርሱ። በእናንተ ትዳር ላይ እንዲህ ዓይነት ሳንካ ካመጣው የዝሙት ኃጢአት እንዲርቁ እርዱቸው።

ልጆቻችሁን ለመርዳት የሚከተሉትን ሁለት ነገሮች ፈጽሙ።

ሀ) እንዴት እውነተኛ ክርስቲያን መሆን እንደሚችሉ መንገዱን አሳዩአቸው።

ለ) እያደጉ ሳለ የንጽሕና ሕይወት እንዲኖሩ አበረታቷቸው። ኃጢአት በሕይወትና በትዳር ላይ ችግርን እንደሚያስከትልም አስታውሷቸው።

የልጆቻችሁ ዕድሜ 13 ሲደርስ "Kiss me, Sweet Baby" ወይም «ተወዳጁ ሕፃን፥ ና ሳመኝ» የሚለውን መጽሐፋችንን እንዲያነቡ ጋብዟቸው። በርካታ ወጣቶች የሚሰናከሉባቸውን ወጥመዶች እንዴት ማለፍ እንደሚችሉ ስለሚያመለክታቸው ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይህንን መጽሐፍ ይወዱታል። (ገጽ 159 ተመልከት)።

ኑኃሚን፡- ፊልሞና ከቤቴ አጠገብ ባለው ኮሌጅ ይማራል። እኔ ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ዘንድሮ እጨርሳለሁ። ብርቱ ክርስቲያን ነው። ካለፈው ዓመት ጀምሮ ወደ ቤተክርስቲያን ይወስደኝ ጀመር። አሁን በሙሉ ልቤ ጌታን የተቀበልኩና የውኃ ጥምቀትም የወሰድኩ ነኝ።

ሊያገባኝ ይፈልጋል። እኔ ግን ለቤተሰቦቼ እንዳይነግር ጠይቄዋለሁ። ምክንያቱም አሁን ገና እየተማርኩ ነው።

ብዙ ጊዜ ወደ ቤታችን ይመጣል (ዋና ምክንያቱ የወንድሜ ጓደኛ መሆኑ ነው።) ችግሩ ግን አንዳንድ ቀን ወደ ቤታችን ሲመጣ ወንድሜና ቤተሰቦቼ አይኖሩም። እንዲህ ከሆነ ሊስመኝ ይጀምራል። ደስ ስለሚለኝ ላስቆመው አልሞክርም። አንዳንድ ጊዜ በጣም ደስ ከመሰኘታችን የተነሣ ልብሶቻችንን አወላልቀን እንጥላለን። በዚያው እንረካለን። ነገር ግን ብልቱን ወደ ብልቴ አያስገባም።

ምንም እንኳ ፍትወተ-ሥጋ ባንፈጽምም የምናደርጋቸው ነገሮች ግን ደስ አይሉም። ይህን ነገር ማቆም እንዳለብን ነገርኩት።

እርሱም «ደንብ አውጪ፤ ምክንያቱም ራሴን መቆጣጠር በጣም አስቸግሮኛል» ሲል መለሰልኝ።

ብሩስና ካሮል እባካችሁ ደንብ አውጡልን።

ውድ ኑኃሚን፥

ሁለት መልካም ደንቦች እኚሁልሽ።

1) ፊልሞና ወደ ቤታችሁ መጥቶ ብቻሽን ካገኘሽ ይመለስና ቤተሰቦችሽ ሲኖሩ ይምጣ።

2) ለብቻችሁ ሆናችሁ በማይረባ ድርጊት ከማባከን ይልቅ ጊዜያችሁን ክርስቶስን በማገልገል ተጠቀሙ። አንቺና ፊልሞና ከሌሎች ክርስቲያን ወጣቶች ጋር መቀላቀል አለባችሁ። እነርሱም በሽርሽር ስፍራ ምግብ በማብሰል፥ መበለቶችን በመርዳት ወይም ቤት –የለሽ ሕፃናትን በመንከባከብ የሚተጉ ናቸው።

ከተጋባችሁም በኋላ አብራችሁ እግዚአብሔርን ማገልገል ቀጥሉ።

አስቴር፡– ወላጆቼ ክርስቲያን ናቸው። ግን በየዕለቱ በገንዘብ ጉዳይ ይጨቃጨቃሉ። እኔ የዚህ ዓይነት ትዳር አልፈልግም።

ሚስት ከባልዋ ገንዘብ መለመን አለባት ወይ? ወይስ የራሷ ገንዘብ ሊኖራት ይገባል?

ውድ አስቴር፥

ባልና ሚስት ገንዘብን ሊይዙ የሚችሉባቸው ሦስት መሠረታዊ መንገዶች አሉ። የመጀመሪያው «ራስ ወዳድ ወንድ» ያለበት ነው።




1) የወንድ ራስ ወዳድ

የወንድ ራስ ወዳድነት በሚንጸባረቅበት መንገድ ባልየው ለሚስቱ ምን ያህል እንደሚያገኝ አይነግራትም። አብዛኛውን ገንዘብ ለሚስቱ ወይም ለልጆቹ ሳይሆን ለራሱ ለማጥፋት ስለሚያቅድ በምሥጢርነት ይይዘዋል።

ዛሬ በርካታ ሴቶች በወንድ ራስ ወዳድነት ሰልችተዋል። ስለዚህም እንዲህ ሲሉ ይደመጣሉ። «ከባሌ ገንዘብ ከምለምን ይልቅ ሥራ ባገኝ ይሻለኛል፤ ያን ጊዜ የማገኘው ሁሉ የራሴ ይሆናል።»

ይህ መልካም ይመስላል። ችግሩ ግን ያንን ቤት ይህ ክንዋኔ ደስተኛ አያደርገውም። ለምን? ምክንያቱም አሁንም ቢሆን በራስ-ወዳድነት የተሞላ ነው። ሚስት ልክ እንደ ባልዋ ራስ ወዳድ ለመሆን ስትወስን ማለቂያ ወደሌለው ውዝግብ ይገባሉ።




2) ሁለት ራስ ወዳጆች

የእግዚአብሔር መንገድ የተሻለ ነው። እርሱ ስለ ገንዘብ ሁለት ነገሮች ተናግሯል።

## ሀ) ለጌታ በመስጠት ለጋሦች ሁኑ።

መጽሐፍ ቅዱስን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ስናነብ ሁልጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የከብት፥ ፍየል፥ ጥራጥሬና የገንዘብ ስጦታ እንዲያመጡ እንደተናገራቸው እንመለከታለን። (ዘጸአት 22፡29-30፥35፡4-5፤ ዘሌዋውያን 1፡2፥ 1፡10፥ 2፡1-7፥5፡7፤ ዘዳግም 18፡3-5፥

2ኛ ሳሙኤል 24:24፤ ምሳሌ 21:26፥ ሚልክያስ 3:8፡10፤ ሮሜ 12:13፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 16:2፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 8:7፥ 9:7፤ 1ኛ ዮሐንስ 3:17–18)።

## ለ) አንዳችሁ ለሌላችሁ ለጋሦች ሁኑ።

እግዚአብሔር «ባል ለሚስቱ ስለሚያስፈልጋት ነገር ሊጠነቀቅ ይገባዋል» ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 3:7)።




3) እውነተኛ ክርስቲያናዊ ጋብቻ

ባል ገንዘቡን ሁሉ በመጠጥ የሚጨርሰው ከሆነ ሚስቲቱን «ገንዘብሽን ለብቻ አኑሪ» በማለት እንመክራለን።

ያም ሆኖ ለማንኛውም ወጣትና ያላገባ ሰው የእኛ ምክር እውነተኛዋን ክርስቲያን አግባ የሚል ነው።

ጋብቻችሁ ገና ረዥም ጊዜ ሲቀረው አብራችሁ ተቀመጡና በገንዘብ ጉዳይ ላይ ተወያዩ።

ሀ) ለጌታ ለመስጠት ለጋሥ ለመሆን፥

ለ) እንዳችሁ ለሌላችሁ ለጋሦች ለመሆን በአንድነት እንደምትወስኑ ተስፋ እናደርጋለን።

ለእግዚአብሔር ሥራ፥ ለምግብ መግዣ. . . ለኪራይ. . . ለቤተሰብ ድጋፍ. . . ለትራንስፖርት፥ ወዘተ. . . በየወሩ የምትሰጡና የምታወጡትን የሚያሳይ በጀት ጊዜ ወስዳችሁ በጽሑፍ አስፍሩ።

ማቴዎስ 6፡19–21ን በአንድነት አሰላስሉ።

ዮሐንስ፡— አንድ አማኝ ለቤተ ክርስቲያን መስጠት ያለበት ገንዘብ ምን ያህል ነው?

ውድ ዮሐንስ፥

እኛ ክርስቲያኖች «ጌታ ሆይ፥ ባለኝ ተሰጥዖ ሁሉ አገለግልሃለሁ (መስበክ፥ ልጆችን ማስተማር ወይም ሌላ ማንኛውም ስጦታ) እንደገናም በገንዘቤ አገለግልሃለሁ፤ ለራሴ ጥቂት ገንዘብ አጠፋለሁ፤ አብዛኛውን ግን መልካሙን የምሥራች ለሕዝቦች ሁሉ ለማድረስ ለአንተ ሥራ እሰጣለሁ» የሚል ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል።

ሐዋርያው ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናት ሰባኪዎችን መላክና እነርሱንም በገንዘብ መደገፍ እንደሚገባቸው ጽፎአል።

«እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? . . . ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?» (ሮሜ 10፡14–15)።

«ወይስ ሥራን ለመተው መብት የሌለን እኔና በርናባስ ብቻ ነን? ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው? . . እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል» (1ኛ ቆሮንቶስ 9፡6–7 እና 14)።

«የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ» (ሮሜ 15፡20)።

«በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት በራብና በጥም. . . በራቁትነት. . . ነበርሁ» (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡27)።

«እስራትና መከራ ይቆይሃል. . . ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልኩትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ» (የሐዋርያት ሥራ 20፡23–24)።

«ወደ እስጳንያ በሄድሁ ጊዜ ሳልፍ . . . ወደዚያ በጉዞዬ እንድትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ» (ሮሜ 15፡24 ተመልከት)።

«እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና» (2ኛ ቆሮንቶስ 9:7)።

«በስሌታችሁ የሚበዛውን ፍሬ እንጂ ስጦታውን ፈላጊ አይደለሁም» (ፊልጵስዩስ 4:17)።

«. . . ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ» (1ኛ ቆሮንቶስ 16:2)።

በእኛ ቤት ከላይ በሰፈሩት ጥቅሶች ላይ መወያየት እናዘወትራለን። ለእግዚአብሔር በአንድነት እንዲህ ብለን ቃል ገብተናል።

ለቤተ ክርስቲያናችን በልግሥና እንሰጣለን። ዕዳለ-ማውታና መበለቶችን እንረዳለን።፣ ከገንዘባችንንም አብዛኛውን ክፍል ወንጌልን በቅርብና በሩቅ ላሉ ሕዝቦች ለሚሰብኩት እንሰጣለን (ሮሜ 10:15)።



እውነተኛ ክርስቲያን ከሆንክ"Arise Boldly with Power" «ኃይልን ለብሰህ በድፍረት ተነሣ» የሚለውን መጽሐፍ በማንበብ ወደ በለጠ ጥንካሬ ልታድግ ትችላለህ። (ገጽ 159 ተመልከት)።

ማርያም፡— እኔና ዳዊት እርስ በርሳችን በጣም እንዋደዳለን! የምንጋባው በሚቀጥለው ዓመት ነው።

ከዘመዶቻችን ብዙዎች አልዳኑም፤ እናም በሠርጋችን ላይ ወንጌል በግልጽ እንዲሰበክ እንፈልጋለን።

አንዳንድ ሰዎች ትልቅ ‹የሠርግ ኬክ›ና ውድ ልብሶችን እንድናዘጋጅ ይመክሩናል። ነገር ግን እኛ በሠርጋችን ላይ የተንዛዛ ወጪ እንዲኖር አንፈልግም።

የክስቲያኖች ሠርግ የግድ ባለ ብዙ ወጪ መሆን አለበትን?

ውድ ማርያም፥

የለበትም። ሠርጎች ብዙ ወጪ የሚያስከትሉ መሆናቸው አስፈላጊ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ ክርስቲያን ወንድና እንዲት ሴት ሊሠርጉ ሊያስቡ በአንድነት ተቀምጠው በሁለት ነገሮች ላይ መወያየት ይኖርባቸዋል።

## የሠርግ ዕቅዶች

1) በሠርጋችን ላይ የሚገኘው ሰው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ያገኝና በክርስቶስም ሆኖ በድፍረት ይኖር ዘንድ ምስክርነቶች፥ ዝማሬና ስብከትን እንዴት መጠቀም እንችላለን?

2) የተንዛዛ ወጪን እንዴት መገደብ እንችላለን? (ሠርጋችንን በከፍተኛ ወጪ ካደረግነው የትዳራችን ጅማሬ ዕዳ ይሆንና እናዝናለን፤ እናም የክርስቶስን መንግሥት ወንጌል ለማሰራጨቱ ለአስፈላጊ ሥራ ገንዘብ ያንሰናል።)

አላስፈላጊ ወጪዎችን ለማስቀረት ሌሎች በርካታ መንገዶችን ማሰብ ትችላላችሁ። ለምሳሌ ያህል ‹የሠርግ ኬክ› ከምታዝዙ ይልቅ የቤተ ክርስቲያን እኅቶች እንዲያዘጋጁላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ። እንደገናም በጣም ውድ ያልሆኑትን የሠርግ ልብሶች መምረጥ ትችላላችሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ «የኃጢአት ስርየት. . . በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል» ብሎአል (ሉቃስ 24፡47)። ይህንን ተልዕኮ ለመታዘዝ ስንል ለራሳችን ብዙ እንዳናወጣ መጠንቀቅ አለብን።

«ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ. . . የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ» (ማቴዎስ 6፡19 እና 33)።

ካሌብ፡— ዛሬ የምሞት ቢሆን ምናልባትም ዘመዶቼ ሚስቴን አባርረው ገንዘብና ንብረቴን ሁሉ ሳይወስዱ አይቀሩም።

በእርግጥም የእኛን ርዳታ የሚሹ የተወሰኑ ዘመዶች እንዳሉን እኔና ሚስቴ ተስማምተናል።

ለእኔ የተሻለ የሚመስለኝ ዕቅድ፦ እኔ ስሞት ሚስቴ ገንዘቤንና ንብረቴን ሁሉ እንድትወርስ ነው። ከዚያ በኋላ የተስማማንባቸውን ዘመዶች እርሷ ትረዳለች።

በምሞት ጊዜ ገንዘቤንና ንብረቴን ሁሉ ሚስቴ እንደምትወረስ እንዴት እርግጠኛ መሆን እችላለሁ?

ውድ ካሌብ፥

ገንዘብና ንብረትህ ሚስትህ እንድትወርስ ማሰብህ መልካም ነገር ነው። ኢየሱስ « ባልና ሚስት አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም» ብሎአል (ማቴዎስ 19፡6)። አንተና ሚስትህ ‹አንድ› እስከሆናችሁ ድረስ የእርሷ የሆነ ሁሉ የአንተ ነው። የአንተ የሆነ ሁሉ ደግሞ የእርሷ ነው። አንተም ብትሞት እንኳ የእርሷ ነው። ‹አንድ› የሚለው ቃል ትርጉም ይህ ነው።

ስለሆነም ካሌብ፥ አንተ ስትሞት ምድራዊ ንብረትህ ሁሉ ለሚስትህ እንደሚሆን መረዳትህ መልካም ነው (ሩት 1፡3 እና 4፡3ን ተመልከት።)

«በምሞት ጊዜ ገንዘቤንና ንብረቴን ሁሉ ሚስቴ እንደምትወርስ እንዴት እርግጠኛ መሆን እችላለሁ?» ብለህ ጠይቀሃል።

ይህን የሚመስል «ኑዛዜ» ጽፈህ ማዘጋጀት አለብህ።

> የ________________የመጨረሻ ኑዛዜ (ስምህን አስፍር)
>
> በሞትኩ ጊዜ ንብረቴን ሁሉ ሚስቴ ________________
>
> (የእርሷ ስም) ልትወርስ ይገባታል________________
>
> (ፊርማህን አኑር) ________________ (ቀን) ________________
>
> (ምስክር እዚህ ይፈርም)________________

ኑዛዜህን ስትጽፍ ከጠበቃ ወይም ከባንክ ባለሙያዎች ምክር መጠየቅ ትችላለህ። አንዳንድ ባንኮች ነፃ ድጋፍ ይሰጣሉ።

ኑዛዜህን ጽፈህ ስታበቃ ለሚስትህ ስጣት። እንደገናም ቅጂውን ለምታምነው «ሰው» ስጠው። (ለምሳሌ መጋቢህ)።

ከአንድ መጋቢ፡- «ወጣቶች ራሳቸውን ለጋብቻ ማዘጋጀት ይችሉ ዘንድ እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?» በሚለው ርእስ ላይ ለመነጋገር ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ስብስባ አካሄደች።

በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ለአምስት ሳምንታት የሚቆይና በሳምንት ሁለት ቀን ማታ ማታ የሚሰጥ የቅድመ -ጋብቻ ትምህርት ማዘጋጀት እንዳለባት ተስማማን። ይህም ኮርስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚሰጥ ይሆናል። የጋብቻቸውን ሥርዓት በቤተ-ክርስቲያናችን ለማካሄድ ያቀዱ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ ትምህርቱን መከታተል ግዴታቸው ነው።

ትልቁ ጥያቄ «ማን ያስተምርልናል?» የሚለው ነበር። በመጨረሻ መልካም ምሳሌነት ያላቸውን አምስት ጥንዶች መረጥን። የሚሸፍኑአቸው ርእሶችም የሚከተሉት ናቸው።

1) እንዴት እውነተኛ ክርስቲያን መሆንና በብስለት ማደግ እንደሚቻል
2) ተግባቦት (ኮምዩኒኬሽን) ከባል/ከሚስት ጋር
3) ከዓመት ወደ ዓመት አንዱ ለሌላው ርኅሩኅና ታማኝ ሆኖ መቀጠል
4) ባልና ሚስት እንዴት በጋራ እግዚአብሔርን ማገልገል እንደሚችሉ
5) ፍትወተ-ሥጋ፥ እርግዝናና ልጆችን ማሳደግ

በእነዚህ በእያንዳንዱ ርእሰ-ጉዳዮች ላይ በመተቸት ልትረዱን ትችላላችሁን?

ውድ መጋቢ፥

«የቅድመ-ጋብቻ ትምህርት» አስደሳች ውጥን ነው! (ቲቶ 2፡4-8)። ሁሉንም ርእሰ-ጉዳዮቻችሁን የሚዳስስና «የጋብቻ እንቆቅልሾችና መፍትሔዎቻቸው- በብሩስና ካሮል ብሪትን» የሚል መጽሐፍ አሳትመናል። (ይህ መጽሐፍ የሚጠቅመው ላገቡ ወይም በቅርቡ ለማግባት ለተዘጋጁ ሰዎች ብቻ ነው። ገጽ 159 ተመልከት።)

ፊልሞና፡- ልያ ከተባለች ልጃገረድ ጋር ፍትወተ-ሥጋ በመፈጸሚ በኃጢአት ወድቄያለሁ። በሚቀጥለው ቀን በጣም አዘንኩ። ኢየሱስ ይቅር እንዲለኝ ጠየቅሁት። እርሱ ስለ እኔ ኃጢአት እንደሞተ አምናለሁ። እናም እንዲህ አልኩት «ከአሁን ጀምሮ ስለ ፍትወተ-ሥጋ የተደነገገውን የአንተን ሕግ መታዘዝ እፈልጋለሁ።»

ከእርሷ ጋር ፍትወተ-ሥጋ ከፈጸምኩ ከአንድ ሳምንት በኋላ ቢጫ ፈሳሽ ከብልቴ መፍሰስ ጀመረ። ወደ ሆስፒታል ሄድኩ። ነርስዋም «ጨብጥ» የሚባል በሽታ እንደያዘኝ ነገረችኝ። መርፌም አዘዘችልኝ፤ እናም አሁን ድኛለሁ።

«ጨብጥ ያጋባሽብኝ አንቺ ነሽ» ብዬ ለልያ ነገርኳት።

«እኔ በሽታ የለብኝም» ስትል መለሰችልኝ በመጠራጠር። በመጨረሻ ግን አሳመንኳት። ወደ ሆስፒታልም ሄደች። አሁን እርሷም ድናለች።

«ጨብጥ» ምንድን ነው? እባካችሁ አብራሩልኝ?

ውድ ፊልሞና፥

ጨብጥ በፍትወተ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ ነው። ሊይዝህ የሚችለው በሽታው ካለባት ሴት ጋር ፍትወተ-ሥጋ ስትፈጽም ነው።

በእርግጥ በፍትወተ-ሥጋ የሚተላለፉ በርካታ በሽታዎች አሉ። እንዲህ ዓይነቱን ማንኛውንም በሽታ ‹የአባላዘር በሽታ› ብለን እንጠራዋለን። (ይህም ማለት በፍትወተ-ሥጋ የሚተላለፍ ማለት ነው።)

ሆስፒታሎች በርካታዎቹን የአባላዘር በሽታዎች ማዳን ይችላሉ። የሆነ ሆኖ አንዳንድ የአባላዘር በሽታዎች (እንደ ኤድስ ያሉት) ፈውስ የላቸውም። እንደ አጋጣሚ አንተን ያገኘህ መዳን የሚችለው ጨብጥ በመሆኑ ዕድለኛ ነህ።

ጨብጥ የሚተላለፈው በፍትወተ-ሥጋ እንደመሆኑ ልያ በሽታው ካለበት ወንድ ጋር ፍትወተ-ሥጋ ፈጽማ እንደነበረ ያመለክታል። ከዚያ በኋላ አንተ ከእርሷ ጋር ግንኙነት ፈጸምክ። እናም በሽታው ወደ አንተም ተዛመተ።

እግዚአብሔር ከጋብቻ ውጪ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት እንዳንፈጽም ያዘናል። ይህንን ሕግ የሚተላለፉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ጨብጥ ወይም ሌላ የአባላዘር በሽታ ይይዛቸዋል።

ወንዱ ጨብጥ በሚይዘው ጊዜ ሽንቱን ሲሸና ሕመም ይሰማዋል። ከዚያም ከብልቱ ውስጥ ቢጫ ፈሳሽ መውጣት ይጀምራል። ይህ ፈሳሽ በውስጥ ሱሪው ላይ ምልክትን የሚተው ነው።

ጨብጥ የያዛት ሴት ደግሞ ከብልቷ ውስጥ ያልተለመደ ዓይነት ፈሳሽ መውጣቱን ታስተውላለች። ወይም በሆድዋ ውስጥ ሕመም ይሰማታል።

ጨብጥ የያዘው ሰው (ወንድም ይሁን ሴት) ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል መሄድ ይኖርበታል። ለሳምንት ቀርቶ አንድም ቀን መቆየት የለበትም/ባትም።

አሁን ደስ የማይል ነገር ልንነግርህ ነው።

## ጨብጥ በርካታ ሴቶችን መኻን ያደርጋቸዋል።

አንዲት ልጃገረድ መኻን ልትሆን የምትችለው እንዲህ ነው። ጨብጥ እንዳለበት ሳታውቅ ከአንድ ወንድ ጋር ፍትወተ-ሥጋ ትፈጽማለች። በዚያ ወቅት ጨብጥ ከእርሱ ወደ እርሷ ይተላለፋል። ነገር ግን ለብዙ ቀናት ይህን አትገነዘበውም። ሕመም አይሰማትም፤ ከብልቷም ያልተለመደ ፈሳሽ አይወጣም። ነገር ግን ጨብጥ በጸጥታ የመዋለጃ አካሏን እያጠቃ ነው። በመጨረሻ ግን ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ሕመም ሊሰማት ይጀምራል፤ ያልተለመደ ፈሳሽን ትመለከታለች። ከዚያ በኋላ ወደ ሆስፒታል ትሄዳለች፤ ግን በጣም ዘግይታለች። ጨብጥ ቀደም ብሎ መኻን አድርጓታል።

እንዲህ ከገጠማቸው ልጃገረዶች አንዷ በጋዜጣ የፍቅር አማካሪ ለሆነችው ሳንድራ እንዲህ ጽፋ ነበር።

ውድ ሳንድራ፥

ከአምስት ዓመት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ፍትወተ-ሥጋ ፈጸምኩ። ልጁ ጤናማ ይመስል ነበር። ምንም ዓይነት በሽታ አለበት ብዬ አልጠረጠርኩም።

ከብዙ ቀናት በኋላ ከሆዴ ሥር ሕመም ይሰማኝ ጀመር። ወደ አንዲት ሐኪም ሔድኩ። እርሷም «ወደ እኔ የመጣሽው በጣም ዘግይተሽ ነው፤ ጨብጥ የማኅፀንሽን ቧንቧ ጎድቶታል። ከዚህ በኋላ የልጅ እናት መሆን አትችይም» ብላ ነገረችኝ።

አሁን ደስ የሚል ወጣት ወንድ ሊያገባኝ ይፈልጋል። መጀመሪያ ደስ ብሎኝ ነበር፤ ዛሬ ግን ልቅሶዬን መግታት አልቻልኩም። እናቴም ከእኔ ጋር አለቀሰች። እርሷንም እንዲህ አልኳት። «እማማ እባክሽ፦ መውለድ ነገ ትነግረዋለች።

ምን እንደሚል ለመስማት ጓጉቻለሁ።

እስከ ጋብቻቸው ቀን ድረስ ፍትወተ-ሥጋ የማይፈጽሙ ልጃገረዶች ምንኛ ደስተኞች ናቸው! ሳንድራ እባክሽ ጋዜጣሽን በሁሉም ስፍራ ላሉ ልጃገረዶች ይህን ለመምከር ተጠቀሚበት።

እስከ ሠርጋችሁ ቀን ድረስ ‹አይሆንም› በሉ።

| | |
|---|---|
| እንደማልችል ለእርሱ ትነግሪልኛለሽ? እኔ ልነግረው አልችልም» | |

ፊልሞና ሆይ፥ ለልያ «ጨብጥ ከአንቺ ተጋባብኝ» ብለህ መንገርህ መልካም ነው። በሽታው እንዳለባት እንድትገነዘብ ረድተሃታል። ጨብጥ መኻን ሳያደርጋት በፊት ወደ ሆስፒታል እንድሄደች ተስፋ እናደርጋለን።

በደብዳቤህ ላይ «ኢየሱስ ይቅር እንዲለኝ ጠየቅሁት» ብለሃል፤ ኢየሱስ እንዴት ይቅር ሊልህ ይችላል? ምክንያቱም ወደ ምድር መጥቶ በአንተ ፈንታ ሥቃይን ተቀብሏል። . . . እናም በእርሱ የሚያምኑትን ይቅር ሊል ቃል ገብቷል።

ነገር ግን ኢየሱስን እንደ ጌታ እስካልተቀበልከው ድረስ እንደ ይቅርታ ሰጪ ልትቀበለው አትችልም። ስለሆነም ለእርሱ እንዲህ ብለህ መናገርህ መልካም ነው። «ከአሁን ጀምሮ ስለ ፍትወተ-ሥጋ የተደነገገውን የአንተን ሕግ መታዘዝ እፈልጋለሁ።»

> ማስታወሻ፡- ማንም ሰው ከጨብጥና ከማንኛውም እንደ ቂጥኝና ‹ኸርፒስ› ካሉ የአባላዘር በሽታዎች ራሱን ነፃ ማድረግ ይችላል። እንዴት? ልክ እንዲሁ ከኤድስም ራስህን መጠበቅ ትችላለህ። ገጽ 46 እስከ 50 ተመልከት።

ውድ አቶ እና ወይዘሮ ብሪትን፥

አሥራ ስምንት ወራት ለሚፈጅ ኮርስ ባሕር ማዶ እገኛለሁ። አሁን ችግሬ ሚስቴ ከእኔ ጋር ያለመሆኗ ነው። ሕፃኑን ልጃችንን ይዛ በአገር ቤት ነች።

ስለ ሥጋዊው ፍላጎት በወንድነቴ ምን ማድረግ እችላለሁ? እዚህ በርካታ ውብ ልጃገረዶች አሉ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ብቅ ብዬ እንዳያቸው ይጋብዙኛል። ሚስቴንና ልጄን እወዳለሁ። ግን 18 ወራት ረዥም ናቸው። ደግሞም ፍትወተ-ሥጋ ያምረኛል። ምን ባደርግ ይሻለኛል?

አቶ ብቸኛው ልትሉኝ ትችላላችሁ።

ውድ አቶ ብቸኛው፥

ወ/ሮ ብቸኚት እንዲህ ያለ ደብዳቤ ጽፋ ቢደርሰንስ ምን ማለት ይኖርብን ይሆን?

> *ውድ አቶና ወይዘሮ ብሪትን፥*
>
> *ስለ ባሌና ስለ ሕፃኑ ልጃችን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ባለቤቴ አሁን 18 ወራት ለሚፈጅ ኮርስ ባሕር ማዶ ይገኛል።*
>
> *አንዲት ወጣት ሚስት ስለ ሥጋዊ ስሜቶቿ ምን ማድረግ ትችላለች? አንዳንድ ወንዶች ባሌ ውጪ መሆኑን ሲሰሙ ብቅ ብለን እንጠይቅሽ ይሉኛል። እስከ አሁን ድረስ ‹አይሆንም› ስላቸው ቆይቻለሁ። ግን 18 ወራት ረዥም ናቸው። ደግሞም ፍትወተ-ሥጋ ያምረኛል። ምን ባደርግ ይሻለኛል?*
>
> *ወ/ሮ ብቸኚት*

ከወይዘሮ ብቸኚት የዚህ ዓይነት ደብዳቤ ብንቀበል ኖሮ እንዲህ ነበር የምንላት። «በቤትሽና በቤተ ክርስቲያን ጠንክረሽ በመሥራትና በመትጋት ኃይልሽን ተጠቀሚ። ለባልሽም ሁልጊዜ ጻፊለት። ታማኝ ሆነሽ ለመቆየት እንዴት እንደተወሰንሽ ግለጪለት። አብዝተሽ ጸልዩ። አእምሮሽን በቅዱስ ቃሉ ሙይው። ፈጽሞ አልኮል አትጠጪ። ለፈተና ከሚዳርጉ ቦታዎች ሽሺ።

እናም አቶ ብቸኛ ለአንተም የምንመልስልህ ይህንኑ ነው!

ግላዲስ፡- በጣም ፈርቻለሁ። እባካችሁ እርዱኝ፤ ታላቅ እኅቴ በእንባ እየታጠበች ነው። እንዲህም አለችኝ። «ባሌ ሊፈታኝ ይፈልጋል፤ ለምን? ምክንያቱም ልጆች አልወለድኩም።»

ለእርሷ በጣም አዘንኩ። «በእኔም ላይ ተመሳሳይ ዕጣ ቢወድቅስ?» ብዬ በማሰብ ሌሊት መተኛት አልቻልኩም።

እድሜዬ ወደ 19 እየተጠጋ ነው። የሚጠይቁኝን ወንዶች ሁሉ «አይሆንም» እላቸዋለሁ። ነገር ግን አሁን ለአንዱ ሰው ‹እሺ› ማለት ሊኖርብኝ ነው። ምክንያቱም «መውለድ እችል ይሆንን?» የሚለው ጥያቄዬ ምላሽ ያሻዋል።

ውድ ግላዲስ፥

ለአንዱ ወንድ «እሺ» ብትዪ ምናልባትም የአባላዘር በሽታ ሊይዝሽ ይችላል። (ለምሳሌ፡- ጨብጥ) እናም ያ በሽታ የመውለጃ አካሎችሽን ሊያጠቃ ይችላል። አዎን አንዳንዴ ማርገዝ መቻሏን የምታጣራ ልጃገረድ እድሜ ልኳን መኻን ልትሆን ትችላለች!

ግላዲስ አስተውዬ። ልታደርጊው የምትችይው የተሻለው ነገር ኢየሱስ የሕይወትሽ አዳኝና ጌታ እንዲሆን መጠየቅ ነው። እርሱም ይቅር ይልሻል፤ የዘላለም ሕይወትንም ይሰጥሻል።

ከዚያ በኋላ እንዲህ ልትይው ትችያለሽ፤ «ጌታ ሆይ፥ አንተ ወዳጄና አፍቃሪ አባቴ ነህ። ልጅ መውለድ ባልችል ባሌ ቢሞት ወይም ምንም ነገር ቢከሰት ሁሌም አንተ ከእኔ ጋር ትሆናለህ።»

«በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፤
አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤. . .
በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ»

[መዝሙር (24)፥4 ና 6]።

ግላዲስ ጌታን ከተቀበልሽ በኋላ እባክሽ እኅትሽም ይህንኑ እንድታደርግ እርጃት። ከዚያ በኋላ ባሁኑ ሰዓት እርሷ ባለችበት የጨለማ ሸለቆ ውስጥ እርሱ አብሯት ይሆናል።

ካረን፡- ጓደኞቼ እንዲህ በማለት መከሩኝ፤ «ከወንድ ጋር ለመተኛት ፈቃደኛ ካልሆንሽ ዕድሜ ልክሽን ባል አታገኚም፤ ወንዶች እንዲትን ልጃገረድ ለማግባት ከመወሰናቸው በፊት ሊፈትኗት ይፈልጋሉ።»

እኔ ግን ክርስቲያን ነኝ። ምን ማድረግ አለብኝ?

ውድ ካረን፥

እግዚአብሔርን ታዘዢ! የጓደኞችሽን ምክር አትስሚ። እየተናገሩ ያሉት እውነት አይደለም።

ከታች በተመለከተው ሥዕል ወጣቱ የትኛዋን ልጃገረድ እንደሚመርጥ አስቢ።




ሁለት እውነታዎች እነሆ፡-

ሀ) በምድራችን ባሉ የትኞቹም አገሮች ወንዶች ድንግል የሆነች ልጃገረድን ማግባት ይወዳሉ።

ለ) ብዙ ወጣት ወንዶች ለግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ‹አይሆንም› እያሉ ነው፤ ይህም ጋብቻን በንጽሕና ለመጀመር እንዲችሉ ነው።

ማንም የፈለገውን ይበል እንጂ እነዚህ ሁለት እውነታዎች ሐቅ ናቸው። አዎን፥ እግዚአብሔር በየዕለቱ እንዲህ የሚጸልየውን ወጣት ይሰማል።




ስለሆነም ካረን ጓደኞችሽ የሚሉትን ሳይሆን እግዚአብሔርን እመኚ።

> «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል» (ምሳሌ 3፥5–6)።

**አኒ፡–** ደስ የሚሉ ባልና ሚስት (ሉቃስና ሻሮን) በወጣቶች ፕሮግራማችን ላይ ሰበኩ። ሉቃስም እንዲህ አለ «እኔና ሻሮን ከመጋባታችን በፊት አንድ ቀን በውበቷ ተሳብኩና . . . የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንድንፈጽም ጠየቅኋት። ምላሿ ቀጥተኛና ‹አይሆንም› የሚል ነበር። በሚቀጥለው ቀን ወደ አእምሮዬ ተመልሼ እንዲህ አልኩ ‹እንቢ በማለቷ ደስተኛ ነኝ! ከኃጢአት አዳነችኝ። እንዴት ያለች ጥሩ ልጃገረድ ነች! ማስታወሻ ልጽፍላት ይገባኛል»።

ከዚያ ሻሮን፥ ብድግ ብላ፥ የጻፈላትን ማስታወሻ አሳየችን፤ በእነዚህ ዓመታት ሁሉ መካከል አኑራው ነበር። እንዲህ ይላል።

*የምወድሽ ሻሮን፥*

*ባቀረብኩት ጥያቄ አዝኛለሁ። ብርቱ ፈተና ገጥሞኝ እንጂ ማንንም ልጃገረድ ጠይቄ አላውቅም! ለመጠየቅም አላሰብኩም። «አይሆንም» በማለትሽ አመሰግንሻለሁ። እወድሻለሁ!*

ሁላችንም ወጣቶች እውነተኛ ምስክርነታቸውን ወደድነው። የእኔ ችግር ግን በጣም የምወደው የወንድ ጓደኛ ያለኝ መሆኑ ነው። እርሱ ቢተወኝ፥ እሞታለሁ! አንድም ቀን ለግብረ-ሥጋ ግንኙነት ጠይቆኝ አያውቅም። ግን ቢጠይቀኝ ምን ባደርግ ይሻለኛል?

ሻሮን፡- «አይሆንም!» ስትል ሉቃስ ጥሎአት አለመሄዱ ደስ የሚል ነገር ነው። ነገር ግን አንዳንድ ወንዶች ለግብረ-ሥጋ ግንኙነት እንቢ ያሉአቸውን ልጃገረዶች መተዋቸው እውነት አይደለምን?

ውድ አኒ፥

አዎን፥ ለግብረ-ሥጋ ግንኙነት እንቢ ያለቻቸውን ልጃገረድ ጥለው የሚሄዱ ወንዶች አሉ። እንዲህ የሚያደርጉ ወንዶች ምን ዓይነት ናቸው? የሚከተሉት ናቸው፡-



ስሚ አኒ፡- የዚህ ዓይነቱ ወንድ ጥሩ ባል ሊሆን አይችልም። ስለዚህ እርሱ ጥሏት የሄደ ልጃገረድ ዕድለኛ ናት።

በዚያ ወቅት ዕድለኛነቷን ላታስተውል ትችላለች። ነገር ግን በመጨረሻ እንደ እግዚአብሔር ምርጫ ለእርሷ የሆነውን ወጣት ስታገኘው እንዲህ እያለች ሁልጊዜ ማሰላሰሏ አይቀርም።

«ለዚያ ሰው እሺ ብዬው ቢሆን ምን በዋጣኝ. . . ወይም አግብቼው ቢሆን»

አኒ ጥያቄሽ «ለግብረ-ሥጋ ግንኙነት ቢጠይቀኝ ምን ማድረግ እችላለሁኝ» የሚል ነበር። ምላሹ፡-

**ከጋብቻ በፊት ‹አይሆንም› በዪ**



- ትቶሽ ከሄደ ጥሩ ባል የሚወጣው ሰው እንዳልሆነ የሚጠቁም ምልክት ነው።



- እውነተኛ ክርስቲያን ከሆነ ግን ስሜቱ ከበረደ በኋላ ‹አይሆንም› ስለማለትሽ ያመሰግንሻል።

ደስታ፡- ዕድሜዬ 14 ነው። ከ24 ዓመት ወጣት ጋር ድብን ያለ ፍቅር ይዞኛል። «ግንኙነት የምናደርገው በየዕለቱ ስላልሆነ አታረግዢም» ይለኛል።

ውድ ደስታ፥

አንድ ወንድ አንቺን ለማስረገዝ የግድ በየቀኑ ካንቺ ጋር መገናኘት አያስፈልገውም። ብዙ ልጃገረዶች በመጀመሪያው የፍትወተ-ሥጋ ግንኙነት ያረግዛሉ። እንደ አንቺ ያሉ በእድሜ ለጋ (ዕድሜሽ 14 ስለሆነ) ልጃገረዶች ካረገዙ ደግሞ በአብዛኛው በሚወልዱ ጊዜ ወይ ሕፃኑ ወይም እናቲቱ አንዳቸው ይሞታሉ።

«የ24 ዓመቱ ወጣት» ይተውሽ ዘንድ እንዲነግሩት ለአባትሽ (ወይም ለመጋቢሽ) ንገሪያቸው።

ሎይስ፡- አሮን እና እኔ የአንድ ቤተ-ክርስቲያን አባላት ነን። ሁለታችንም ለሦስት ዓመታት በወንጌል ስርጭት ቡድኑ ውስጥ አብረን አገልግለናል።

አንድ ቀን ማለትም ከስድስት ሳምንታት በፊት በእርሱ መኝታ ቤት አብረን ነበርን። ለብቻችን ስንሆን ይህ የመጀመሪያ ጊዜያችን መሆኑ ነው። አንዳችን የሌላውን መንካት የማይገባንን ስፍራ መነካካት ጀመርን። (ሁለታችንም ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት ድርጊት ፈጽመን አናውቅም።)

ይህ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ክፉ እንደነበረ እናውቃለን። ስለዚህ በጉዳዩ ላይ ጸለይን፤ ለሁለት ሳምንታትም እንዲያ አላደረግንም።

ቆይተን እንደገና ተመለስንበት። . . . መነካካት. . . ብሎም አንዳንድ ልብሶቻችንን ማወላለቅ ቆይቶም በበደለኝነት ስሜት መጀበን ቀጠልን። ከወንጌል ስርጭት ቡድን ጋር ማገልገላችንን አቆምን። አሁን የምንካፈለው በእሑድ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ ብቻ ነው።

ባለፈው ምሽት በጣም ርቀን ተጓዝን። በዚያም ልብሳችንን በሙሉ አወለቅን። ከዚያ በኋላ እርሱ የዘር ፈሳሹን በእኔ ብልት አጠገብ እጅግ ቀርቦ አፈሰሰ።

አሁን ከጭንቀት እፎይ ማለት አልቻልኩም። ምናልባትም አርግዤ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም የዘር ፈሳሹ ከብልቴ ከናፍርት ወደ ብልቴ ውስጥ ዘልቆ ሊሆን ይችላል።

በዛሬው ቀን አሮንና እኔ ረዘም ያለ ውይይት አካሄድን። የገላ ንክኪዎችን በሙሉ እንደምናቆም እርስ በርሳችን ቃል ገባን። እናም እስከምንጋባ ድረስ ፈጽሞ ወደ እርሱ መኝታ ክፍል አልገባም።

የንጽሕና ኑሮ ለመኖርና እግዚአብሔርን ለማገልገል እንፈልጋለን።

ግን በጣም ርቀን የሄድን ስለመሰለኝ እጅግ ፈርቻለሁ። እባካችሁ እርዱን።

> ማስታወሻ፡- ምናልባትም ሎይስ እርጉዝ ልትሆን ስለምትችል "Kiss me, Sweet Baby" ወይም «ተወዳጇ ሕፃን፥ ና ሳመኝ»፤ የሚለውን መጽሐፍ እንድታነብ አበረታታናታል። (ገጽ 159) እንደገናም እርሷና አሮን ቃል የገቧቸውን ነገሮች ማለትም ከመኝታ ክፍል ውጪ መቆየት . . . አካላዊ ንክኪን ማቆም. . . የንጽሕና ሕይወት መኖር . . . እናም እግዚአብሔርን ማገልገል የሚሉትን እንዲጠብቁ በጥብቅ መከረናቸዋል።

አቤሴሎም፡- ከአንዲት እኅት ጋር ትኩስ ፍቅር ጀምሬ ነበር። ትታኝ እስከሄደችበት ቀን ድረስ እንደምትወደኝ ሳስብ ቆይቻለሁ! ትታኝ መሄዱ ታላቅ የልብ ስብራት ሆኖብኛል! ነገር ግን ከእርሷ ጋር የግብረ - ሥጋ ግንኙነት ባለመፈጸሜ እግዚአብሔር ይመስገን!

ከስድስት ወራት በኋላ ከሳንድራ ጋር ተዋወቅሁ። በጣም እወዳታለሁ። እርሷም ክርስቶስንና እኔን ትወዳለች።

በሚቀጥለው ዓመት ለመጋባት ዐቅደናል። አሁን የበፊቷ ልጃገረድ ጥላኝ ስለሄደች እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ሳንድራና እኔ አንድ ልብ አንድም አእምሮ አለን፤ ከእርሷ ጋር ስንንሸራሸር፥ ስናወራና ስለ ችግሮቻችን ስንወያይ በጣም ደስ ይለኛል!

ድንግልናችንን እስከ ሠርጋችን ዕለት ለመጠበቅ አንዳችን ለሌላችን ቃል ገብተናል።

ሰውነትዋን አልነካም። በጣም ቆንጆ ናት፤ ልነካት ከጀመርኩኝ ልብሷን ለማወላለቅ መፈተኔ እንደማይቀር አውቃለሁ። ከዚያም በኋላ. . .

ጥያቄዬ ግን የማልነካት ስለሆነ ለእርሷ ያለኝ ፍቅር ጠንካራ መሆኑን ትጠራጠር ይሆን የሚል ነው። አጣት ይሆን?

ውድ አቤሴሎም፥

በእግዚአብሔር ታመን! እግዚአብሔር ለአንተ ከዚህ የተሻለ ዕቅድ እስከሌለው ድረስ ሳንድራን አታጣትም (ኤርምያስ 29፡11)።

በቅንነት እንዲህ በላት። «በጣም ቆንጆ ነሽ! ልነካሽ ከጀመርኩኝ ልብስሽን ለማወላለቅና የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም እፈተናለሁ፤ ነገር ግን ይህንን እስከ ሠርጋችን ዕለት ለመፈጸም አልፈልግም።»

አቤሴሎም በደብዳቤህ ላይ «ከእርሷ ጋር ስንንሸራሸር፥ ሳናወራና ስለ ችግሮቻችን ስንወያይ በጣም ደስ ይለኛል!» ብለሃል። ያ ጥሩ ነገር ነው! ከተጋባችሁ በኋላም እንዲህ ማድረጉን ቀጥሉ። ከሚስትህ ጋር መነጋገር ደስ እንደሚያሰኝህ ሰዎች ቢያውቁ ይህ አያስፈራህ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዲህ የምትል ደስተኛ ሚስት እናገኛለን። «ወደ ወይን ጠጅም ቤት አገባኝ፥ በእኔ ላይ ያለው ዓላማውም ፍቅር ነው» (መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 2፡4)።

ቤትሪስ፡- ዕድሜዬ 23 ሲሆን ከአንድ ወንድ ሁለት ልጆች ወልጃለሁ። ባለፈው ዓመት ግን ጥሎን ሄደ።

አሁን ሌላ ሰው ሊያገባኝ ይፈልጋል። በጣም ደስ የሚል ሰው ነው፤ ነገር ግን ልጆቼን አይፈልጋቸውም።

«ልጆቼ ከማን ጋር መኖር ይችላሉ?» እያልኩ በየዕለቱ ራሴን እጠይቃለሁ። ተገቢ እንክብካቤ ከማያደርግላቸው ከማንኛውም ሰው ጋር እንዲቆዩ አልፈልግም። ስለሆነም ምን ላደርግላቸው እችላለሁ?

ውድ ቤትሪስ፥

ልጆችሽን ትተሽ አትሂጂ። እየወደድሻቸው ከእነርሱ ጋር የመኖር ኃላፊነት አለብሽ። ያን ኃላፊነት ለአንድ ሌላ ሰው ለመስጠት አትሞክሪ፤ እናታቸው አንቺ ነሽ።

የልጆችሽ አባትም እኩል ኃላፊነት አለበት። እግዚአብሔር ልጆቻቸውን የማይወዱና በሥርዓት የማያንፁ አባቶችን ይቀጣል።

> ልጆቹን ከክፉ ነገር ባለመከልከሉ እግዚአብሔር ዔሊን ክፉኛ ቀጥቶታል (1ኛ ሳሙኤል 3:11–13 ተመልከች)።

አሁን ደግሞ ሊያገባሽ ስለሚፈልገው «በጣም ደስ የሚል ሰው» እንነጋገር። ቤትሪስ እባክሽ በጥንቃቄ አስቢ። በእውነት ይወድሻልን? ስለሚያስፈልግሽ ነገር ያስባልን? ልጆችሽን ለማሳደግ ምን እንደሚያስፈልግሽስ ያውቃልን?

**የሚወድሽ መሆኑ እንደሚያጠራጥረን ልንነግርሽ ግድ ይሆንብናል።**

ቤትሪስ ልጆችሽን የማይቀበለውን ማንኛውንም ሰው አታግቢ። ይልቁንም ፊትሽን ወደ ሰማያዊው አባት መልሺ። ኃጢአትሽን ያስተሰርይ ዘንድ ልጁን ለመሥዋዕት እንዳቀረበው እመኚ። ልጆችሽን በመንከባከብ ለእርሱ ታዘዢ።

እግዚአብሔር እንዲሁ በብቸኝነት የምትኖሪበትን ብርታት ይሰጥሻል። ወይም ልታገቢው የሚገባሽን ትክክለኛ ሰው ወደ አንቺ ያመጣል።

እርሱን ስታገለግዪውና ልጆችሽን ስትንከባከቢ እግዚአብሔር ደግሞ አንቺን ይንከባከብሻል። አንቺ የእርሱ ልጅ ነሽና።

አንዳንድ አባቶች ልጆቻቸውን ትተው ይሄዳሉ። ሰማያዊ አባትሽ ግን «አልተውሽም» ይላል (ዕብራውያን 13:5)።

ጢሞቴዎስ፡- ልያን ለማግባት እፈልጋለሁ። ችግሩ ግን ልጅ አላት። ሕፃኑ ሁለት ዓመት ሆኖታል። አባትየው ስለማይፈልገው ልጁ ከእርሷ ጋር ይኖራል።

ከረዥም ጊዜያት በፊት ልያ ኃጢአቷን ለቤተ ክርስቲያን ተናዝዛ የተወሰነባትን የሥነ-ሥርዓት ቅጣት ተቀብላለች። አሁን በእሑድ ት/ቤት በማስተማርና ስደተኞችን በመርዳት እየተጋች ነው።

እወዳታለሁ፤ ነገር ግን ሁልጊዜ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አለብኝ «ከሌላ ሰው የወለደችን ሴት ማግባት እችላለሁን?»

ምን ማድረግ ይገባኛል?

ውድ ጢሞቴዎስ፥

ይቅር በላት (ቆላስይስ 3፡13)። ከዚያ በኋላ ለእርሷ ያለህ ፍቅር መመዘኛዎቹን ሁሉ የሚያልፍ ሆኖ ካገኘኸው (ገጽ 25-33) ስለ ጋብቻ ጉዳይ አነጋግራት። ልጁን እንደምትወደው፥ እንደምታስተምረውና እንደ ራስህ ልጅ እንደምታየው ቃል ግባላት። ከዚያም ያንን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ተጠንቀቅ!

ግሎሪያ፡- ክርስቶስን ከልቤ እወዳለሁ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። ማግባት ወይስ ሳላገባ መኖር. . .

ለምን አገባለሁ? ለምንስ ሳላገባ እኖራለሁ?

ውድ ግሎሪያ፥

ሳያገቡ መኖር የሚመረጥበት አንድ ጥሩ ምክንያት አለ። ያም ደግሞ፥ የክርስቶስን ወንጌል እርሱም መልካሙን የምሥራች ለራስሽ አገር ሰዎችና ለሌሎችም ሕዝቦች ለማሰራጨት ጊዜሽን መጠቀም ነው።

ማግባት የሚፈለግበት አንድ ጥሩ ምክንያት አለ። ያም ደግሞ አንቺና ባለቤትሽ የክርስቶስን ወንጌል መልካሙን የምሥራች ለሕዝባችሁና ለሌሎችም አገሮች ለማሰራጨት በጋራ እንድትሠሩ ነው።

ስለሆነም ግሎሪያ፥ ሳታገቢ ለመኖር ከወሰንሽ በሕይወትሽ እያንዳንዱን ቀንና ሰዓት ለክርስቶስ መንግሥት አውዪው (1ኛ ቆሮንቶስ 7፡32-35)።

ለማግባት ከወሰንሽ ደግሞ መልካሙን የምሥራች ለማሰራጨት ከአንቺ ጋር መሥራት ደስ የሚያሰኘውን ጓደኛ ለመምረጥ ተጠንቀቂ (2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14)።

"Arise Boldly with Power" ወይም «ኃይልን ለብሰህ በድፍረት ተነሣ» የሚለውን መጽሐፍ ብታነቢ በጣም ይጠቅምሻል (ገጽ 159 ተመልከቺ።)

ማርቆስ፡- ከአራት ዓመታት በፊት ጵርስቅላ የተባለችውን ብርቱ ክርስቲያን ልጃገረድ ተዋወቅሁ። ጊዜው እየገፋ ሲሄድም ለእርሷ ያለኝ ፍቅር አደገ። በጣም ብዙ ነገሮችን ተወያየን። የሚያስፈልገኝን ታውቃለች። እኔም የእርሷን።

ብዙ ጊዜ ስለ ቤተሰቦቻችን እየጸምን እንጸልያለን፤ ከክርስትና ውጪ ሆነው አስከፊ ሕይወትን ይገፋሉና።

በበዓላት ቀን «የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በየዕለቱ» የተሰኘውን ትምህርት ለሕፃናት የሚያቀርቡትን እኅቶች እንረዳለን።

እርሷ ለእኔ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነች ውድ ስጦታ ነበረች። በመንፈሳዊ ነገሮች እንዳድግም ረድታኛለች። ብዙ ጊዜ ተንበርክኬ ጌታን ስለ እርሷ አመሰግኛለሁ።

ትናንትና በእግራችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ሳለ እርሷን የማናግርበት መልካም አጋጣሚ አገኘሁ። ለእርሷ ያለኝን ፍቅርና እንዳገባትም ያለኝን ትልቅ ፍላጎት ገለጽኩላት።

አዳመጠችኝ፤ ነገር ግን ብዙም አልተናገረችም።

ዛሬ ጧት ስልክ ደውላ እንዲህ አለችኝ። « እባክህ ለእኔ ስለ ፍቅር አታውራልኝ፤ ለሌላ ሰው የጋብቻ ቃል ኪዳን አድርጌያለሁ።» አዘንኩ። ተደነቅሁ።

እንዴት እንደደነገጥኩማ አይነሣ!

አሁንም በሙሉ ልቤ እወዳታለሁ። ሌላ ሰው ልታገባ ትችላለች ብዬ አላምንም። ምንም እንኳ እርሷ በቀጥታ የመለሰችልኝ ቢሆንም አሁንም በእግዚአብሔር ላይ እምነት አለኝ። እንዲህ ዓይነት ነገር እኔ በምወዳት ልጅ ላይ እንዲደርስ ማለትም ሌላ ሰው እንድታገባ እግዚአብሔር እንደማይፈቅድ አውቃለሁ። እርሷ ከጌታ ለእኔ የተላከች ልዩ ስጦታ ናት።

በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳለኝና እንደማገባትም ዛሬ ነገርኳት። በእግዚአብሔር የሚታመኑ ሁሉ እንደማያፍሩ ደግሞ አውቃለሁ።

ውድ ማርቆስ፥

መጽሐፍ ቅዱስ ዮሴፍ እንዴት ለባርነት ወደ ግብፅ እንደተሸጠ ይነግረናል (ዘፍጥረት 39፡1-21።) ተስፋ መቁረጥ ተሰምቶት ነበርን? በጣም! ግን ከብዙ ዓመታት በኋላ ለወንድሞቹ እንዲህ አላቸው።

«እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሆነው ቤተሰባችን በግብፅ ሕያው ይሆን ዘንድ አሰበው» (ዘፍጥረት 50፡20)።

አየህ ማርቆስ ልክ ዮሴፍ እንዳደረገው አንተም በእግዚአብሔር መታመን ይኖርብሃል። እርሱ ሕይወትህን ለመልካም እንዳቀደው እመን።

ምናልባትም ጵርስቅላ ያኛውን ሰው ታገባ ይሆናል። አዎን፥ ያ ሊከሰት ይችላል። እናም እንዲህ ከሆነ በጣም ተስፋ ትቆርጥ ይሆናል።

ታዲያ ምን ማድረግ ትችላለህ? ለጋብቻህና ለእያንዳንዱ የሕይወትህ መስመር እግዚአብሔር የተሻለ ዕቅድ እንዳለው እመን።

«እንደማገባት በእግዚአብሔር ላይ እምነት አለኝ» ብለሃል።

ማርቆስ፡- ይህ አባባልህ በእግዚአብሔር ላይ ያለህን እምነት አያመለክትም። በራስህ ላይ እየታመንክ ነው። «ለእኔ መልካም የሆነውን ዕቅድ አውቃለሁ፤ እግዚአብሔር ሆይ፥ እባክህ የእኔን ፈቃድ ፈጽም» እያልክ ነው።

እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል።

«ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም» (ኤርምያስ 29፡11)።

«የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ» እያልን እንድንጸልይ ኢየሱስ አስተምሮናል» (ሉቃስ 22፡42)።

ማርቆስ አንተ ጥሩ ክርስቲያን ነህ። በእግዚአብሔር ትታመናለህ ግን አድምጥ፤ በእግዚአብሔር የበለጠ መታመን አለብህ።

በራስህ ላይ ከምትታመነው የበለጠ በእርሱ መታመን ያስፈልግሃል። እንዲህ ብለህ መጸለይም ይገባሃል።



አቤል፡- አንጂላ የምትባል ልጅ ወድጄ በፍቅሯ ማበዴ ነው። እናቴ እንኳ ተቀብላት እርሷን እንዳገባ ተስፋ ታደርጋለች።

ነገር ግን ይህችን ልጅ ላነጋግራት ስሞክር «አቶ ትክክል የራሴ የሆነ ሰው ነው፤ የማገባውም እርሱን ነው» ትለኛለች።

በምንም መንገድ አሳቧን ላስቀይራት ብሞክርም ልትሰማኝ እንኳ አትፈልግም።

ለእርሷ ያለኝ ፍቅር ብርቱ ነው። አሁኑኑ የእርሷ «አቶ ትክክል» ሳይወስዳት በፊት ላገባት እፈልጋለሁ።

ቀኑን ሙሉ የማስበው በምሽትም የማልመው ይህን የፍቅር ከንዋኔ ነው። በመጀመሪያ ካየኋት ቀን አንሥቶ ክብደቴ ቀንሷል። ልቤም በሽተኛ ሆኗል። እርሷን በፍቅር ካላሸነፍኩ ምን እንደምሆን መገመት ያዳግተኛል። ራሴን ብገድል ነው የሚሻለኝ።

እንድትወደኝ ለማድረግ ‹መስተፋቅር ወደሚደግሙ› ሰዎች መሄድ ይኖርብኝ ይሆን? ካላገኘኋትና የራሴ ካላደረግኋት ማበዴ ነው።

ውድ አቤል፥

አንድ ወደ አእምሮህ ያልመጣ አሳብ ቢኖር ‹በእግዚአብሔር ልታመን› የሚል ነው። ምናልባትም እንዴት ክርስቲያን መሆን እንደምትችል የነገረህ ሰው አይኖር ይሆናል።

«እኔ የምፈልገው አንጂላን ብቻ ነው፤ ስለ እግዚአብሔር መስማት አልፈልግም» ትል ይሆናል። ነገር ግን አሁን ከዚህ ቀጥሎ የምነግርህ ነገር ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው።

> በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም (ዮሐንስ 3፡36)።

አቤል፥ እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ለአንተ ሲል ወደ ምድር ላከው። አንተ ስለ ሠራኸው ኃጢአት ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሠቃየ። የዘላለምን ሕይወት ልትቀበል የምትችልበት ብቸኛ መንገድ ከኃጢአት መመለስና በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ይቅርታን ልትቀበል እንደምትችል ማመን ነው። ያንን ስታደርግ እውነተኛ ክርስቲያን ከመሆንም በላይ የመንግሥተ ሰማያትንም ተስፋ ትቀበላለህ።

እግዚአብሔር አንጄላን ይሰጥህ ይሆን? ምናልባት–አልያም ሌላ የተሻለች ሴት ለአንተ ይኖረው ይሆናል።

አንተ ክርስቲያን ከሆንክ በኋላ ለአንጄላ እንዴት የዘላለምን ሕይወት መቀበል እንደምትችል ልትገልጽላት ትችላለህ፤ ምናልባትም ክርስቲያን ለመሆን ትወስን ይሆናል። እናም ምናልባት ሚስትህ ትሆን ይሆናል። ነገር ግን አንተን ላለማግባት ብትወስን አትጨነቅ። ራስህን አትግደል። እንደገናም ትወድህ ዘንድ መስተፋቅር ደጋሚ ዘንድ አትሂድ (ዘሌዋውያን 19–31፤ ዘዳግም 18፡9፡14፤ 2ኛ ነገሥት 23፡24፤ ኢሳይያስ 8፡19)።

በእግዚአብሔር ብቻ እመን። አንተ በዚህ ሰዓት በምድር ላይ ካሉ ልጃገረዶች ሁሉ አንጄላ የተሻለች ነች ብለህ ታስባለህ። ነገር ግን በምድራችን ላይ ያሉትን ልጃገረዶች ሁሉ አታውቃቸውም። እግዚአብሔር ያውቃቸዋል። በእርሱ እመን። አገልግለው፤ ታመነው።

ፊልጶስ፡– ዛሬ በአውቶቡስ ወደ ሥራ ስሄድ አንድ ሰው ስለ ክርስቶስ ነገረኝ። ሳዳምጠው ሳለ ኃጢአተኛ መሆኔን ተገነዘብኩ። እዚያው ቦታ ላይ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኜ ለመቀበል ወሰንኩ።

ዋነኛው ጥያቄዬ ይህ ነው። አሁን እኔ ክርስቲያን ነኝ። ከዝሙት ኃጢአት ርቄ መኖር እችላለሁ?

ውድ ፊልጶስ፥

አዎን፥ ትችላለህ!

ጌታን ከመቀበልህ በፊት በየዕለቱ ኃጢአት ይቆጣጠርህ ነበር። ነገር ግን በዚያ አውቶቡስ ላይ እግዚአብሔር ኃጢአትህን ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስንም ሰጥቶሃል።

ፊልጶስ *"What the Bible really says about the Power of the Holy Spirit"* ወይም «የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥ ምን ይላል?» የምትል አነስተኛ መጽሐፍ በአድራሻህ ልከንልሃል። ያንን ካነበብክ በኋላ «በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ድል አድራጊ መሆን እችላለሁ!» ወደሚል መረዳት ትደርሳለህ።

ማስታወሻ ለአንባቢያን፡– ለፊልጶስ የላክንለትን አነስተኛ መጽሐፍ ማግኘት ትፈልጋላችሁ? እንግዲያው ደስ ይበላችሁ! በሚቀጥለው ገጽ የዚያችን አነስተኛ መጽሐፍ ነፃ ቅጂ ታነባላችሁ!

«በወጣቶች የሚነሡ ጥያቄዎች» በሚለው መጽሐፋችን ላይ ይህን ቅጂ ስናካል ዋጋውን ግን አልጨመርንም። ስለዚህ በእርግጥም ነፃ ቅጂ ነው ማለት ይቻላል።

# የመንፈስ ቅዱስን ኃይል

## በተመለከተ

## መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥ ምን ይላል?

> የጸሐፊው ማስታወሻ፦ በተለያዩ የዓለም ክፍል እየተዘዋወርኩ ሳስተምር ከቀድሞ ተማሪዎቼ በርካታ አስደናቂ ደብዳቤዎችን ተቀብያለሁ። ይህንን አነስተኛ መጽሐፍ ሳዘጋጅ ‹ዮሴፍ› ብዬ የሰየምኩትን ሰው ተያያዥ ደብዳቤዎች ለመፍጠር ብዙ ወጣቶች የጻፉልኝን ደብዳቤዎች በማዋሃድ ተጠቅሜያለሁ። ጸሎቴም እንዲህ የሚል ነው «ጌታ ሆይ፥ ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ ያነበበ ሰው ሁሉ ለድል የሚያበቃውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሞላ።»

ውድ አቶ ብሪትን

ምናልባትም ታስታውሰኝ ይሆናል። በምታስተምረው የኬሚስትሪ ክፍለ- ትምህርት በጣም ደስተኛ ነበርኩ። ነገር ግን ምሳ ሰዓት ላይ መጽሐፍ ቅዱስን ስታስጠና አንድም ቀን መጥቼ አላውቅም። አሁን በአንድ የንጥረ-ነገሮች ቤተ ሙከራ ውስጥ ተቀጥሬ እሠራለሁ። እና ልብ በል፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኜ ተቀብያለሁ፤ የውኃ ጥምቀትንም ወስጄ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባል ሆኛለሁ።

አዎን፥ ጸሎቶችህ ተሰምተዋል!

ነገር ግን የክርስትና ሕይወቴ እንደሚገባ እያደገ አለመሆኑን ልነግርህ ይገባኛል፤ በቂ ድል ወይም ደስታን አልጨበጥኩም።

ለእኔም ለመጻፍ ጊዜ እንደሚኖርህ ተስፋ አደርጋለሁ።

በእርግጥ የአንተው

ውድ ዮሴፍ፥

ደብዳቤህ በእውነቱ ዕለቱን ብሩህ አድርጎልኛል!

ተስፋ መቁረጥ ቢጫጫንህም እኔን አይደንቀኝም። ይህ ሁልጊዜ የሚያጋጥም ነው። ልረዳህ ደስተኛ ነኝ።

«ታላቁ ጥያቄ» የተባለውን አቅርቤልህ ልጀምር።

ታላቁ ጥያቄ

በእግዚአብሔር ፊት ብትቆምና እርሱ

*«ስለ ምን ወደ መንግሥተ ሰማይ እንድትገባ ልፍቀድልህ?»*
ብሎ ቢጠይቅህ ምን ምክንያት ታቀርባለህ?

በዚህ ደብዳቤዬ ላቀርብልህ የምወደው ጥያቄ ይህን ብቻ ነው። በሚቀጥለው ደብዳቤህ ብሩስ ብለህ ብቻ ጥራኝ።

እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን

ብሩስ

ውድ ብሩስ፥

ስለምላሽህ አመሰግንሃለሁ። ያቀረብክልኝ ጠጣር ጥያቄ በጥልቀት እንዳስብ ያስገደደኝ መሆኑን ልገልጽልህ ይገባኛል! መልሴ ያረካህ እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። እርሱም ይኸው፡-

ለታላቁ ጥያቄ የእኔ ምላሽ

እግዚአብሔር
*«ስለ ምን ወደ መንግሥተ-ሰማይ እንድትገባ ልፍቀድልህ?»*
ብሎ ቢጠይቀኝ ምላሼ እንዲህ ነው።
*«ለመንግሥተ-ሰማያት የምበቃ አይደለሁም፤*
*በእርግጥም የሚገባኝ ገሃነም ነው።*
*ግን ወደ መንግሥተ-ሰማያት ልገባ የምችልበት አንድ ምክንያት አለ።*
*ያም ኢየሱስ ስለ ኃጢአቴ በእኔ ፈንታ መሠቃየቱና*
*እኔም በእርሱ ለማመን መምረጤ ነው።» (ዮሐ. 3፥16)*

ውድ ዮሴፍ:

*እጅግ በጣም ጥሩ* መልስ ነው! በአሜሪካ፥ አፍሪካ፥ አውሮፓና እስያ ለሚኖሩ በርካታ ሰዎች ይህንን ጥያቄ አቅርቤያለሁ። አንድ ሰው በእርግጥ ክርስቲያን መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው።

እውነተኛ ክርስቲያኖች ያልሆኑ ሰዎች በተለምዶ እንዲህ ይላሉ፡—

«ጥሩ ሥራዎች ለመሥራት ስለምሞክር፥ ቤተ ክርስቲያን ስለ ማዘወትርና አብዛኛዎቹን ኃጢአቶች ላለመፈጸም ስለምጥር እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ—ሰማያት እንድገባ ይፈቅድልኛል ብዬ አስባለሁ።»

ነገር ግን እውነተኛ ክርስቲያኖች ልክ እንደ አንተ ይመልሳሉ። ዮሴፍ፥ እውነተኛ ክርስቲያኖች በራሳቸው መልካም ሥራ አይታመኑም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ሥራ ያምናሉ።

እውነተኛ ክርስቲያኖች «ጥሩ ሥራ በመሥራት መንግሥተ—ሰማይን ለማግኘት ተስፋ አደርጋለሁ» አይሉም። ይልቁንም ኃጢአተኝነታቸውን በማመን «ሥቃይ ይገባኛል፤ ነገር ግን ኢየሱስ ስለ እኔ ሥቃይን ተቀብሏል» ነው የሚሉት።

ዮሴፍ፥ አሁን ሦስት ነገሮችን ልነግርህ እችላለሁ፡—

1) ክርስቲያን ነህ። ለታላቁ ጥያቄ የሰጠኸው ምላሽ ኢየሱስ አንተ ለፈጸምከው ኃጢአት የመሞቱን እውነታ እንደምታምን ያሳያል።

2) ክርስቲያን በሆንክበት በዚያ ቀን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶሃል።

3) በየዕለቱ *በመንፈስ ቅዱስ መሞላት* ያስፈልግሃል።

ዮሴፍ፥ አንተ የመጀመሪያው ነጥብ ገብቶሃል። እግዚአብሔር ለአንተ ሁለተኛውን አድርጓል። አሁን ሦስተኛውን በሥራ ማዋል ይጠበቅብሃል። በመጀመሪያው ደብዳቤህ «በቂ ድል ወይም ደስታን አልጨበጥኩም» ብለሃል። ለችግርህ ምላሹ *በመንፈስ ቅዱስ መሞላት* ያሻሃል የሚል ነው።

በእርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም ክርስቲያኖች እንዲህ ይናገራል፥ «መንፈስ ይሙላባችሁ. . .» (ኤፌሶን 5:18)። ይህ ማለት ደግሞ እንደሚከተለው ነው፡—

## በመንፈስ መሞላት ማለት

- በየዕለቱ ለእኔነት ‹እንቢ›፥ ለመንፈስ ቅዱስ ‹እሺ› ማለት
- እግዚአብሔር የተሻለ ሕይወት እንድትኖር ይረዳህ ዘንድ ከመጠየቅ ይልቅ «ጌታ ሆይ፥ ዛሬ በምን መንገድ ላገልግልህ?» ማለት
- ለራስህ ከመኖር ይልቅ ለእርሱ መኖር
- «የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ» የሚል መሻት
- አመለካከትህ ራስህን ያማከለ ከሚሆን ይልቅ በየዕለቱ እግዚአብሔርን ያማከለ እንዲሆን መፍቀድ
- የራስህ ሕይወት ምቾት የተሞላበት እንዲሆን ከመጣር ይልቅ ሕይወትህን ለወንጌል ስርጭት መስጠት

በመንፈስ ለመሞላት ያ በድንገት የሚሆንበትን ዕለት መጠበቅ ይኖርብህ ይሆን?

የለም። በመንፈስ መሞላት አንድ ጊዜ ብቻ የሚከሰት ነገር አይደለም። በየዕለቱ የሚሆን ነው። ደግሞም ምርጫ ነው።

በመንፈስ መሞላት ማለት *እያንዳንዱን ዕለት* በእንዲህ ዓይነት ዝንባሌ መጀመር ነው።

ጌታ ሆይ፥ በዛሬው ቀን ዓላማዬ

መንፈስ ቅዱስን መታዘዝና ከኃጢአት መራቅ ነው።

ሕይወቴ አስቸጋሪ ቢሆን እንኳ

ወይም ደግሞ ብዙ ገንዘብ ቢኖረኝ ወይም ቢያንሰኝ

ጌታ ሆይ፥ በአንተው ድጋፍ ላገለግልህ እወዳለሁ።
ወደ ገሃነመ-እሳት በመጓዝ ላይ ላሉ ሰዎች

እንዴት የዘላለምን ሕይወት መቀበል እንደሚችሉ
እነግራቸዋለሁ።

እንደዚህ መጸለይ በጀመርኩ ጊዜ ገና የ17 ዓመት ወጣት ነበርኩ። መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን የሕይወቴን ክፍል እንዲሞላ በተለይም

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አራት ጉዳዮች በተመለከተ እንዲረዳኝ ጋበዝኩት።

1) **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፡-** «ከአሁን በኋላ ዝም ብዬ አላነበውም! መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት ማጥናት እጀምራለሁ» በማለት ለእግዚአብሔር ቃል ገባሁ።

2) **ልጃገረዶች፡-** በ17 ዓመቴ ከልጃገረዶች ጋር ኃጢአት ላለመፈጸም ቃል ኪዳኔን አደስኩ። በየዕለቱና በየስፍራው ቆንጆ ልጃገረዶችን ስለምመለከት ይህ በጣም አስቸጋሪ ነበር። ነገር ግን ለእነዚያ ፈተናዎች ሁሉ ‹አይሆንም› የሚል ምላሽ እንድሰጥ መንፈስ ቅዱስ ረዳኝ።

3) **ምስክርነት፡-** ለእግዚአብሔር እንዲህ ስል ቃል ገባሁ። «በትምህርት ቤት ላሉ ጓደኞቼ ሁሉ ስለ ደኅንነት እነግራቸዋለሁ።» እስከዚያ ጊዜ ድረስ ስለ ኢየሱስ ለየትኛውም ጓደኛዬ አንሥቼበት አላውቅም ነበር። ገና ስጀምር እንዴት ፈርቼ ነበር! ነገር ግን ለአንዱ የመመስከር ዕድል ባገኘሁ ቁጥር እየቆየሁ እንዴት ደስ ይለኝ ነበር!

4) **ገንዘብ፡-** እንደ ልጅ ቀበቶ እየሠራሁ በመሸጥ ጥቂት ገንዘብ አጠራቅሜ ነበር። በ17 ዓመቴ ገንዘቤን እንዴት መጠቀም እንዳለብኝ መንፈስ ቅዱስን መጠየቅ እንደሚኖርብኝ ተረዳሁ። ከዚያ በኋላ ለቤተ ክርስቲያናችን የወንጌል ስርጭት ለሚውለው ተቀማጭ መስጠት ጀመርኩ። ብዙ ጊዜ በእርግጥ የማያስፈልጉኝን ነገሮች ለመግዛት እፈተን ነበር። ስለዚህ መስጠት ቀላል አልነበረም።

አየህ ዮሴፍ፥ በመንፈስ መሞላት ማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስሜትን የሚቀሰቅስ ስብከት ስትሰማ ወይም ስትዘምር ብቻ የሚከሰት አጭርና አስደናቂ ስሜት አይደለም።

በመንፈስ ለመሞላት በየዕለቱ ከባድ ምርጫዎችን ማድረግ አለብህ። አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን ለመኖር የተሻለው መንገድ ነው!

ልጄ ዮሴፍ፥ እንዲህ አድርግ። በሁሉም የሕይወት አቅጣጫዎች በመንፈስ የተሞላህ መሆንን ምረጥ። በየዕለቱ ያንኑ ምርጫ አድርግ! ከዚያ በኋላ የምትናፍቀውን ድልና ደስታ ትጨብጣለህ።

ውድ ብሩስ፥

ያልከኝን አደረግሁ! እያደርግሁትም ነው! በየዕለቱ መንፈስ ቅዱስን እንዲሞላኝና . . . የሕይወቴን አቅጣጫዎች ሁሉ እንዲቆጣጠር እጠይቀዋለሁ።

አሁንም ግን ትልቅ ችግር አለብኝ! ሴት ጓደኛዬን እንዴት የዘላለምን ሕይወት መቀበል እንደምትችል ነግሬያታለሁ። ጌታን ለመቀበል እንደምትወስን በእርግጥ ተስፋ አድርጌ ነበር። ነገር ግን በመጨረሻ እንቢ አለች። እንዲያውም እኔን «በጭራሽ ደግሜ ላይህ አልፈልግም» አለችኝ።

በጣም አዘንኩ!

በመንፈስ መሞላት ድልና ደስታን ያመጣልሃል ብለኸኝ ነበር። እስካሁን ድረስ ስለጨበጥኩት ድል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ ነገር ግን ደስታዬ ወዴት አለ?

ውድ ዮሴፍ፥

ስለ ሴት ጓደኛህ ምን እንደሚሰማህ ይገባኛል። ስለ እርሷ ተግተን መጸለይ ይኖርብናል።

ስለ ራስህ «ደስታ» አትጨነቅ። ይመጣል። የሴት ጓደኛህን አጥተሃል። ነገር ግን ከዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ስለ ሰጠህ መልካም ሚስት ስታመሰግነው ብሰማ ብዙም አይደንቀኝም።

ሕይወት በአስቸጋሪ ገጠመኞች የተሞላች ናት። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ጌታህ ይሆን ዘንድ በምርጫህ ከገፋህበት እነዚያን ችግሮች ያሠለጥንህ ዘንድ ይጠቀምባቸዋል። ይህን የሚያብራራ ታሪክ ይኸውልህ፤ እንደምትወደውም እርግጠኛ ነኝ።

## በጌታው የሠለጠነ ፈረስ

ከረዥም ዘመናት በፊት መኪኖች እንደአሁኑ መንገዶችን ሳያጥለቀልቁ አንድ ሠረገላና አራት ጎታች ፈረሶች ያሉት ሰው ነበረ። በሠረገላው ውስጥ ያሉት መቀመጫዎች በቆዳ ተለብጠዋል። ከሠረገላው ፊት የሚያምሩት አራት ፈረሶቹ ይቆማሉ። ፈረሶች በሚገባ የሠለጠኑ ናቸው። አሳዳሪያቸው እንዲሄዱ ሲያዝዝ በአንድነት ይነሣሉ። ዛቡን በቀስታ እንኳ ከጎተተ ሁሉም በአንድ ጊዜ ወደዚያው አቅጣጫ ይዞራሉ። «ቁም» ካላቸው ደግሞ በቀስታ አረጋግተው ሠረገላውን ያቆሙታል። እናም በየትኛውም ስፍራ ሠረገላው ሲቆም ፈረሶቹ

ለሚቀጥለው እንቅስቃሴ ዝግጁ ሆነው ይቆያሉ። ሣር አይግጡም፤ እግራቸውን እንኳ አያንቀሳቅሱም።

አንድ ቀን ባለቤቱ ሠረገላውን በመንገድ ላይ አቆመና አጥሩን ለማጠባበቅ ሄደ። ጋሪው በቆመበት በዚያው ስፍራ ሌሎች ሁለት ሰንጋ ፈረሶች ሣር ይግጡ ነበር። እነርሱም አራቱን ፈረሶች እንዲህ አሉአቸው። «ለምን ዝም ብላችሁ ትቆማላችሁ? ሣሩ ምን ያህል ለምለም እንደሆነ አታስተውሉምን? ይልቅ ኑ ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ»።

ነገር ግን አራቱ ፈረሶች ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አልተመለከቱም። የጌታቸውን ድምፅ እየተጠባበቁ በዚያው ባሉበት ቆሙ።

«ኑ ከእኛ ጋር ተጫወቱ፤ በሩጫ እንወዳደር፤ ልትይዙን ሞክሩ!» በማለት ሁለቱ ፈረሶች እንደገና ሊያግባቧቸው ሞከሩ።

ፊታቸውን አዙረውም ሸመጠጡ፤ ነገር ግን ዞር ብለው ቢመለከቱ የተከተላቸው አልነበረም።

ስለሆነም «ጨዋታ የማትወዱት ስለ ምን ነው? መኮሳተራችሁስ ለምንድን ነው?» በማለት በሠረገላ ጎታቾቹ ፈረሶች ላይ ጮኹባቸው።

አሁንም አራቱ ፈረሶች አንዲት ቃል እንኳ ሊመልሱ አልሞከሩም። አሳዳሪያቸው እስኪመለስና እንሂድ እስኪላቸው ድረስ እዚያው ቆሙ።



ከሁለት ቀናት በኋላ ጌታው እነዚያን ሁለት ፈረሶች ያዛቸው። አንገታቸውን በገመድ አስሮም በረዥም አጥር ወደ ተከበበው የማሠልጠኛ ስፍራ ወሰዳቸው።

እነዚያን ለምለም ኮረብታዎች ለቅቀው ሲሄዱ ሁለቱ ፈረሶች በጣም አዘኑ! በማሠልጠኛው ስፍራ ከእግራቸው ሥር የሚያዩት ነገር ቢኖር ቡናማ ቀለም ያለው አቧራ ብቻ ነበር። ከአጥር ወደ አጥር ቢሮጡም ማምለጫ አላገኙም።

በሚቀጥለው ቀን ልምምዱን ለማስጀመር አሠልጣኛቸው መጣ፤ ልጓምን በአፋቸው ካስገባ በኋላ ትእዛዛትን ሰጣቸው። ፈረሶቹም እንዲህ አሰቡ። «ይህ ሥልጠና አስፈሪ ነው? ከለምለሙ መስክ ተገልለን እንዲህ ዓይነት አሳዛኝ ሥራ ውስጥ የተዘፈቅነው ስለ ምንድን ነው!»

በመጨረሻም አንዱ ፈረስ ለሌላኛው እንዲህ አለው። «ይህን አጥር ጠላሁት። ነጻነቴን ፥ ለምለሙን መስክና የወንዙን ንጹሕ ውኃ እፈልጋለሁ። ከዚህ በኋላ ተጨማሪ ሥልጠና አልፈልግም።»

ከዚያ በኋላ አንድ ቀን በሩ ተከፍቶ አገኘው። በደስታ ወደ ለምለሙ መስክ ሸመጠጠ።

ሌላውም ፈረስ እንዲሁ የማምለጥን አጋጣሚ አግኝቶ ነበረ። ነገር ግን ለመቆየትና የጌታውን ፈቃድ ለማድረግ ወሰነ።

አሠልጣኙ አምልጦ የሄደውን ፈረስ እንዲመለስ አላስገደደውም። ይልቁንም ለመሠልጠን የመረጠውን ፈረስ ማለማመዱን ቀጠለ።

ሳምንታት ባለፉ ቁጥር ልምምዱ የበለጠ እየጠነከረ ሄደ። ያም ሆኖ ግን ይህ ፈረስ የጌታውን ፈቃዶች ሁሉ ማድረግን እየተማረ ነበር።

በመጨረሻ ልምምዱ አበቃ። አዲስ የሠለጠነው ፈረስም ቀደም ብለው የጌታቸውን ሠረገላ ይጎትቱ ከነበሩት ፈረሶች ጋር እንዲቀላቀል ተፈቀደለት።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሥልጠናው ጠፍቶ የሄደው ፈረስ በዛፍ ጥላ ሥር በመዝናናት ላይ እያለ በድንገት የዚያ ጌታ ሠረገላ መንገዱን አቋርጦ ሲመጣ ተመለከተ። እናም ሠረገላውን ከሚጎትቱት ውብ ፈረሶች አንዱ የእርሱ ባልንጀራ እንደሆነ አስተዋለ።

«ያ ባልንጀራዬ የከበረው እኔ ግን የተናቅሁት ስለ ምንድን ነው?» ሲል ለራሱ አጉረመረመ። «ጌታው ለምን የእርሱን ሠረገላ የመጎተት አስደሳች ኃላፊነትን አልሰጠኝም? ዳሩ ግን ግድ የለኝም። እኔ ነፃ ነኝ። ያ ዕድለ–ቢስ ባልንጀራዬ ከሠረገላው ጋር በገመድ ተጠፍሯል።

ያም ሆኖ ግን ደስተኛ ይመስላል። ግን ልዩነት አያመጣም፤ እኔ ነፃ ነኝ!»

በሚቀጥለው ዓመት ዝናብ አልነበረም። ለምለም የነበሩት መስኮች ቡናማ ሆኑ። ወንዞችም ደረቁ።

ከማሠልጠኛው ጠፍቶ የሄደው ፈረስ ሣር ፍለጋ ከቦታ ቦታ ተንከራተተ። ግን ምንም አላገኘም።

አንድ ቀን ትንሽ የሚበላ ነገር ፍለጋ የደከሙ እግሮቹን እየጎተተ ይሄድ ነበር. . . ከዚያ በኋላ የአሳዳሪው ሠረገላ በመንገዱ ላይ በፍጥነት ሲሽከረከር አየ። የእርሱ ባልንጀራ ከአራቱ ፈረሶች አንዱ ነበር። እናም አሁን ድረስ ጤናማ ነው!

«ባልንጀራዬ ሆይ» አለ በጩኸት ጠፍቶ የሄደውና የደከመው ፈረስ «በእነዚህ የድርቅ ቀናት እንዴት ጤናማና ጠንካራ መሆን ቻልክ? የትም ስፍራ የመሄድ መብት ቢኖረኝም ዛሬ ብፈልግም እኔ ምንም የሚበላ አላገኘሁም። ምግብ ከየት ታገኛለህ? በጣም አምሮብሃል፤ ነገር ግን በዚያ በረኸም አጥር የተከበበ ቀፋፊ የማሠልጠኛ ስፍራ እንደቆየህ አውቃለሁ። እናም ለጌታህ የመታዘዝ ግዴታ ነበረብህ»።

ተጠያቂው ፈረስም እንዲህ ሲል መለሰለት። «ጌታዬን ለመታዘዝ ያስገደደኝ የለም፤ ግን ለእርሱ መታዘዝ ያስደስተኛል። ሥልጠናው ከባድ ነበር፤ ግን ጌታዬ ይወደኛል። በእጁም ይመግበኛል»።



ዮሴፍ፥ ልጄ፥ መንፈስ ቅዱስ መልካም ጌታ ነው።

ከእርሱ ሥልጠና ፈጽሞ አትሽሽ።

በየዕለቱ ለእርሱ ለመታዘዝ ውሳኔህን አድስ!

ያ ቀላል አይሆንም።

ለተለያዩ ኃጢአቶች «አይሆንም» ማለት በተለይም

ወጣቶችን ሁሉ የሚፈትነውን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት
መሸሽ አስቸጋሪ እንደሆነ ሁልጊዜም ትረዳለህ።
ነገር ግን ጌታህን መታዘዝ ስትቀጥል፥
ሕይወትህ በሙሉ እየተለወጠ ይሄዳል፥
እናም አንድ ቀን የጋብቻህ ጉዳይ ይሻሻላል፥
ስለሆነም እንዲህ ትላለህ፥
«ጌታዬን መታዘዝ ‹ግዴታ› አይደለም፤
እርሱን መታዘዝ ደስ ያሰኘኛል።»

ውድ ብሩስ፥

ጌታዬ ከሚሰጠው ሥልጠና በጭራሽ ሸሽቼ አልሄድም! ለትልልቆችና ለልጆች ሁሉ የፈረሱን ታሪክ እየነገርኩ ነው። ሁሉም እየተረዱት ነው። «በተለይም ሥልጠናው ከባድ ነበር፤ ግን ጌታዬ በእጁ ይመግበኛል» የምትለዋን ክፍል በጣም ይወዱታል።

ዛሬ አእምሮዬ በጥልቅ እንደተረበሸ ልነግርህ ይገባኛል። በአውቶቡስ ላይ ያገኘሁት አንድ ሰው ከአንድ ሰዓት ለማያንስ ጊዜ በመንፈስ መጠመቅ እንዳለብኝ አስረዳኝ።

ብሩስ፥ በመንፈስ ቅዱስ አልተጠመቅሁም ነበር እንዴ?

‹በመንፈስ መጠመቅ› የሚባለው ‹በመንፈስ መሞላት› ከተባለው ጋር አንድ ነውን?

ውድ ጆ

አዎን አንተ በመንፈስ ተጠምቀሃል።

የለም፥ «መጠመቅ» የሚለው ከ«መሞላት» ጋር አንድ አይደለም። በመንፈስ «መጠመቅ» ማለት መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ሊኖር መምጣቱን ያመለክታል።

ዮሴፍ፥ አንተ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቅኸው ከብዙ ሳምንታት በፊት ጌታን በተቀበልህበት ወቅት ነበር። በዚያ ቀን መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ መኖር ጀመረ።

ስለዚህ በአውቶቡስ ላይ ያገኘህ ሰው እንዲያስፈራራህ አትፍቀድለት።

አንተ በእርግጠኝነት በመንፈስ ተጠምቀሃል።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 ጳውሎስ ሁሉም ክርስቲያኖች በመንፈስ የተጠመቁ መሆናቸውን ገልጾአል። ከተለያየ ዘር ብንሆንም እንኳ ያ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ ተናግሯል። . . . አንድ አካል ነን። ለምን? ምክንያቱም በአንድ መንፈስ ተጠምቀናል።

«አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን. . . እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና» (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)።

«እኛ ሁላችን» የሚሉትን ቃላት ልብ በል። ጳውሎስ «አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈስ ተጠምቀዋል፤ አንዳንዶቹ ግን አልተጠመቁም» አላለም። ያለው እንዲህ ነው፦ «እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናል»።

ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ነገሮችን ሲናገሩ መስማት ያሳዝናል። «በእኛ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ በሙላት ይሠራል፤ ነገር ግን አንዳንድ አብያተ ክርስቲያን በመንፈስ ያልተጠመቁ ብዙ አማኞች አሉአቸው»።

ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ስንመለከት «በመንፈስ መጠመቅ» የሚሉት ቃላት በሰባት ቦታዎች ተጠቅሰዋል። ጥቅሶቹ ማቴዎስ 3፡11፤ ማርቆስ 1፡8፤ ሉቃስ 3፡16፤ ዮሐንስ 1፡33፤ የሐዋ. 1፡5፦ 11፡15–16፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡13 ናቸው። እነዚህ ጥቅሶች እያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን በመንፈስ እንደተጠመቀ በግልጽ ያመለክቱናል።

ውድ ብሩስ፦

አሁን ግራ ተጋብቻለሁ። በመንፈስ «በመሞላት» ና በ «መጠመቅ» መካከል ያለው ልዩነት ገብቶኛል እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም።

ጌታን በተቀበልኩበት ቀን በመንፈስ ተጠምቄያለሁ፤ ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ በእኔ ውስጥ ለመኖር መጥቷል።

አሁን በክርስትና ሕይወት ጉዞዬን ቀጥያለሁ። በየዕለቱ «በመንፈስ መሞላት»ን መምረጥም አለብኝ። ይህ ማለት ደግሞ ሁሉንም የሕይወት አቅጣጫዎች ለእርሱ መስጠት ማለት ነው።

ስለሆነም እኔ በመንፈስ የተጠመቅሁ ነኝ፤ ምክንያቱም እርሱ በውስጤ አለ። ሕይወቴን ለእርሱ መስጠት እስከቀጠልኩ ድረስ በመንፈስ የተጠመቅሁ ነኝ።

እንዲያ ነው?

ውድ ዮሴፍ፥

በትክክል እንዲያ ነው! እግዚአብሔር የእርሱን ድርሻ ፈጽሟል። መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶሃል።

አሁን አንተ የራስህን ድርሻ መወጣት አለብህ። ራስህን በመስጠት መቀጠል አለብህ። (እናም በእርሱ የተሞላህ ትሆናለህ።)

| እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሳን በሙላት ሰጥቶኛል። እኔስ ራሴን ሙሉ በሙሉ እየሰጠሁት ነውን? | እግዚአብሔር በመንፈስ አጥምቆኛል። እኔስ በመንፈስ ለመሞላት እተጋለሁን? |
|---|---|

ዮሴፍ፥ አሁን ለአንተ አዲስ ጥያቄ አቀርባለሁ። ይህን ለመመለስ ጥረት አድርግ። በርካታ ክርስቲያኖች ደካማ የሆኑት ለምንድን ነው?

ውድ ብሩስ፥

ጥሩ ጥያቄ ነው! ጌታን ከተቀበልኩበት ዕለት ጀምሮ ብዙ ክርስቲያኖች ደክመው ሳገኛቸው በጣም እደነግጥ ነበር። የእሑድ አምልኮ ይካፈላሉ፤ ነገር ግን ለጓደኞቻቸው አይመሰክሩም፥ ለእግዚአብሔር ሥራ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን እንደሚገባ አይሰጡም። መጽሐፍ ቅዱሳቸውን አያጠኑም፥ በጸሎት ፕሮግራሞች የሚካፈሉት በጣም አልፎ አልፎ ነው። እናም በቤታቸው ደስታ የለም። ምክንያቱም እንደ ባልና ሚስት ፍቅርና መከባበር በመካከላቸው የለም።

የማስበው እንደሚከተለው ነው:-

## ደካማ ክርስቲያኖች

በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ:- ደካማ ክርስቲያኖች እንኳ በውስጣቸው መንፈስ ቅዱስ ይኖራል።

በመንፈስ ቅዱስ አለመሞላት:- ደካማ ክርስቲያኖች ሁልጊዜም ለመንፈስ «አይሆንም» የሚሉ ሲሆኑ ለእኔነት ግን ምላሻቸው «እሺ» ነው። በመንፈስ ከመሞላት ይልቅ በአብዛኛው በእኔነት የተሞሉ ናቸው።

ውድ ዮሴፍ፥

መልስህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማል።

ጳውሎስ ለደካማ ክርስቲያኖች እንዲህ ብሏል።

«እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥. . . ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም. . . . ወተት ጋትኋችሁ. . .» (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡1–2)።

«ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን?» (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡19)።

«መንፈስ ይሙላባችሁ. . . ሚስቶች ሆይ. . . ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ባሎች ሆይ. . . ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፤ . . . አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው» (ኤፌሶን 5፡18–25፥ 6፡1–4)።

ጳውሎስ ለደካማ ክርስቲያኖች ሲጽፍ «እናንተ ክርስቲያኖች ሆይ፥ ደካሞች ናችሁ፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ የለም» እንዳላለ ልብ በል።

በዚያ ፈንታ ግን እንዲህ ተናገረ። «ሕፃናት ናችሁ፥ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ እንዳለ አታውቁምን? መንፈስ ይሙላባችሁ»።

በመንፈስ መሞላትን በሚመርጡ ጊዜ (በእኔነት ከመሞላት ይልቅ) በሚከተሉት መንገዶች እንደሚለወጡ ነግሯቸዋል፡–

ሚስቶች ባሎችን በሚያከብሩበት አኳኋን

ባሎች ሚስቶቻቸውን በሚያከብሩበት መንገድ

ልጆች ለወላጆቻቸው በሚታዘዙበት አካሄድ

አባቶች ልጆቻቸውን በምክር በሚያሳድጉበት ዘዴ።

ደካማ ክርስቲያኖች የደስታ ቁልፍ ምን እንደሆነ ሊረዱ ይገባል። ይኸውም *በእኔነት ከመሞላት ይልቅ በመንፈስ መሞላት ነው።*

ውድ ብሩስ፥

ዛሬ በጣም ተጨንቄያለሁ። በልሳን መናገር እፈልጋለሁ፤ ግን አልሆነልኝም። ሰዎች ሊረዱኝ ቢሞክሩም እንኳ ምንም ጠብ ያለ ነገር የለም። ለምን? በእኔ በኩል ችግር ይኖር ይሆን?

ይህ ሁሉ የሆነው አንድ አሜሪካዊና ባለቤቱ እኔ የምሠራበትን ቤተ ሙከራ ለመጎብኘት በመምጣታቸው ነው። ቤተ ሙከራውን

እያዞርኩ ሳስጎበኛቸው ሳለ እንዲህ ሲሉ ነገሩኝ። «አሥር ሚሊዮን አሜሪካውያን ከአልኮል ጋር በተያያዙ በሽታዎች ይሠቃያሉ»።

እኔም «ጌታን እስከተቀበልኩበት ቀን ድረስ አልኮል የእኔንም ሕይወት እያበላሸ ነበር» አልኩኝ። ስለ ክርስቶስ የበለጠ መናገር ፈራሁኝ። ለነጮች መመስከር ለእኔ ይከብድብኛል። ለምን እንደ ሆነ ግን አላውቅም።

ወዲያውኑ ሁለቱም «ክርስቲያን ነህ! እግዚአብሔር ይመስገን! እኛም እንዲሁ ነን!» በማለት አደነቁ።

አቅፈውኝም እንዲህ አሉኝ «ተመልከት፥ የምሳ ሰዓት ደርሶአል፤ ከእኛ ጋር ለምሳ ወደ አረፍንበት ሆቴል እንሂድ»።

እየተመገብን ሳላም «መንፈስ ቅዱስን ተቀብለሃል? » ሲሉ ጠየቁኝ።

«አዎን» ብዬ መለስኩ።

«እስኪ ንገረን» አሉኝ በመደነቅ።

እኔም እንዲህ ተናገርኩ፥ «ጌታን በተቀበልኩ ዕለት ደኅንነትንና መንፈስ ቅዱስን ተቀብያለሁ»። ከዚያም የማስታውሰውን ጥቅስ ጠቀስኩላቸው።

> «እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ» (ኤፌሶን 1፡13)።

«በልሳኖች ተናግረህ ታውቃለህ?» ብለው ጠየቁኝ።

«በጭራሽ» ነበር ምላሼ።

ፊታቸው ኮስተር አለ፤ እንዲህም አሉኝ «መንፈስ ቅዱስን የሚቀበል ሰው ሁሉ በልሳን መናገር አለበት። በራሳችን ሕይወት ይህንን አይተናል፤ በመቶ በሚቆጠሩ ሌሎች ሰዎችም እንዲሁ »።

ከዚያም ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው በልሳኖች የተናገሩባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሳዩኝ (የሐዋርያት ሥራ 2፡4፤ 10፡44-46 እና 19፡6)።

«እባካህን ዮሴፍ» አሉኝ በመቀጠል «እጆቻችንን እንጫንብህ፤ ስንጸልይልህ- መንፈስ ቅዱስን ትቀበላለህ፤ በልሳኖችም ትናገራለህ፤ ልሳኖች ማስረጃዎች ናቸው»።

እጃቸውን ከጫኑ በኋላ እንዲህ አሉኝ። «መናገር ጀምር፥ ግን በእንግሊዝኛ አይደለም፤ ልሳንህን አፍታታ፤ ማንኛውንም ድምፅ አውጣ»።

ብዙ ድምፆችን አወጣሁ፤ ግን ምንም ዓይነት ልሳን አልመጣም። አሁን ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ተጭኖኛል።

ውድ ዮሴፍ፥

አትጨነቅ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ለአንተ የሚሆን ማበረታቻ አለው።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው በልሳኖች ስለተናገሩ ሰዎች ሦስት ጊዜ መጻፉ እውነት ነው (የሐዋርያት ሥራ 2:4፤ 10:44–46 እና 19:6)። በዚያው መጽሐፍ ላይ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነገር ግን በልሳኖች መናገራቸው ያልተወሳበትም ክፍል መኖሩ እውነት ነው (የሐዋርያት ሥራ 4:31፤ 8:17፤ 9:17–18፤ 13:52)።

ስለሆነም «መንፈስ ቅዱስን የሚቀበል ሰው ሁሉ በልሳኖች ይጸልያል» ወይም ደግሞ «ልሳኖች ማስረጃዎች ናቸው» ማለት አይገባንም።

ሮሜ 12:4–8 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 12:4 እስከ 13:1 ያለውን ስናነብ በልሳን መናገር ለጥቂት ክርስቲያኖች የተሰጠ ስጦታ እንደሆነ ትረዳለህ። ሌሎቹ ክርስቲያኖች ሌሎች ስጦታዎችን ይቀበላሉ።

ዮሴፍ፥ አንተም ስጦታዎችን ተቀብለሃል። ምናልባትም «አስተማሪ» ልትሆን ትችላለህ (1ኛ ቆሮንቶስ 12:28)፥ ወይም የ«መስጠት» ስጦታ ይኖርሃል (ሮሜ 12:8)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገልህን በቀጠልክ መጠን ምን ስጦታዎች እንዳሉህ መለየት ትጀምራለህ።

ደግሞም በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ ወንድሞችና እኅቶች አንተ የሌለህ ዓይነት ስጦታ እንዳላቸው ታስተውላለህ። አንተ ከእነርሱ ጋር መሥራት ይገባሃል፤ እነርሱም ከአንተ ጋር መሥራት ይኖርባቸዋል። እናንተ በአንድነት አካል ናችሁ።



አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን. . .
(1ኛ ቆሮ. 12:17)

ሁሉም ሰው በልሳኖች የመናገር ስጦታ ቢኖረውና የምሕረት፥ የአገዛዝ፥ ወይም የአገልግሎት ስጦታ ያለው ሰው ባይገኝ ያቺ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት መልክ ይኖራታል? (ሮሜ 12:6–8)።

በሰው አካል ውስጥ ዓይን እጅን

«አታስፈልገኝም» ልትለው አትችልም (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡21)።

በተመሳሳይ መንገድ እኛ ክርስቲያኖች «ሁሉም ሰው የእኔን ስጦታ ማግኘት አለበት፤ ምክንያቱም ጥልቅ መንፈሳዊ ልምምድን ያስገኛል» ከሚል አመለካከት ርቀን በአንድነት መሥራት አለብን።

ዮሴፍ፥ አሜሪካውያን ወዳጆችህ ሁሉም ክርስቲያን በልሳኖች የመናገር ስጦታ ሊኖረው ይገባል ብለው በማሰባቸው አዝናለሁ። ያንን አትመን። መጽሐፍ ቅዱስህን ማንበብ ቀጥል፤ ለእግዚአብሔርም ሦስት ነገሮችን ቃል ግባ፡-

1) የሰጠኸኝን ስጦታዎች ሁሉ እጠቀማለሁ፤ እናም የተለያየ ስጦታ ካላቸው አማኞች ጋር ሆኜ አገለግልሃለሁ። እንደ አካል ተባብረን እንሠራለን።

2) እኔ የሌለኝን ስጦታ በሌሎች ዘንድ ባየው በዚህ ቅናት አይይዘኝም (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡15)።

3) የእኔ ዓይነት ስጦታ የሌላቸውን ሰዎች ዝቅ አድርጌ አልመለከትም (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡21-25)።

ውድ ብሩስ፥

ደብዳቤህ አበረታቶኛል። ግን በጥቂቱ ነው። አሁንም ታች እንደወረድኩ ነው። ብዙ ጊዜ አሜሪካውያኑ ወዳጆቼ የነገሩኝን እያስታወስኩ እንዲህ በማለት እደነቃለሁ። «እውነት በእኔ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አለ?»

እስካሁን ምንም የተለየ ነገር አላጋጠመኝም።

በቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ወገኖች አስደናቂ ልምምዶችን አሳልፈዋል። አንዲት ልጃገረድ «ባለፈው ሳምንት ከእሑድ ፕሮግራም በኋላ እግዚአብሔርን ማምለኬን ለመቀጠል ወደ ኋላ ቀረሁ፤ በድንገትም በቃላት ሊገለጽ በማይችል ደስታ ተሞላሁ። ከዚያም በራእይ ኢየሱስን ከአጠገቤ ተቀምጦ አየሁት» በማለት መስክራለች።

ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ዓይነታቸው የበዛ ልዩ ልምምዶችን አሳልፈዋል።

ነገር ግን አንዳንዶቻችን ምንም አላየንም።

አሁን እኛ ወጣቶች ተከፋፍለናል፤ አንዳንዶች በልምምዶቻቸው ሲኩራሩ. . . ሌሎቻችን ደግሞ ምንም ባለማየታችን የበታችነት እየተሰማን ነው።

ውድ ዮሴፍ:

እባካችሁ «ልዩ ልምምዶች» እንዲከፋፍሉዋችሁ አትፍቀዱ። ልዩ ልምምድ ውስጥ ለገቡና እዚያ ደረጃም ላልደረሱ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል እንመልከት።

## ሀ) ልዩ ልምምድ ውስጥ ለገቡ ክርስቲያኖች

ሐዋርያው ጳውሎስ «ወደ ሦስተኛው ሰማይ መነጠቁን» እንደ ልምምድ ያነሣው አንድ ጊዜ ብቻ ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 12:2)። ያም ሆኖ ግን እንዲህ አልተናገረም። «ሁሉም ክርስቲያኖች የዚህ ዓይነት ልምምድ ያሻቸዋል፤ ምክንያቱም የኃይል ቁልፍ ነውና።» በዚያ ፈንታ ጢሞቴዎስ ለተባለው ወጣት ለብርቱ የክርስቲያን ሕይወት ሦስት ደረጃዎች እነዚህ ናቸው ይለዋል።

> ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ይለዋል:-
>
> 1) በጌታችን ምስክርነት አትፈር፤ ስለ ወንጌል አብረኸኝ መከራን ተቀበል (2ኛ ጢሞቴዎስ 1:8)።
>
> 2) ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ራስህን ስጥ (2ኛ ጢሞቴዎስ 2:15 እና 3:16)።
>
> 3) ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ሽሽ፤ ጽድቅን ተከተል (2ኛ ጢሞቴዎስ 2:22)።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ «ልዩ ልምምድ ያስፈልግሃል» እስካላለው ድረስ እኛም «እያንዳንዱ ሰው እኔ የደረስኩበት ልምምድ ያሻዋል» ማለት የለብንም። ይልቁንም ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የነገረውን በተመሳሳይ መልኩ ለሰዎች ማስተላለፍ አለብን። እነርሱም ምስክርነት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ ከኃጢአት መሸሽና ጽድቅን መከተል ናቸው።

## ለ) ልዩ ልምምድ ውስጥ ላልገቡ ክርስቲያኖች

የተለየ ልምምድ ባይኖርህም አትጨነቅ፤ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ስለመኖሩ እግዚአብሔርን አመስግን። በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ምረጥ።

የዮሐንስ ወንጌል፥ ቆላስይስ ምዕራፍ ሦስት፥ ኤፌሶን፥ 1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ ዘፍጥረትና ሌሎችንም አጥና። ለክርስቶስ በድፍረት ኑር!

## *ልዩ ልምምዶች ሁሉ ከእግዚአብሔር ናቸውን?*

በቅርቡ መጋቢያችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እያነበበ ሳለ አንዲት ወይዘሮ መሳቅ ጀመረች። በኋላም «የምስቀው በመንፈስ ነበር» ስትል ተናገረች።

የሴትየዋ ልምምድ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ነበርን? በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዲህ ያለ ልምምድ እናገኛለን?

በሌላ ጊዜ በፕሮግራሙ መካከል አንድ ሰው በመሬት ላይ ወደቀ። መንፈስ ቅዱስ ነከቶኝ ነው ሲልም ተናገረ። ነገር ግን ሰኞ ዕለት የኃጢአት ሕይወቱን ቀጠለ።

እነዚህ ዓይነት ልምምዶች ከመንፈስ ቅዱስ ናቸው ብለን ማመን ይገባናልን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

> «ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን
> መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ»
>
> (1ኛ ዮሐንስ 4፡1)።

አንድ ልምምድ ከእግዚአብሔር ነው ማለት የሚቻለው፡-

ሀ) መጽሐፍ ቅዱስ ከዚያ ልምምድ ጋር የሚስማማ ከሆነ (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16)።

ለ) ልምምዱ ያገን ሰው በቅድስናና እግዚአብሔርን በመምሰል እንዲኖር ከረዳው ብቻ ነው (ማቴዎስ 7፡22–23)።

**የመንፈስ ፍሬ፡-** ወደ ተለየ ልምምድ ውስጥ መግባትና አለመግባታችን ልዩነት አያመጣም። እኛ ሁላችን የግድ ልንፈጽመው የሚገባን ነገር ግን «በመንፈስ ፍሬ» ማደግ ነው።

**የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥**
**ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ . . .**
**ራስን መግዛት ነው (ገላትያ 5፡22)።**

ውድ ብሩስ፡-

ባለፈው ወር የዓመት ዕረፍቴን ወሰድኩና ከሌሎች ስድስት ወጣቶች ጋር ለቤተ ክርስቲያን ተከላ 400 ኪሎ ሜትሮች ወደሚርቅ

አንድ ቦታ ሄድኩኝ። ወደ ቤት በመመለስ ላይ ሳለሁ ነበር በወባ መለከፌን ያወቅሁት። ከዚያ የተነሣ ሦስት ቀን ሆስፒታል ተኛሁ።

ከዚያ በኋላ ዛሬ ደብዳቤህን ተቀበልኩ። የመንፈስ ፍሬን በተመለከተ ያነሣኸው በእርግጥም ልቤን ነክቶኛል። እውነቱን ለመናገር ብዙዎቹ እነዚህ ፍሬዎች በሕይወቴ አይታዩም። በቤተክርስቲያን ተከላ ጉዞአችን እንኳ ከወጣቶች ጋር እርስ በርስ እንጋጭ ነበር። ለዚህ መንስዔው እኔ መሆኔን ምክንያቱም ትዕግሥትና ቸርነት ስለሌለኝ እንደሆነ አውቄያለሁ። ስለዚህ ነገር ሳስብ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ እውነተኛ ክርስቲያን መሆኔንም እጠራጠራለሁ።

ውድ ዮሴፍ፥

አትጨነቅ፤ አንተ ክርስቲያን ነህ። ይህን ያወቅሁት ለዘላለም ሕይወት ያለህ ተስፋ የኢየሱስ መሥዋዕትነት እንደሆነ ስለምታምን ነው።

ታዲያ ኃጢአትን መተው ለምን አዳገተህ? ምላሹ ይህ ነው። አሁን አንተ ክርስቲያን ነህ፤ መንፈስ ቅዱስም በውስጥህ አለ። ነገር ግን ኃጢአተኛው ተፈጥሮህ አሁንም ኃጢአትን እንድታደርግ ይለማመጥሃል።

ክርስቲያን ከመሆንህ *በፊት* መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ አልነበረም። ስለሆነም ኃጢአተኛው ተፈጥሮ በሕይወትህ ይገዛ ነበር። በእነዚያ ቀናት ድል ማድረግ አትችልም ነበር። ኃጢአተኛው ተፈጥሮህ ሁልጊዜም ይቆጣጠርህ ነበርና (ሮሜ 6፡6)።




አሁን ክርስቲያን ነህና ሕይወትህ ፈጽሞ የተለየ ነው። ጌታን በተቀበልክ ዕለት መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶሃል። እናም ስንሰለትህን በጥሶ ከኃጢአተኛው ተፈጥሮ ነፃ አውጥቶሃል። አሁን ኃጢአተኛ ተፈጥሮህ ኃጢአትን እንድታደርግ *ሊያስገድድህ* አይችልም። *ሊጋብዝህና ሊፈትንህ* ይችላል፤ *ሊያስገድድህ* ግን አይችልም።




ስለሆነም በአንተ ውስጥ አሁን ጦርነት ይካሄዳል። ይኸውም በአንተ ኃጢአተኛ ተፈጥሮና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ነው። በየዕለቱ ያ ውጊያ ይሰማሃል።

ኃጢአተኛው ተፈጥሮህ ወደ ኋላ እንድትሄድና ድሮ ደስ ትሰኝባቸው ወደ ነበሩት ኃጢአቶች እንድትመለስ ይጋብዝሃል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን እንድትታዘዝ ያበረታታሃል።

> 17«ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥
>
> እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ. . .
>
> 19የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥
>
> 20ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል. . .
>
> 21ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።
>
> 22የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት. . .ራስን መግዛት ነው»
>
> (ገላትያ 5:17–22)።

አዎን ክርስቲያናዊ ሕይወት አስቸጋሪ ጦርነት ነው። እናም ይኸው ውጊያ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ በየዕለቱና እስከ ሞት ድረስ ይቀጥላል።

በመንግሥተ ሰማይ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ አይኖረንም። ነገር ግን በምድር ሳለን እኛ ክርስቲያኖች ከዚያ ተፈጥሮ ፈተናዎች ጋር እንዋጋለን።

ስለሆነም ዮሴፍ፥ ቸርና ታጋሽ መሆን ሲሳንህ አትደነቅ። ክርስቲያን መሆንህም አትጠራጠር።

በውስጥህ ኃጢአተኛው ተፈጥሮና መንፈስ ቅዱስ መኖራቸውን ተገንዘብ። እናም ኃጢአተኛው ተፈጥሮህ ኃጢአትን እንድትሠራ ሲለምንህ እንኳ መንፈስ ቅዱስን ለመታዘዝ ምረጥ።

ኃጢአተኛው ተፈጥሮህ ዕርቃናቸውን የሆኑ ልጃገረዶች ምስል እንድትመለከት ሲጠይቅህ ያንን ለመፈጸም እንቢ ማለት ትችላለህ። ኃጢአተኛው ተፈጥሮህ አሁን የአንተ ጌታ ስላልሆነ እንቢ ለማለት በቂ ኃይል አለህ። እግዚአብሔር ሰንሰለቱን በጥሷል። ነፃ ነህ! «እንቢ» ለማለት የሚያስችል ኃይል አለህ።

# የክርስቲያን ሕይወት

የተወለድከው ኃጢአተኛ ተፈጥሮን ይዘህ ነው። ያ ተፈጥሮ ጌታን እስከተቀበልክበት ቀን ድረስ ሲቆጣጠርህ ኖሮአል። ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶሃል፤ ነጻም አውጥቶሃል። አሁን ያ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ሊለምንህ ይችላል፤ ሊያስገድድህ ግን አይችልም።




በየዕለቱ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔርን በመታዘዝና በትሕትና እንድታድግ ያበረታታሃል። . . . ኃጢአተኛው ተፈጥሮ ግን «ኃጢአት መዝናኛ ቀልድ ነው» እያለ ይነግርሃል። ነጻ እስከ ሆንህ ድረስ ማንን እንደምትታዘዝ መምረጥ ይኖርብሃል። ስለሆነም በጥንቃቄምረጥ! ኃጢአት ሕይወትህን ያበላሻል።






እግዚአብሔር የአኗኗር ዘይቤህንና ቤትህን ሊለውጥ ይፈልጋል። ራስህን ውድቀት ውስጥ ካገኘኸው ተናዘዝ፤ ተመለስ። የክርስትና ሕይወትህን አትተው። እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በየዕለቱ በውጊያ ሕይወት ቀጥል። . . . እግዚአብሔርም እንዲህ ይልሃል፦ «በክርስቶስ ደም ታምነሃልና ኃጢአት የለብህም፤ ወደ መንግሥተ ሰማይ ግባ» (ራእይ 7፡9–17)።

በኃጢአት
ከዚያም
ፈጽሞ





ውድ ብሩስ፥

ከአሁን በኋላ ክርስቲያን ስለመሆኔ አልጠራጠርም። ስለ ውጊያዎቼም ቢሆን አልደነቅም። ኃጢአተኛው ተፈጥሮዬ ኃጢአትን እንዳደርግ ያስገድደኛል ብዬም ከአሁን በኋላ አልፈራም።

አሁን ከዚህ በፊት ሆኖ በማያውቅ ሁኔታ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለመራመድ ቆርጫለሁ፤ ኃጢአተኛውን ተፈጥሮዬን አላዳምጥም።

ብሩስ፡- ይህንን ስማ፤ ዛሬ ከትንሹ ወንድሜ (ዕድሜው 14 ነው) ደብዳቤ ደረሰኝ። ጌታን እንደ ግል አዳኙ ለመቀበል ወስኖአል። በጣም ተደስቻለሁ!

ጊዜዬን ቢራ በመጠጣትና ዕፆችን በመጠቀም በማባክንበት በዚያ ጊዜ ለእርሱ ምንኛ ክፉ ምሳሌ ነበርኩ!

ከደቂቃዎች በፊት ለደብዳቤው መልስን ጽፌያለሁ። ካሰፈርኩት ከፊሉ ይህንን ይመስላል።

*ውድ ወንድሜ ፊልጶስ፥*

*ጌታን ለመቀበል ስትወስን ያደረግኸው ምርጫ ብልህነት የታከለበት ነው። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአትህን ይቅር ብሏል፤ ነፃም አውጥቶሃል፤ በመንፈስ ቅዱስ አጥምቆሃል።*

*መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል መጠበቅ የለብህም። በአሁኑ ሰዓት እርሱ በአንተ ውስጥ እየኖረ ነው።*

*ማድረግ ያለብህ ነገር ቢኖር በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ነው። ያ ማለት ደግሞ እርሱን በእያንዳንዱ የሕይወትህ ዝርዝር ጉዳዮች የበላይ ማድረግ ነው። ኃጢአተኛ ተፈጥሮህን ለማድመጥ እንቢ በል። ድንገት ራስህን በኃጢአት ውስጥ ብታገኘው ተናዘዝ. . . ንስሐ ግባ!*

*ፍቅር፥ ትዕግሥት፥ ቸርነትና ሌሎችም ፍሬዎች በሕይወትህ ያፈራሉ። በቤትህና በትምህርት ቤትህ የሚያገኙህ ሰዎች ለውጦቹን ያስተውሏቸዋል። ያኔ በክርስቶስ በኩል እንዴት የዘላለምን ሕይወት እንደተቀበልክ. . . ትነግራቸዋለህ።*

ልክ አንተ ለእኔ እንደምታደርገው በተከታታይ እጽፍለት ጀመር! ብሩስ፥ ዓርብ ዕለት የአንተ ወዳጅ ኤልያስ ማስዋንጋኒ ወደሚሰብከበት የስታዲየም ፕሮግራም ሄድኩ። እርሱም እንዲህ ጠየቀን «የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን (ለምሳሌ—በልሳኖች መናገር) የሚያሳይ ግን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች (ለምሳሌ ቸርነት) የሌለው ሰው ብታዩ ስለ እርሱ ምን ታስባላችሁ?»

ከዚያም እንዲህ በማለት የራሱን ጥያቄ መለሰ። «በወጣትነቴ ዘመን በልሳኖች የመናገርና የመሳሰሉት ስጦታዎች ያሏቸው ክርስቲያኖች እጅግ ብርቱ ይመስሉኝ ነበር። አሁን ግን *ፍሬ ሳያሳዩ ዝም ብሎ በልሳኖች ከመናገር ይልቅ የመንፈስ ፍሬዎች እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ተረድቻለሁ።»*

> «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት. . . ራስን መግዛት ነው» (ገላትያ 5፡22)።

በዚያው ስታዲየም በአንተና በማስዋንጋኒ የተጻፈውንና "Arise Boldly With Power" ወይም «ኃይልን ለብሰህ በድፍረት ተነሣ» የተሰኘውን መጽሐፍ ገዛሁ። እስከ ዛሬ ካነበብኳቸው ሁሉ የላቀ ነው።

ውድ ብሩስ፥

ልክ ትናንትና ለአንተ የጻፍኩልህን ደብዳቤ ፖስታ ቤት አስገባሁ። ግን ዛሬ አሳዛኝና አስደናቂ የሆነ ነገር ገጠመኝ።

ባለፈው ወር በወባ ተለክፌ ሆስፒታል በገባሁ ወቅት ሎይስ የምትባል ልጃገረድ ተዋወቄ ነበር። ነርስ ነች። . . . ሲበዛ ቆንጆ ናት። በየዕለቱ የደም ግፊቴን የምትለካ ሲሆን ረዘም ያለ ጊዜ ወስዳም ታጫውተኛለች። የት እንደምሠራ፥ የት እንደምኖር፥ ምን ዓይነት መጽሐፍ እንደምወድ፥ ወዘተ. . . ለማወቅ ትፈልጋለች።

እኔም ያንን አጋጣሚ እንዴት በክርስቶስ በማመን የዘላለምን ሕይወት እንዳገኘሁ እነግራት ዘንድ ተጠቀምኩበት። ይህ በእውነቱ ደስ አላሰኛትም።

ከሆስፒታል ከወጣሁ በኋላ ደግሜ እንደማላያት አሰብኩ። ነገር ግን ዛሬ በሬ ሲንኳኳ ሰማሁ፤ ሎይስ ነበረች። በጥሩ አለባበስና በደመቀ ፈገግታ።

ሰላምታ ተለዋወጥን። ነገር ግን ብቻዬን ስለነበርኩ ወደ ቤት እንድትገባ አልጋበዝኳትም።

የሞቀው ፈገግታዋ ሳይደበዝዝ «ደስ የሚል ቤት ነው» አለች። ወደ ውስጥም ዘለቀች። ቀጥላም እንዲህ አለችኝ። «ዋናውን በር ቆልፈው፤ ጊዜው አስተማማኝ አይደለም»።

በእንግዳው መቀበያው ክፍል ተቀምጠን ለጥቂት ደቂቃዎች አወጋን። ከዚያም የፍራፍሬ ጭማቂ ለማምጣት ወደ ማብሰያው ክፍል ሄድኩ። ስመለስ በዚያ አልነበረችም።

«ሎይስ. . .?» በማለት ተጣራሁ።

«እዚህ ነኝ፥ የእኔ ሸጋ» ድምፅዋ የመጣው ከመኝታ ቤቴ ነበር። በሩን ስከፍተው ቀይ የውስጥ ሱሪ ብቻ ለብሳ አልጋዬ ላይ ጋደም ብላለች። ልክ እንዳየችኝ ዘልላ ከአልጋ ላይ ወረደች። አቅፋ ትስመኝም ጀመር።

ወዲያውኑ እጆቼ የእርስዋን የውስጥ ሱሪ ማውለቅ ጀመሩ።

ከዚያም ይህን ነገር ለማቆም ራሴን አስገደድኩት።

እያመንታሁ ሳለ እርሷ ፈጠን ብላ ከቦርሳዋ ውስጥ ኮንዶም ይዛ መጣች። አስገራሚ ፈገግታዋን እያሳየችም «አትጨነቅ፤ ይህንን መጠቀም ትችላለህ» አለችኝ።

እርቃነ ገላዋን ላለመመልከት የተቻለኝን ጥረት አደርግሁ።

በፍትወት እየነደደች በዝግታ መጥታ እንደገና አቀፈችኝ።

ወደ ኋላ እያፈገፈግሁ «አይሆንም ሎይስ፥ ነግሬሻለሁ፤ አሁን ክርስቲያን ነኝ። እንደገና ወደ ዝሙት አልመለስም» አልኳት።

«ክርስቲያን ብትሆንም እንኳ አሁንም ወንድ ነህ፤ አይደለህም እንዴ? እስኪ ልየው» እያለች ቀበቶዬን ትፈታ ጀመር።

አእምሮዬ ክርስቲያን ያልነበርኩበትን ዘመን መዳሰሱን ቀጠለ። አንዲት ሴት ልጅ ቀሚሷን እንድታወልቅልኝ ለማሳመን ምን ያህል መልፋት ነበረብኝ! አሁን ደግሞ እነሆ ልታስወልቀኝ የምትፈልግ ልጃገረድ ከፊቴ ቆማለች! ላስቆማት መሞከሬ ምንኛ ጅልነት ነው!

ሎይስ ከሩቅ መፈተኔን ተመለከተች። ይህ ደግሞ ድርጊቱን እንድትገፋበት የልብ ልብ ሰጣት።

የሆነ ሆኖ እንደ ምንም ብዬ የምቃወምበትን ጉልበት አገኘሁ።

«ስሚ ሎይስ፥ አላደርገውም። አሁኑኑ ልብስሽን ልበሺ» አልኳት ቀበቶዬን እያጠበቅሁ።

አነጋገሬ ቁርጠኛ ስለነበር እኔን አስደነቀኝ። «እዚያ እጠብቅሻለሁ» ያልኳት ፊቴን አዙሬ ወደ እንግዳ ማረፊያ ክፍሉ እየተራመድኩ ነበር።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ብቅ አለች። ልብሷን የለባበሰች ሲሆን ዓይኖቿ በእንባ ታጥበዋል። «ስለማትወደኝ አዝናለሁ» አለች ዓይኖቿን በለስላሳ ወረቀት እያበሰች።

«እወድሻለሁ» አልኳት በእውነተኝነት። «በጣም ቆንጆ ልጅ ነሽ፤ ነገር ግን እንድትወስኚና ጌታን እንድትቀበዪ እፈልጋለሁ» አልኳት።

ሎይስ ዝም ብላ ዓይኖቿን መጠራረግ ቀጠለች።

ወደ ዋናው በር አብሬያት ተራመድኩ፤ ቁልፉን ከፈትኩና «ደህና ሁኚ» አልኳት። ርቃ ከሄደች በኋላ በሩን ከውስጥ ቆልፍኩና ራሴን በእጆቼ ደግፌ ተቀመጥሁ።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ አሳቦች ወደ አእምሮዬ ጎርፉ። «ምን ዓይነት ጅል ነኝ?» ይል ነበር አንዱ የአሳቤ ክፍል። «ባደርገው የእኔ ስሕተት አልነበረም፤ እራሷ ጠይቃኝ. . . ስትለምነኝ»።

ሮጬ ሄጄ መልሼ ላመጣት ተመኘሁ።

ነገር ግን አልሆነም። ዛሬ በኃጢአተኛው ተፈጥሮ ላይ ድልን እንደ ጨበጥሁ ተረዳሁ። ያንን ድል አሁን ላጣው አይገባም። ወደ ቀደመው ሕይወቴ ብመለስና ከልጃገረዶች ጋር ብቀብጥ ፍጻሜዬ ምን ይሆናል?

**ኃጢአት ሊያጠፋኝ ይፈልጋል፤ እኔ ኃጢአትን መግደል አለብኝ፤ ያለበለዚያ እርሱ ይገድለኛል።**

ብሩስ፥ ክርስቲያን መሆን ቀላል አይደለም! አሁን ግን ካገባሁ በኋላ እንኳ በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ የልጃገረዶችን ፈተና መቋቋም እንዳለብኝ ተረድቼአለሁ።

ልምምዱ አስቸጋሪ ነው፤ ቢሆንም ጌታዬ ይወደኛል!

እግዚአብሔር ያዘጋጀልኝን ድንቅ ወይዘሪት እስካገባ ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመፈጸም እችላለሁ።

ውድ ዮሴፍ፥

እንዴት ያለ ድል ነው! በፍርድ ቀን ስለዚህ ድል በጣም ደስ ትሰኛበታለህ (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡10)።

በምታገባም ጊዜ ሚስትህ ለሌሎች ሴቶች «አይሆንም» እያለ መንፈስ ቅዱስን የሚታዘዝ ባል በማግኘቷ ደስ ትሰኛለች (መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 6፡3 እና 8፡6–7)።



# Books You Should Read!




Teenage girls love this book! So do parents!




For all serious Christians. Power to do God's work!




Young men love this book! It gives surprising answers from the Bible!




A book for married people, not for single young people. Sex, Pregnancy, Adultery...

WRITE TO: S. NHLAPO, MANAGER, BOX 1114, ROODEPOORT, 1725, SOUTH AFRICA